# ገ

**ገ** ከ"**ጀ**" ፊደል ዘር ቀጥሎ የሚመጣ የአማርኛ ፊደል (ግእዙ ሆሄ)::

**ገሃ** ስ 1. ጠንካራነት የሌለው፥ በቀላሉ ፍርክስክስ የሚልና እርጥበት ቶሎ የሚለየው የአፈር አይነት:: 2. በፍም የሚበስል ብርኩታ፥ ቂጣ::

**ገሃነም** ስ ሃጢአት የሰራ ወይም በደል የፈፀመ ሰው ከሞት በሂላ ቅጣት ይቀበልበታል ተብሎ በሃይማኖት ሰዎች ዘንድ የሚታመንበት የስቃይና የፍዳ ቦታ::

**ገሃነመ እሳት** ዝ.ከ.

**ገሃድ** ስ 1. ስውር ያልሆነ፥ ግልፅ ወይም ይፋ:: 2. "**ጋድ**" ን ተመ.

***ገለለ**

**ገለልተኛ** ቅ 1. በሰው ነገር ጣልቃ የማይገባ:: 2. ከሌላው ነጠል ወይም ራቅ ብሎ ያለ::

**ገለልተኛ አገሮች** ስ ሃያላን ተብለው ከሚታወቁት አገሮች ጋር ከየትኛውም ያልወገኑ ወይም የእነሱ ተባባሪ ያልሆኑ አገሮች::

**ግላሉ (ገላሉ÷ጋለሉ)** ስ ከእርሻና ከአዝርእት መሃል ተነቅሎ ወደ ውጭ የሚጣል አረም::

**ግል** በፊደል ተራው ተመ.

**ተገለለ** ግ ተለየ፥ ተነጠለ፥ ራቀ፥ ብቸኛ ሆነ::

**አገለለ** ግ ለየ፥ ነጠለ፥ አራቀ፥ ለብቻ አደረገ::

**ገለመጠ** "**ገላመጠ**" ን ተመ.

**ገለማ** ግ 1. ብዙ ከመመገብ የተነሳ አንገፈገፈ(ብዙ ጊዜ ጣፋጭ ነገር):: 2. ጣእሙ ወይም ሽታው ተበላሸ (ብዙውን ጊዜ ምግብ)::

**ገለሞተ**

**ገለሞተች** ግ ጋለሞታ ሆነች::

**ጋለሞታ** ስ 1. እድሜዋ ለትዳር ደርሶ ያላገባችና ብቻዋን የምትኖር ሴት:: 2. ባል አግብታ የሞተባትና ብቻዋን የምትኖር ሴት:: 3. ሽርሙጣ፥ አመንዝራ ሴት:: 4. ባል ፈታ ብቻዋን የምትኖር ሴት::

**ግለሙትና** ስ 1. የብቸኝነት ኑሮ (ለሴት) 2. የዝሙት ኑሮ፥ሽርሙጥና ::

**አገለሞተ** ግ ከባልዋ የተፋታች ሴትን አስጠጋ ወይም ረዳ::

***ገለሰለሰ**

**ገለስላሳ** ቅ ክፍል ክፍል ብሉና ተዘናፍሉ የሚታይ (የጤፍ ዛላ፥ ሳር፥ ፀጉር)::

**ተግለሰለሰ** ግ ክፍል ክፍል ብሎ ተዘናፈለ ወይም ተኛ (የጤፍ ዛላ፥ ፀጉር፥...)::

**አግለሰለሰ** ግ ክፍል ክፍል ብሎ እንዲዘናፈል ወይም እንዲተኛ አደረገ (የጤፍ ዛላን፥ ፀጉርን፥...)::

**ገለሰሰ** ግ 1. ገለፈጠ ወይም ድድን አሳየ:: 2. (ሰው ወይም ነፋስ) ዛፍን ከስር ነቅሎ ጣለ፥ ገረሰሰ፥ ገነደሰ::

**ተገለሰሰ** ግ ተገረሰሰ፥ ተገነደሰ (ዛፍ)::

**ገለበ**[1] ግ እንደ ቀሚስ ያለ ልብስን በመግለጥ ወይም በመግፈፍ እርቃንን አሳየ፥ ራቁት አደረገ::

**ተገለበ** ግ ተገለጠ፥ እርቃኑን ቀረ፥ ተራቆተ::

**ገለበ**[2] ግ ላይ ላዩን ብቻ አቃጠለ፥ አሳረረ(እሳት):: *ሳሮውን እሳት ገለበው::*

**ግልብ** ቅ 1. በደንብ ያልበሰለ ወይም ላይ ላዩን ብቻ እሳት ያገኘው::2. (ዘይ.) ሀ. በጠለቀ እውቀት ላይ ያልተመሰረተ ወይም በደንብ ጥናት ያልተደረገበት፥ ብስለት የለሌው:: *ያቀረበው ሃሳብ ግልብ ነው::* ለ. የጠለቀ እውቀት የሌለው፥ ጥራዝ ነጠቅ (ሰው)::

**ተገለበ** ግ ላይ ላዩን ተቃጠለ ወይም አረረ::

***ገለበለበ**

**ግልብልብ** ቅ በፍጥነት ቶሎ ቶሎ የሚነድ ወይም የሚቃጠል (እንደሳርና ገለባ ያለ ነገር)::

**ተግለበለበ** ግ በፍጥነት ቶሎ ቶሎ ነደደ፥ ተንቀለቀለ፥ ተንበለበለ::

**አግለበለበ** ግ በፍጥነት ቶሎ ቶሎ አንቀለቀለ፥ አነደደ፥ አንበለበለ::

**ገለበጠ** ግ 1. አንድን ነገር ከአንድ እቃ ወደ ሌላ እቃ አዛወረ:: 2. አጋባ፥ ባዶ አደረገ::3. ደፋ፥ ከነበለ:: 4. በብዛት ጠጣ ወይም ከለበሰ:: 5. ለወጠ፥ ቀየረ (ፍርድን፥ ሃሳብን፥. . .):: 6. የውስጡን ወደ ውጭ ወይም የታቹን ወደ ላይ በኩል አደረገ::7 አንድን ፅሁፍ ከሌላ ፅሁፍ ላይ እየወሰደ ፃፈ ወይም ቀዳ:: 8. ከአንድ ቋንቋ ወደ ሌላ ተረጎመ :: 9. በሃይል ስልጣን ነጠቀ ወይም ወሰደ:: *የዘውድ አገዛዙን የገለበጠው ወታደር ነው::*

**ገልብጥ** ቅ (ስድብ) ጠዉ፥ ቀምቃሚ::

**ገልባጣ** 1. በአንድ አሳብ የማይረጋ፥ አቋም የለሽ፥ ወላዋይ:: 2. ቅርፁ እንደ ሰፌድ ወይም ዝርግ ሰሃን ያለ ሆኖ ከስረኛው ወይም ከታችኛው ክፍል ወደላይ የተለመጠ፥ ገላላ (እቃ)::

**ገልባጭ** ቅ ገልብጥ::

**ገልባጭ መኪና** እንደ አፈር፥ አሸዋ፥ ድንጋይ ያሉትን ነገሮች ተጭኖ ሌላ ቦታ በመውሰድ ያለ ሰው ጉልበት በራሱ ሃይል ማራገፍ የሚችል መኪና::

**ግልባጭ** ስ ቅጅ፥ ኮፒ (የፅሁፍ)።

**ግልብጥ** ቅ 1. የውስጠኛው ክፍል ወደላይ የሆነ ወይም የተገለበጠ። 2. ወላዋይ፥ በሃሳቡ የማይረጋ፤ የቀድሞ ሃሳቡን ለውጦ ተቃራኒውን የያዘ። ስ 3. አሰራሩ ወደ ውጭ የሆነ ጉንጉን፤ የሹርባ አይነት።

**ተገለበጠ** ግ 1.ተደፋ፥ ተከነበለ። 2.የውስጠኛው ወይም የታችኛው ክፍል ወደ ውጭኛው ወይም ወደላይኛው በኩል ሆነ።3. ተለወጠ፥ ተቀየረ (በፊት ከነበረው አስተሳሰቡ፥ እምነቱ፥...)። 4. በሃይል ከስልጣኑ ተወገደ ወይም ወረደ። 5. ተተረጎመ፥ ተወሰደ። *ይህ ቃል ከእንግሊዘኛ የተገለበጠ ነው።* 6. ከሌላው ነገር ላይ ተቀዳ፥ ተፃፈ።

**ተገለባበጠ** ግ 1. ተተረማመሰ፥ ተመሰቃቀለ። 2. ተቀያየረ፥ ተለዋወጠ (ሃሳብ፥ ውሳኔ፥...)። 3. በፊት የነበረው ሃሳቡ፥ ውሳኔው፥ አቋሙ ተለወጠ ወይም ተቀየረ።

**ተገለባባጭ** ቅ ሃሳቡን የሚቀያይር፥ ወላዋይ፥ በአንድ አቋም የማይፀና።

**ተገላበጠ** ግ 1. ከነበረበት ከአንደኛው ወገን፥ አቅጣጫ ወይም ጎን ወደ ሌላው ወገን ወይም አቅጣጫ ዞረ። 2. በመግዛትና በመሸጥ ሂደት ላይ ገንዘቡ ተንቀሳቀሰ። 3. ከመወፈር የተነሳ ከወደመቀመጫ በኩል ያለ የሰውነት ክፍል በመራመድ ጊዜ ጎልቶ በሚታይ ሁኔታ ተንቀሳቀሰ።

**አገለባበጠ** ግ 1. አተረማመሰ፥ አመሰቃቀለ። 2. ቀያየረ፥ ለዋወጠ። 3. ሸቀጥን በመግዛትና በመሸጥ ገንዘብን አንቀሳቀሰ።

**አገላበጠ** ግ 1. አለዋወጠ፥ አቀያየረ፥ አዘዋወረ። 2. ሸቀጥን በመግዛትና በመሸጥ ገንዘብ አንቀሳቀሰ። 3. መታ፤ አንቆራጠጠ (በዱላ)። 4. እየገለጠ አየ (መፅሃፍን፥ መፅሄትን፥...)።

**አስገለበጠ** ግ እራሱ የፃፈውን ወይም የሰራውን ሌላ ሰው እንዲቀዳ፥ እንዲፅፍ ፈቀደ፤ አስኮረጀ።

**ገለባ** ስ 1. የተሰባበረ የገብስ፥ የስንዴ፥... አገዳ ወይም የብርእ ድቃቂ። 2. የእህል አሰር፥ ንፉሽ፥ እንግውላይ። 3. (ዘይ.) ቀላል፥ ፍሬቢስ ቁም ነገር የሌለው።

***ገለታ**

**ግልቱ** ቅ ከርታታ፥ ባካና፥ ባተሌ።

**ተንገላታ** ግ ተጉላላ፥ ተንከራተተ።

**አንገላታ** ግ አጉላላ፥ አንከራተተ።

**ገለታ** ስ ወሮታ፥ ውለታ፥ ብድራት።

***ገለወደ**

**ገልዋዳ** ቅ (ስድብ) ስራ ፈቶ ወዲያ ወዲህ የሚል፥ አውደልዳይ።

**ተንገላወደ** ግ ስራ ፈቶ ወዲያ ወዲህ አለ፥ዞረ።

**አንገላወደ** ግ ስራ አስፈታ፥ ወዲያና ወዲህ አንቀዋለለ።

***ገለደመ**

**ግልድም** ስ ከወገብ በታች ሰውነት ላይ ተጠምጥሞ የሚለበስ ብትን ወይም ዝርግ ጨርቅ፤ሽርጥ።

**ግልድሞሽ** ዝ.ከ.

**ተገለደመ** ግ በወገብ ላይ ታሰረ፥ ተሸረጠ (ያልተሰፋ ብትን ጨርቅ፥ ሽርጥ)።

**አገለደመ** ግ አሸረጠ፤ ከወገቡ በታች ሰውነቱ ላይ በመጠምጠም ያልተሰፋ ጨርቅን ወይም ግልድምን ለበሰ።

**ገለዶ** ስ ቅርፀ ደጋን የበግ ፀጉር መሸሰቻ ቢላዋ።

***ገለጀጀ**

**ገልጃጃ (ገለጀጅ)** ቅ (ስድብ) ቂል፥ ሞኝ፥ ነሁላላ ፥ጅል።

**ተንገላጀጀ (ተንገለጀጀ)** ግ ተጃጃለ፥ ሞኝ ሆነ፥ ቄለ።

**አንገላጀጀ (አንገለጀጀ)** ግ አጃጃለ፥ አቄለ፥ ሞኝ አደረገ።

***ገለገለ**

**ግልጋሎት** ስ ጥቅም፥ስራ።

**ተገለገለ** ግ ለአንድ አይነት ተግባር ተጠቀመ። *በባንኩ የተገለገለው ብዙ ሰው ነው / መኪናውን ለስራ ብቻ ተገልገልበት።*

**ተገልጋይ** ቅ ተጠቃሚ ።

**አገለገለ** ግ 1. ጥቅም ሰጠ ወይም ጥቅም ላይ ዋለ። 2. ተቀጣሪ በመሆን ወይም በሌላ መልክ ስራ ሰራ፤ የጉልበት፥ የእውቀት አገልግሎት አበረከተ።

**አገልጋይ** ቅ ተቀጥሮ የሚያገለግል (ብዙውን ጊዜ በግለሰብ ቤት ውስጥ)።

**አገልግሎት** ስ ጥቅም፥ ስራ።

**ከአገልግሎት ውጭ ነው** አርጅቷል ወይም ተበላሽቷል፥ ጥቅም አይሰጥም።

**የአገልግሎት** አንድ ሰው ለተሰጠው ግልጋሎት የሚከፍለው ተጨማሪ ክፍያ ወይም አንድ ሰው ለሰጠው አገልግሎት የሚከፈለው ተጨማሪ ክፍያ።

**የአገልግሎት ካሳ** ስ አንድ ሰው ተቀጥሮ ካገለገለበት መስሪያ ቤት ሲለቅ ወይም መስሪያ ቤቱ ሲፈርስ መስሪያ ቤቱ የሚሰጠው ገንዘብ ።

**የአገልግሎት ዘመን** አንድ ሰው ወይም ነገር የሰራበት ወይም የሚሰራበት፥ ጥቅም የሰጠበት ወይም የሚሰጠበት ጊዜ።

**ገለጠ (ገለፀ)** ግ 1. ገፈፈ፥ ገለበ፥ ከፈተ (ልብስን፥መጋረጃን፥የተሸፈነን፥የተከናነበን ነገር)።

2. ወለል አለ፥ ብርሃን ሆነ፥ ጠራ፤ ለቀቀ። *ወለማው ገለጠ።* 3. ምስጢርን በይፋ አወጣ፥ ተናገረ ወይም አወራ። 4. አስረዳ፥ አብራራ፥ አፍታታ፥ ግልፅ አደረገ።

**መግለጫ** ስ 1. ስለአንድ ጉዳይ በፅሁፍ ወይም በቃል የሚቀርብ ማብራሪያ። 2. አንድ ምልክት ስለሚወክለው ሃሳብ ማብራሪያ ሆኖ የሚያገለግል ፅሁፍ።

**ገለፃ(ገለጣ)** ስ ማብራሪያ፥ መግለጫ ።

**ገላጣ** ቅ ሜዳ፥ መስክ ወይም በላዩ ላይ የተሰራ ወይም የበቀለ ነገር የሌለበት፥ በምንም ነገር ያልተሸፈነ (ባዶ መሬት)።

**ግላጭ** (ብዙ ጊዜ ከ "በ" ጋር ይነገራል) ስ 1. ያለምንም ተሻሚ፥ ለብቻ። *የሚፈልገውን በግላጭ ላገኘው።* 2. ዝናብ ወይም ደመና የሌለው፥ ብራ (ቀን፥ ሰማይ)።

**ግልፅ (ግልጥ)** ቅ 1. ገሃድ፥ ይፋ። 2. ሽፍን ወይም ድፍን ያልሆነ። *ግልፅ መኪና። 3.* የተብራራ፥ ቀላል፥ ውስብስብ ያልሆነ (ሃሳብ፥ ፅሁፍ፥...)።

**ተገለጠ** ግ 1. ተገፈፈ፥ ታየ፥ተከፈተ (የተሸፈነ ነገር)። 2. ይፋ ወጣ፥ ተነገረ ወይም ተወራ (ምስጢር)። 3. ግልፅ ሆነ፥ ታወቀ፥ታየ።

**ተጋለጠ** ግ 1. የፈፀመው ድርጊት ይፋ ወጣ፥ ታወቀበት። 2. ለአደጋ፥ለእፍረት፥... ተዳረገ፥ ተጋፈጠ። 3. ችግር ወይም አደጋ ሊደርስበት ሆነ፤ ለአደጋ ወይም ለችግር ተመቻቸ።

**አጋለጠ** ግ 1. አሳልፎ ሰጠ፥ ወነጀለ (ምስጢር በማውጣት)። 2. አንድን ነገር አብሮ ለማድረግ ከተስማማ በሗላ ሃሳቡን ለውጦ አፈገፈገ፤ አጋፈጠ።

**ገለጠመ** ግ 1. ሰበረ፥ ቀለጠመ፥ አነከተ። 2. ገረሰሰ፥ ገነደሰ፥ ጣለ(ዛፍን)። 3. (ዘይ.) ናቀ፥ ሰደበ፥ አዋረደ።

**ገለጠጠ** ግ በለጠጠ፥ በጣም ገለጠ።

**መገለጢጥ** ቅ (ስድብ) በሆነው ባልሆነው የሚስቅ፥ ገልፋጣ።

**ገልጣጣ (ገለጠጥ)** ቅ መገለጢጥ።

**ተገለጠጠ** ግ ተበለጠጠ፥ በጣም ተገለጠ።

**ተንገለጠጠ** ግ ተገለጠጠ።

**አንገለጠጠ** ግ ገለጠጠ።

**ገለፀ** "ገለጠ"ን ተመ.

**ገለፃ** "ገለጠ" ስር ተመ.

**ገለፈት** ስ 1. ቅርፊት፥ ልጣጭ፥ ሽፋን (የጥራጥሬ፥...)። 2. የእባብ ቆዳ ግልፋፊ።

**ገለፈጠ** ግ 1. በሆነ ባልሆነው ነገር ሳቀ፤ ድዱን ገለጠ። 2. ላጠ፥ ገለፈፈ።

**ገልፋጣ (ገለፈጥ)** ቅ (ስድብ) በሆነ ባልሆነ ነገር የሚስቅ፤ መገለጢጥ።

**ግልፍጥ** ዝ. ከ.

**ተገለፈጠ** ግ ተላጠ፥ ተገለፈፈ።

**ገለፈፈ** ግ ላጠ፥ ገፈፈ (ገለፈትን፥ ቆዳን)።

**ገለፈፍ (ገልፋፋ)** ቅ ሞኝ፥ ጅል፥ ቂል።

**ግለፋፊ** ስ ልጣጭ፥ ቅርፊት።

**ግልፍፍ** ቅ ገለፈፍ።

**ተገለፈፈ** ግ ተላጠ፥ ተነሳ (ቆዳ፥ ቅርፊት፥..)።

**ገላ** ስ ከላይ የሚታየው ሰውነት ወይም አካል።

**ገላው ነውር አወጣ** ገላው አበጠ ወይም ቆሰለ ወይም ለምፅ ወጣበት።

**ገላውን ሰደደ** አረፈ፥ ፍርሃት አልባ ሆኖ ያለ ስራ ወይም ያለ ስጋት ተቀመጠ።

**የገላ ሳሙና** ስ በተለይ ለሰውነት መታጠቢያ የተሰራ ሳሙና።

**ገላ ነክ** ስ ከውስጥ የሚለበስና በቀጥታ ገላ ላይ የሚያርፍ (ውስጥ ልብስ፥ ሙታንታ)።

**ገላሎ** "*ገለለ" ስር "ግላሎ"ን ተመ.

**ገላመጠ (ገለመጠ)** ግ 1. በግልምጫ አይን ተመለከተ። 2. አቃጠለ፥ ፈጀ(የእሳት ወላፈን)።

**ግልምጫ** ስ የጥላቻ፥ የንቀት፥ የቁጣ አስተያየት።

**ተገላመጠ** ግ 1. ወደ ሗላ ወይም ግራና ቀኝ ዞር ዞር እያለ አየ። 2. ገላመጠ።

**ገላገለ** ግ 1.ለያየ ወይም አስጣለ፥ ከለከለ (እየተደባደቡ ወይም እየተጣሉ ያሉ ሰዎችን)። 2. አስታረቀ፥ አስማማ። 3. ከችግር፥ ከመከራ፥... አሳረፈ፥ አላቀቀ።

**ገላጋይ** ቅ ተው ባይ፥አስታራቂ።

**ገላግሌ** ቅ የሚያረካ፥ የሚያስደስት፥ አንጀት አርስ።

**ግልግል** ስ 1. እፎይታ፥ እረፍት። 2. እርቅ፥ ሽምግልና።

**ተገለገለ** ግ ልማታ ወይም ልደባደብ አለ፤ ተጋበዘ።

**ተገላገለ** ግ 1. ከችግር፥ ከስቃይ፥ ከጭንቀት፥... ተላቀቀ፥ አረፈ። 2. ታረቀ፥ ተስማማ።

**ተገላገለች** ግ ወለደች።

**አገላገለ** ግ 1. አለያየ፥ ከለከለ፥ አስተወ፥ ገላገለ (እየተደባደቡ ወይም እየተጣሉ ያሉ ሰዎችን)። 2. አዋለደ።

**ገላጣ** "ገለጠ" ስር ተመ.

**ገል** ስ በአብዛኛው ለእሳት መጫሪያ የሚያገለግል

የሽከላ እቃ ስባሪ::

**ገልባጭ** "ገለበጠ" ስር ተመ.

**ገልብጥ** ዝ. ከ.

**ገልቱ** ቅ (ስድብ) ሙያ ቢስ፥ ረሀጥ::

**ገልዋዳ** "ገለወደ" ስር ተመ.

**ገልጃጃ** "*ገለጀጀ" ስር ተመ.

**ገልጣጣ** "ገለጠጠ" ስር ተመ.

**ገልፋጣ** "ገለፈጠ" ስር ተመ.

**ገልፋፋ** "ገለፈፈ" ስር ተመ.

**ገመለ** ግ 1. በወፍራሙ የተበካን የማሽላ ወይም የበቆሎ ሊጥ በወፍራሙ ጋግሮ ሳይበስል አወጣ:: 2. ወፍራምና የማያምር እንጀራ ጋገረ::

**ግምል** ስ 1. ሳይበስል የወጣ ዳቦ ወይም ቂጣ:: ቅ 2. (ዘይ.)ከተቀመጠበት የማይነሳ፥ ውዝፍ፣ ስነፍ::

**ተገመለ** ግ ተጋግሮ ሳይበስል ወጣ (ቂጣ፥ዳቦ፥...)::

**ገመመ** ግ ሰበረ ወይም ጎረደ (የሸክላ እቃ አንገትን)::

**ገመሞ** ቅ አንገቱ የተሰበረ ወይም የተሸረፈ (እንስራ፥ ገንቦ፥...)::

**ገመሞ ራስ** ስ (ስድብ) ትልቅና ሞላላ የሆነ ራስ::

**ገመምተኛ** "*ገገመ" ስር ተመ.

**ገመረ** ግ አደገ፥ ተለቀ፥ ከፍ አለ::

**ገመሬ [ዝንጀሮ]** ስ ትልቅ አውራ ዝንጀሮ::

**ገመሮ** "ጉመሮ"ን ተመ.

**ገመሰ** ግ 1. ሁለት ቦታ ከፈለ፥ ሁለት አደረገ:: 2. አረሰ፥ሰነጠቀ(መሬትን):: 3. ፈነከተ፥ ተረተረ::

**ገሚስ** ቅ ግማሽ ወይም እኩሌታ::

**ግማሽ** ቅ አንድ ሁለተኛ ወይም የአንድ ነገር እኩሌታ::

**ግማሽ ቀን** ስ ከሰአት በፊት ወይም ከሰአት በሗላ ያለው ቀን::

**ተጋመሰ** ግ 1. እኩል ተጋራ ወይም ተካፈለ:: 2. ግማሽ ላይ ደረሰ፥ ሊያልቅ ተቃረበ::

**ተጋማሽ** ቅ ግማሽ ወይም እኩሌታ::

**አጋመሰ** ግ 1. አካፈለ ወይም አጋራ:: 2. ግማሽ ላይ አደረሰ ወይም ሊጨርስ ተቃረበ::

**አጋማሽ** ቅ ግማሽ ወይም እኩሌታ::

***ገመሸረ**

**ተገማሸረ** ግ 1. አማረበት፥ ተዘናፈለ፥ ዳበረ (ሰብል፥ ሳር፥...):: 2. (ዘይ.) የኩራት አካሄድ ሄደ፣ ተጎማለለ::

**አገማሸረ** ግ አሳመረ፥ አዘናፈለ፥ አዳበረ (ሰብልን፥ ሳርን፥...)::

**ገመተ** ግ 1. በአይን ሀሊና መዘነ ወይም ገመገመ:: 2. ይሆናል ብሎ አሰበ::

**ገማች** ቅ ዋጋ የሚተምን::

**ግምት** ስ 1. የአንድ ነገር (የመጠን ወይም የልክ) ተመን:: 2 ትክክለኛው መጠን፥ ልክ ወይም ሁኔታ ሳይታወቅ በይሆናል እንዲህ ነው ተብሎ የሚሰጥ አስተያየት::

**ተገመተ** ግ 1. በይሆናል ተመዘነ፥ ተለካ፥ ተገመገመ:: 2. በስራው፥ በተናገረው፥... ተመዘነ፥ ተገመገመ፣ ትዝብት ላይ ወደቀ::

**ተገማመተ** ግ እርስ በርስ ተፈታተነ፥ ተሞካከረ (በጉልበት፥ በጠባይ) ::

**አገማመተ** ግ አስተዛዘበ::

**አስገመተ** ግ ትዝብት ላይ ጣለ::

**ገመነ** ግ ተናደደ፥ በገነ::

**ተግመነመነ** ዝ. ከ.

**ገመና** ስ 1. እንዳይታወቅ ወይም እንዳይገለጥ የሚፈለግ ነውር፥ ድክመት፥ እንከን:: 2. ሌላ ሰው እንዲያውቀው የማይፈለግ የራስ ችግር ወይም የግል ሁኔታ::

**ገመና ከታች** ነውርን ወይም ምስጢርን የሚደብቅ ወይም የሚጠብቅ::

**ገመደ** ግ ሸረበ፥ አጠላለፈ (ክርን፥ገመድን፥...)::

**ገመድ** ስ ከፈትል ወይም ከልጥ ወይም ከቃጫ፥... እየተሸረበና እየተጠላለፈ የሚሰራና ለማሰሪያ፥ ለማንጠልጠያ፥.. የሚያገለግል ነገር::



ገመድ

**በገመዱ ገባ** አንዱ በሰራው ወንጀል ወይም ነገር ሌላው ተቀጣ፥ ታሰረ::

**[የ]ገመድ ዝላይ** ስ ጫፍና ጫፉን ተይዞ በጭንቅላት ላይና በእግር ስር የሚዞርን ገመድ በተደጋጋሚ በመዝለል የሚደረግ ጨዋታ::

**ገመድ አፍ** (ስድብ) ተብታባ፥ ኮልታፋ (ለአዋቂ)::

**ገመድ ጉተታ** ስ ቁጥራቸው የተመጣጠነ ሁለት ቡድኖች ከወዲያና ከወዲህ የገመዱን ጫፎች ይዘው በመጎተት አንደኛው ወገን ሌላውን ከተወሰነ ክልል ውስጥ ጎትቶ ለማስገባትና አሸናፊ ለመሆን የሚደረግ የውድድር ጨዋታ::

**ገመደለ** ግ 1. በትልቁ ቆረሰ (ለምሳሌ ዳቦን)::

2. አዛባ፥ አጣመመ (ፍርድን)። 3. አራከሰ፥ ዝቅ አድርጎ ገመተ (ዋጋን)።

**ገመድ** "ገመደ" ስር ተመ.

**ገመገመ** ግ 1. ገመተ፥ ተመነ፥ በአይነ ህሊና ለካ። 2. የአንድን ስራ ሁኔታ፥ ጥራት፥ አሰራር አጥንቶ ወይም አይቶና መዝኖ አስተያየት ሰጠ፤ ድክመትና ጥንካሬውን አሳየ።

**ገምጋሚ** ቅ የአንድን ነገር ጥራት፥ ዋጋ፥ ... ወይም የአንድን ስራ ሁኔታ ወይም ክንውን፥... አይቶ ወይም አጥንቶና መዝኖ አስተያየት የሚሰጥ።

**ግምገማ** ስ የአንድን ስራ ሁኔታ፥ክንውን፥ ጥራት፥... የማየት ወይም የማጥናትና የመመዘን ተግባር።

***ገመገመ**

**ተስገመገመ** ግ ዝናም ሊጥል ተቃረበ፤ ሰማዩ ተጉረመረመ፥ የነጎድጓድ ድምፅ ተሰማ።

**አስገመገመ** ግ አጉረመረመ፥ የነጎድጓድ ድምፅ አሰማ (ሰማይ)።

**ገመገም** ስ የተራራ አግድመት፥ ተረተር።

**ገመጠ** ግ 1. በጥርሱ ቆርሶ በላ (ዳቦን፥ ፍራፍሬን፥...)። 2.ሸረፈ፥ ሰበረ (ለምሳሌ እንስራን፥...)።

**ገማጣ** ቅ ሸራፋ፥ ሰባራ፥ ገመጥ።

**ተገመጠ** ግ ተሸረፈ፥ ተሰበረ።

**ገመጠጠ** ግ አሽሟጠጠ፥ አንጓጠጠ።

**ገምጣጭ** ቅ አሽሟጣጭ፥ ነቃፊ ።

**ገሚስ** "ገመሰ" ስር ተመ.

**ገማ** ግ ከረፋ፥ ሸተተ፥ ጠነባ።

**ግማት** ስ መጥፎ ሽታ፥ ክርፋት።

**ግማታም** ቅ (ስድብ) መጥፎ ሽታ ያለው፥ ክርፋታም።

**ግም** ቅ 1.ቆሻሻ፥ ፅዳት የሌለው፥ መጥፎ ሽታ ያለው። 2. (ዘይ፥ ስድብ) ረሀጥ፥ ሙያ ቢስ፥ ዝርክርክ።

**ተግማማ** ግ ተበላሸ፥ ተበሳበሰ፥ ገማ።

**አገማች** ግ ሳትፈለፍል ቀረች፥ አበሰበሰች (ዶሮዋ እንቁላሏን)።

**አግመቶ በል** ስ ስጋን እስከሚሸት አቆይቶ የሚበላ እንደ ነብር ያለ አውሬ።

**አግማማ** ግ 1. አበሰበሰ፥ አበላሸ፥ እንዲገማ አደረገ። 2 .(ዘይ.)አጥላላ፥ አበሻቀጠ፥ አራከሰ።

**ገማች** "ገመተ" ስር ተመ.

**ገማጣ** "ገመጠ" ስር ተመ.

**ገምባሊ (ገንባሌ)** ስ ከቁርጭምጭሚት አንስቶ እስከ ጉልበት ያለውን የእግር ክፍል የሚያለብስ ከቆዳ ወይም ከሹራብ የሚሰራ የቅልጥም መሸፈኛ ወይም መከለያ።



ገምባሌ

**ገምቤሎ** "ጋምቤሎ"ን ተመ.

**ገምቦ** "ገንቦ"ን ተመ.

**ገምናና(ገምናኔ)** ቅ 1. ኩሩ፥ ጅንን። 2. ጀግና፥ ጎበዝ።

**ገምጋሚ** " ገመገመ" ስር ተመ.

**ገምጣጭ** "ገመጠጠ" ስር ተመ.

**ገሞራ** ቅ ብርቱ፥ ሃይለኛ፥ ጎበዝ።

**ገረመ**[1] ግ 1. ጨመተ፥ ረጋ አለ። 2. ገራም ሆነ፥ ለመደ።

**ገራም** ቅ 1. ቅን፥ ርህሩህ፥ ገራገር። 2. ሃይለኛ ያልሆነ፥ አመለ ለስላሳ (ከብት)።

**ገረመ**[2] ግ ደነቀ። *ወሬውን ስሰማ ገረመኝ።*

**ግሩም** ቅ 1. ቆንጆ፥ ጥሩ። 2. ድንቅ።

**ተገረመ** ግ ተደነቀ፥ እፁብ ድንቅ አለ።

**አስገረመ** ግ አስደነቀ፥ እፁብ ድንቅ አሰኘ።

**አስገራሚ** ቅ አስደናቂ።

**ገረመመ** ግ ገላመጠ፥ በቁጣ አይን አየ።

**ገረመደ (ጎረመደ)** 1. በትልቁ ቆረሰ፥ ገመሰ። 2. ምድርን ገለባበጠ፥ በረቀሰ፥ አረሰ (በመድፍ በቦምብ፥...)።

**ገረረ** ግ 1. በጣም አቃጠለ፥ ከረረ (ፀሃይ)። 2. በጣም ጋለ፥ ሰማ፥ ጠበረረ. (ምጣድ)። 3. ተንበለበለ፥ ነደደ(እሳት)። 4. በጣም ደረቀ፥ ቆረፈደ፥ ተንከፈረረ(ብዙውን ጊዜ ቆዳ)።

**ገራራ** ቅ የጋለ፥ የሚያቃጥል።

**ገረሰሰ** ግ ከስሩ ነቅሎ ጣለ፥ አፈለሰ። *ነፋስ ዛፉን ከስሩ ገርስሶ ጣለው ።*

**ገረሸ**

**ግርሻ** ስ አንድ በሽተኛ እንደ መሻል ካለው በሂላ እንደገና እንደ አዲስ የሚያመው የመጀመሪያው አይነት በሽታ።

**አገረሸ** ግ 1. ተሽሎ ወይም ለቆ የነበረ በሽታ እንደገና አመመ፤ ህመሙ ተመለሰ። 2. (ዘይ.) እንደገና ተነሳ ወይም ተጀመረ (ፀብ፥ ፍቅር፥...)።

***ገረበበ**

**ገርባባ(ገረበብ)** ቅ ግጥም፥ ልስቅ፥ ልክክ የማይል ወይም ያላለ (ከዳን፥ መዝጊያ)።

**ገርበብ አለ** ግ ግጥም ሳይል ቀረ፥ በመጠኑ ከፈት አለ፤ መለስ አለ (ከዳን፥ በር)።

**ገርበብ አደረገ** ግ ግጥም ሳያደርግ ወይም ላላ አድርጎ ከደነ ወይም ዘጋ፤ መለስ አደረገ።

**ተንገረበበ** ግ አልጠጋ ወይም ልክክ አልል አለ፤ ተንከረፈፈ፥ ገርባባ ሆነ።

**አንገረበበ** ግ ገርበብ አደረገ።

**ገረኑክ** ስ መልኩ ቀላ ያለ አሸዋማ ሆኖ ጀርባው ላይ ደመቅ የሚል፥ ጉያውና ደረቱ እንዲሁም የአይኖቹ ዙሪያ ነጭ የሆነ መልክ ያለው፥ ደረቅ በሆኑ ቆላማ ስፍራዎች የሚኖር የዱር እንስሳ፤ ጉጉፍቱም ይባላል (ስእሉን የዱር እንስሳ ስር ተመ.)።

**ገረንገሬ** ስ 1. በወይና ደጋ የሚበቅልና ጥንካሬ የሌለው የዛፍ አይነት። 2. ከገረንገሬ እንጨት የሚገኝ ሙጫ።

**ገረኘ** ግ እግር ከወርች አሰረ፥ ቀፈደደ።

**ገረዘ(ገዘረ)** ግ 1. የወንድን ብልት ልንቡጥ ወይም የወሸላን ሸፋን ቀነጠበ፥ ቆረጠ። 2. የረዘመ የተክልን ጫፍ ቆረጠ፥አስተካከለ።

**ግርዝ** ቅ የተገረዘ።

**ግርዘት(ግዝረት)** ስ የወንድን ብልት ልንቡጥ ወይም የወሸላን ሸፋን የመቁረጥ ድርጊት።

**ተገረዘ** ግ ተቀነጠበ፥ተቆረጠ(የወንድ ብልት ልንቡጥ ወይም ሸፋን ወይም ተክል)።

**ገረዘዘ** ግ ተጫጫነ፥ አሸነፈ፥ ጣለ(ለምሳሌ እንቅልፍ)።

**ገረደ** ግ ገረድ አደረገ።

**ገረድ** ስ በገንዘብ ተቀጥራ ሰው ቤት የምታገለግል ሴት፤ የቤት ሰራተኛ።

**ግርድና** ስ ገረድ ሆኖ ማገልገል።

**ተገረደች** ግ ገረድ ሆነች።

**ገረደሰ** ግ ገነደሰ።

**ገረደፈ** ግ ከካ፥ ሸረከተ(እህልን)።

**ግርድፍ** ቅ 1. ሸርካት፥ ክርትፍ፥ ያልደቀቀ። 2. (ዘይ.) ያልተብላላ፥ ያልበሰለ ወይም በደንብ ጥናት ያልተደረገበት (ሃሳብ፥ አስተያየት፥...)።

**ገረድ "ገረደ"** ስር ተመ.

**ገረጀፈ** ግ ያለእድሜው ሰውነቱ ግዙፍ ሆነ፥ ትልቅ ሰው መሰለ፤ አረጀ።

**ገርጃፋ** ቅ ያለእድሜው ሰውነቱ ግዙፍ የሆነና ያረጀ የሚመስል።

**ገረገረ**[1] ግ 1. ገረገራ ሰራ፤ በግድግዳ መልክ በአጠና አጠረ፥ ገደገደ። 2. እንቅፋት ሆነ፥ አሰናከለ፥ አከላከለ፥ አወከ።

**ገረገራ** ስ 1. በአጠና ወይም በፍልጥ የሚሰራ የቤተክርስቲያን አጥር። 2. በመስመር እንደ አጥር ሆኖ የተተከለ የቤተክርስቲያን አፀድ።

**ገርጋሪ** ቅ እንቅፋት የሚሆን፥ የሚያሰናክል፥ አዋኪ።

**ገረገረ**[2] ግ 1. በረገገ፥ ደነበረ (ከብት)። 2. አቆበቆበ ለመበርገግ ጳርጳር አለ።

**ገርጋሪ** ቅ ደንባሪ፥ ድንጉጥ።

**አገረገረ** ግ ለመበርገግ ወይም ለመደንበር አቆበቆበ፥ ጆሮውን ሸመጠጠ (ከብት)።

**ገረገራ "ገረገረ**[1]**"** ስር ተመ.

***ገረገበ**

**ገርገብ አለ** ግ 1. በመጠኑ በሰለ፥ ሾቀ (ባቄላ፥ አተር፥...) ። 2. ታገሰ ወይም በረድ አለ (ረሃብ፥ ንዴት፥ ቁጣ)።

**ተንገረገበ** ግ በመጠኑ ተቀቀለ ወይም በሰለ፤ ሾቀ (ባቄላ፥ አተር፥...)።

**አንገረገበ** ግ 1. በመጠኑ አበሰለ ወይም ቀቀለ፤ አሾቀ (ባቄላን፥ አተርን፥...)። 2. (ዘይ.) አጠቃ፥ አሸነፈ (ጠላትን)።

**እንግርግብ** ስ በመጠኑ የተቀቀለ (ባቄላ፥ አተር፥...)።

**ገረገደ "ገደገደ"**ን ተመ.

**ገረጋንቲ** ስ ጠጠር፥ ኮረት።

**ገረጣ** ግ 1. ነጣ፥ በሰለ፥ ለመሰብሰብ ደረሰ (ሰብል)። 2. ወዘና ወይም ደምግባት አጣ፤ አመድማ ሆነ።

**ገረፈ** ግ 1. መታ፥ ሸነቆጠ (በአለንጋ፥ በአርጩሜ፥...)።2. ለበለበ፥ ለመጠጠ (የእሳት ወላፈን)። 3. ግድግዳን በአሸዋ፥ በደቃቅ ጠጠርና በሲሚንቶ ድብልቅ በሻካራው መረገ። 4. ወይፈንን ለእርሻ ገራ ወይም አሰለጠነ።

**ግርፊያ** ስ በአለንጋ ወይም በጅራፍ፥... የሚደረግ ምት።

**ግርፋት** ስ 1. ግርፊያ። 2. በተገረፈ ገላ ላይ የሚታይ ሰንበር፥ ቁስል። 3. ብዙውን ጊዜ በአፍ ውስጥና በአፍ አካባቢ እንደ እከክ ሸፍ ብሎ የሚወጣ ቁስል። 4. ምች ።

**ግርፍ** ስ 1. በተገረፈ ሰውነት ላይ የሚታይ ሰንበር፥ ቁስል። 2. እርሻ የተለማመደ ወይፈን። 3. አንድን ስራ፥ ሙያ ፥ እምነት ወይም አስተሳሰብ ከሌላ ሰው በመቅሰም ወይም በመማር በድርጊቱ ወይም በአስተሳሰቡ እንደአስተማሪው የሆነ ሰው። *የእግዜ ግርፍ።* ቅ 4. በአሸዋ፥ በደቃቅ ጠጠር፥ በሲሚንቶ በሻካራው የተመረገ (ግድግዳ)።

**ገረፍ ገረፍ አደረገ** ግ አልፎ አልፎ ወይም ላይ ላዩን ተመለከተ ወይም ተናገረ።

**ተጋረፈው** 1. በአፉ አካባቢ ወይም በአፉ ውስጥ እንደ እከክ ሸፍ የሚል ቁስል ወጣበት፥ አመመው 2. ምች መታው።

**ገራ**[1] ግ ፈረስን፥ በቅሎን አሰለጠነ(እንዲጋልብ፤ እንዲሰግር)።

**ግር** ቅ የተገራ፥ የሰለጠነ (ፈረስ፥ በቅሎ)።

**ተገራ** ግ ተማረ፥ ሰለጠነ (ፈረስ፥ በቅሎ እንዲጋልብ፥እንዲሰግር)።

**ገራ**[2] ግ ለዘበ፥ ገር ሆነ፥ ቀለለ::

**ገር** ቅ 1. የዋህ፥ ቅን፥ ተንኮል የሌለበት:: 2. ጠንካራ ያልሆነ፥ ልል::

**ገራገር** ቅ የዋህ ቅን፥ ተንኮል የሌለበት::

**ገራራ** "ገረረ" ስር ተመ.

**ገራም** "ገረመ[1] " ስር ተመ.

**ገራገር** "ገራ[2]" ስር ተመ.

**ገሬ** ስ 1. ማሩ የተመጠጠ ባዶ የማር እንጀራ፤ ከዳ:: 2. ገመምተኛ (ከወባ በሽታ)::

**ገሬንጭ** ስ የበርበሬ የመጀመሪያው ምርት ወይም ዛላ ከተለቀመ በሂላ በማሳው ላይ ቆሞ የሚቀረው የበርበሬ ተክል፤ ተክሉ በድጋሚ የሚሰጠው ፍሬ ወይም ዛላም ገሬንጭ ይባላል::

**ገር** "ገራ[2] " ስር ተመ.

**ገርባባ** "ገረበበ" ስር ተመ.

**ገርዳሳ** ስ ፀጉርን ወደ ላይ ደግፎ እንዲይዝ ተደርጎ በራስ ዙሪያ የሚታሰር ሻሽ፤ ቀልቤ::

**ገርዳሳ ሻሽ** ዝ.ከ.

**ገርጃፋ** "ገረጀፈ" ስር ተመ.

**ገርጋሪ**[1] "ገረገረ[1] ስር ተመ.

**ገርጋሪ**[2] "ገረገረ[2] ስር ተመ.

**ገርጌሶ** ስ መንቆሩ ጠፍጠፍ ብሎ በጣም ረዥም የሆነ፥ ነጭ ወይም ቡላ መልክ ያለውና ሞቃታማ በሆነ አካባቢ በመንጋ የሚኖር ትልቅ የአሞራ አይነት(ስእሉን አሞራ ስር ተመ.)::

**ገሰረ** ግ በብዛት ጠጣ፤ ገሸረ::

**ገሰሰ**[1] ግ 1. ጣሰ፥ ተላለፈ፥ አፈረሰ(ህግን) :: 2. ሻረ፥ ለወጠ፥ ገለበጠ (ፍርድን):: 3. አጠፋ፥ ወሰደ (ክብረ ንፅህናን)::

**ገሰሰ**[2] ግ ለቀቀ፥ ደበዘዘ፥ ደበሰ(ወርቅ)::

**ገሰሰ**[3] ግ ግስን አረባ::

**ግስ** ስ (ሰዋ.) የአረፍተ ነገር መግቻ፤ ማሰሪያ አንቀፅ ወይም ቃል::

**ተገሰሰ** ግ ረባ (ግስ)::

**ገሰበ** ግ 1. ይህንንም ያንንም ሳይመርጥ በላ ወይም ጠጣ:: 2. በብዛት ጠጣ፤ ገሰረ::

**ገሰገሰ** ግ 1. ቶሎ ቶሎ ተራመደ፥ ተጣደፈ ፥ ፈጠነ:: 2. አደገ፥ ረዘመ፥ ትልቅ ሆነ (ለምሳሌ ተክል):: 3.ተሻሻለ፥አደገ(በእውቀት፥ በስልጣኔ፥...)::

**ገስጋሽ** ቅ ፈጣን ሂያጅ::

**ገሰፀ(ገሰጠ)** ግ 1. ተቆጣ:: 2. መከረ::

**ግሳፄ** ስ 1. ቁጣ:: 2. ምክር::

**ተገሰፀ** ግ 1. ቁጣ ደረሰበት፥ ተቆጣ:: 2.ተመከረ::

**ተግሳፅ** ስ 1. ቁጣ:: 2. ምክር::

**ገሳ** ስ 1 ጠርዙ እንደ ሰይፍ ስለትና ስፋት ያለው በረግረግ ቦታ የሚበቅል የሳር አይነት:: 2. ከገሳና ከቄጠማ የሚሰራ የእረኞች የዝናም ልብስ::

*ገሳ

**ግሳት** ስ 1. ከሆድ ውስጥ በአፍ በኩል የሚወጣ ጋዝ ወይም ብስና:: 2. ከሆድ ውስጥ ጋዝ ወይም ብስና በአፍ በኩል ሲወጣ የሚሰማው ድምፅ::

**ግሳታም** ቅ (ስድብ) ብስናታም::

**አገሳ** ግ 1. ከሆዱ ውስጥ በአፉ በኩል ጋዝ ወይም ብስና አስወጣ:: 2. አስገሳ:: 3 ለማስፈራራት፥ ቁጣን ለመግለፅ፥... ከፍተኛ ደምፅ አሰማ (አንበሳ፥ በሬ፥...)::

**አስገሳ** ግ ከሆድ ውስጥ በአፍ በኩል ጋዝ ወይም ብስና እንዲወጣ ምክንያት ሆነ (ምግቡ፥ መጠጡ፥ ...)::

**ገስጋሽ** "ገሰገሰ" ስር ተመ.

**ገሶ** ስ ደንጎራ፤ ረዘምና ቀጥ ያለ እጀታ ያለው መጥረቢያ መሰል የጉድጓድ መቆፈሪያ::

**ገሸለጠ** ግ 1. ላጠ፥ መለጠ፥ ገፈፈ(ሽፋንን፥ ቆዳን):: 2. ገረፈ:: 3. ፋቀ ወይም መለጠ (የቁርበት ፀጉርን):: 4. ስጋን ከአጥንት ለየ፥ ላጠ:: 5. ፈጀ፥ ለበለበ፥ አቃጠለ(የፈላ ውሃ ወይም እሳት):: 6. መነተፈ፥ ወሰደ፥ በላ (ገንዘብን):: 7. (ዘይ.) አማ::

**ግሽልጥ** ቅ የተገሸለጠ፥ ምልጥልጥ፥የተላጠ፥ መለመላውን የቀረ::

**ተገሸለጠ** ግ 1. ተላጠ፥ ተገለፈፈ፥ ተገፈፈ(ሽፋን፥ ቆዳ፥...):: 2. ተመለጠ፥ ተነሳ (የቁርበት ፀጉር):: 3. ተላጠ፥ ተለየ፥ ተላቀቀ(ስጋ ከአጥንት)::

**ተገሸላለጠ** ግ ተላላጠ፥ ተመላለጠ::

**ገሸረ**[1] ግ 1. በአንድ ቦታ ለረጅም ጊዜ እንዲቀመጥ አደረገ:: 2. አቆየ፥ አዘገየ፥ አስቀመጠ (ለምሳሌ ስራን)::

**ተገሸረ** ግ በአንድ ቦታ ለረዥም ጊዜ ተቀመጠ::

**ግሽር** ስ የጋን ወይም የማድጋ ውሃ::

**ገሸረ**[2] ግ በብዛት ጠጣ::

*ገሸሸ

**ገሸሽ አደረገ** ግ ችላ አለ፥ ተወት አደረገ፥ አገለለ::

*ገሸገሸ


**ግሽግሽ አለ** ግ ተንገሸገሸ::

·**ግሽግሽ (እንግሽግሽ) አደረገ** ግ አንገሸገሸ::

**ተንገሸገሸ** ግ ተማረረ፥ ተሰላቸ፥ ተንገፈገፈ::

**አንገሸገሸ** ግ 1. አስመረረ፥አሰለቸ፥አንገፈገፈ::

2. መረረ፥ ጎፈነነ።



**ገበሎ** ስ ረዥም ጭራ፥ አራት እግርና ሻካራ ቆዳ ያለው፥ ከተሳቢ እንስሳት ወገን የሚመደብ አነስተኛ እንስሳ።

**ገበረ** ስ 1. ግብር ሰጠ፥ ከፈለ። 2. ለጥ ሰጥ አለ፥ አሜን ብሎ ተገዛ።

**መገበሪያ** ስ 1. ግብር ወይም አስራት የሚገበርበት ቦታ ወይም ገበሎ ጊዜ። 2. (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) ለቁርባን ወይም ለመስዋእት እንዲሆን ለቤተክርስቲያን የሚሰጥ ነጭ ስንዴ።

**የመገበሪያ ቁና** ስ በአንዳንድ አካባቢዎች ገበሬው ለቤተክርስቲያን ወይም ለመንግስት የሚሰ ጠውን እህል የሚሰፍርበት ቁና።

**ገባር** ስ የራሱ የሆነ ርስት የሌለውና የሌላ ሰው ርስት እያረሰ ለባለመሬቱ ግብር ይከፍል የነበረ ገበሬ ወይም አራሽ።

**ግብር** ስ 1. ገቢ ያለው ዜጋ ሁሉ በተወሰነ ጊዜ እንደገቢው መጠን ለመንግስት የሚከፍለው የተወሰነ ገንዘብ። 2. በቤተ መንግስት ወይም በታላላቅ ባለስልጣናት ቤት ይደረግ የነበረ ግብዣ። 3. ቀደሞ ገበሬ ለሚያርሰው መሬት ለመንግስት፥ ለመልከኛ፥... በእህል፥ በገንዘብ፥ በከብት፥ በጉልበት ስራ፥... መልክ ያደርግ የነበረው ክፍያ።

**ግብር ገባ** በቤተመንግስት ወይም በታላላቅ ባለስልጣናት ቤት በሚደረገው ግብዣ ላይ ተጋባዥ ሆኖ ተገኘ።

**ግብር አገባ** አንድ ባለስልጣን ወይም ንጉስ ድግስ አዘጋጅቶ ብዙ ሰዎችን ጋበዘ።

**የግብር ይውጣ** የግዴለሽነት ወይም ከልብ ያልሆነ ድርጊት።

**የግብር ስንዴ** የ "መገበሪያ"ን ሁለተኛ ፍቺ ተመ.

**ግብረ በላ** በድሮ ጊዜ ደመወዝ ወይም ሌላ መተዳደሪያ የሌለውና በንጉስ፥ በመሳፍንት፥... ቤት እየተቀለበ የሚኖር (ሰው)።

**ግብረ ጠል** ቅ ለያዘው መሬት ለመንግስት ግብር ያልከፈለ።

**አስገበረ** ግ አንድን አካል በጦር ወይም በሃይል አሸንፎ እንዲገብርለት አደረገ።

*ገበረ[1]

**ምግባር** ስ 1. ስራ፥ አድራጎት። 2. ባህርይ ወይም ጠባይ።

**ምግባረ መልካም** ቅ ጥሩ፥ የሚያስመሰግን ባህርይ ወይም ጠባይ ያለው።

**ምግባረ ሰናይ** ስ መልካም ስራ።

**ገቢር[ግስ]** ስ (ሰዋ.) ቀጥተኛ ተሳቢ የሚያስፈልገው የግስ አይነት፤ አድራጊ ግስ።

**ገባሬ ሰናይ** ስ 1. በጎ አድራጊ። 2. (ኢ.ኦ.ተ.ቤ) በስርአተ ቅዳሴ ጊዜ ቅዳሴን በመሪነት የሚቀድስ ዋናው መሪ ቄስ ወይም ዲያቆን።

**ግብር** ስ ስራ፥ አመል ጠባይ።

**ግብረሃዋርያ** ስ የክርስቶስ ሃዋርያት የሰሩትንና ያስተማሩትን ትምህርት የሚገልፅ የሃዲስ ኪዳን መፅሃፍ ክፍል፤ የሃዋርያት ስራ።

**ግብረሰዶም** ስ በወንድና በወንድ መካከል የሚደረግ የግብረስጋ ግንኙነት።

**ግብረስጋ** ስ ፍትወት፤ ሩካቤ ስጋ፤ ወሲብ።

**ግብረአበር** ስ በተንኮል ወይም በመጥፎ ስራ ተባባሪ ወይም አባሪ የሆነ፤ ሴረኛ።

**ግብረገብ** ስ 1. የጥሩ ወይም የመልካም ስራ ትምህርት። 2. መልካም ምግባር።

**ተገብሮ [ግስ]** ስ (ሰዋ.) ቀጥተኛ ተሳቢ የማያስፈልገው የግስ አይነት ወይም ተደራጊ ግስ። *ያእቆብ ሳረፀ።*

**ተግባር** ስ ስራ፥ ድርጊት።

**ተግባረ ስጋ** ስ እንደ እርሻ፥ ንግድ የመሳሰለና በዚህ አለም ላይ ለመኖር የሚያስፈልግ ስጋዊ ስራ።

**ተግባረ ነፍስ** ስ እንደ ፆምና ፀሎት ያለና ለመንፈሳዊ ህይወት የሚያስፈልግ መንፈሳዊ ስራ።

**ተግባረ እድ** ስ እንደ አናጢነት፥ ሜካኒክነት፥...ያለ የእጅ ሙያ።

*ገበረ[2]

**ገበሬ** ስ በእርሻ ስራ የሚተዳደር ሰው፤ አርሶ አደር፤ አርሶ በላ፤ አራሽ።

**ገበሬ መጣኝ** ቅ እንደ ገበሬው ጉብዝና ወይም ስንፍና በደንብ ወይም እየለገመ የሚያርስ በሬ፤ አባያ በሬ።

**ገበሬ ማህበር** ስ ብዙ ገበሬዎች በህብረት ሰርተው ለመጠቀም የሚያቋቁሙት ማህበር።

**ግብርና** ስ የእርሻና የከብት እርባታ ስራ።

**ገበር** ስ እንደ ኮት፥ቀሚስ፥ ጃኬት፥... ባሉ ልብሶች ላይ በውስጥ በኩል የሚሰፋ፥ ብዙውን ጊዜ ለስላሳና ስስ የሆነ ጨርቅ።

**ገበር ምጣድ** ስ እንደ ምጣድ ጠፍጣፋ ሆኖ ዞሪያውን ጠርዙ እንደ ጎድጓዳ ሳህን ከፍ ያለና ከሸክላ የሚሰራ የዳቦ መጋገሪያ።

**ገበርባሬ** ስ ሰፋፊ በሆነ ጥቁር፥ ቀይና ቢጫ ጥለት ይሰራ የነበረ የሃር ልብስ።

**ገበር እንቧይ** ስ ነጣ ያለ ሰፋፊ ቅጠል ያለው ቅጠሉም ግንዱም እሾሃማ የሆነ ፍሬው ሲበስል ሎሚ የሚመስልና በአንዳንድ አካባቢዎች

እንደሳሙና ለልብስ ማጠቢያነት የሚያገለግል አነስተኛ የእፅዋት አይነት፤ ፍሬውም ገበር እንቧይ ይባላል::

**ገበርዲን** ስ ለኮትና ለሱሪ የሚሆን የሱፍ ጨርቅ አይነት::

***ገበሰበሰ**

**ግብስብስ** ስ 1. ጥራጊ+ ቆሻሻ:: 2. ቅ (ዘይ.) ከጥራቱ ይልቅ ብዛቱ ያመዘነ::

**ተግበሰበሰ** ግ 1. የሚፈለገውም የማይፈለገውም በብዛት ተሰበሰበ+ ተከማቸ:: 2. ረጅም ልብስ ለብሶ ተንጋፈፈ+ ተንተተ+ ተንዘረፈፈ::

**አግበሰበሰ** ግ 1. በብዛት ሰበሰበ+ ወሰደ:: 2. ያገኘውን ሁሉ ሳይመርጥ በላ:: 3. ጥራቱን ሳይጠብቅ ያገኘውን ሁሉ ሰበሰበ+ አከማቸ:: 4. ቃተተ+ አንዘረፈፈ (ልብስን)::

**ገበታ** ስ 1. ከመቃ ወይም ከቀርከሃ ባለእግር ሆኖ የሚሰራና እንደ መሶብ ያለ እቃ:: 2. ማእድ፤ ምግብ የቀረበበት እቃ:: 3. ከእንጨት ተጠርቦ የሚሰራ በመፅሃፍ ጥራዝ ገራና ቀኝ ላይ የሚገኝ የመፅሃፍ አቃፊ:: 4. ዋልታ:: 5. ገበቴ:: 6. አስራ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሚሆኑ ትናንሽ ክብ ጉድጓዶች ያሉት ከእንጨት የሚሰራ የገበጣ መጫወቻ::

**ገበታ(ማእድ)** **ዘረጋ** ምግብ አቀረበ::

**ገበታ ጣለ** ዝ.ክ.

**ገበታው ደነገጠ** የቀረበው ምግብ በሙሉ ተሟጥጦ ተበላ+ ምንም ሳይተርፍ ቀረ::

**ገበታ አስደንጋጭ** (ስድብ) የሚቀርብለትን በሙሉ ምንም ሳያስቀር የሚበላ::

**የገበታ መዝገበ ቃላት** ስ በቀላሉ ከአንድ ቦታ ወደሌላ ቦታ ለማዘዋወር የማይቻል በመሆኑ አንድ ቦታ ተቀምጦ ለማመሳከሪያነት የሚያገለግልና ሰፋ ያሉ መረጃዎችን የያዘ ትልቅ መዝገበ ቃላት::

**ገበታ ሃዋርያ** ስ 1. "ግብረ ሃወርያ"ን ተመ.:: 2. (ቤ.ክህ.) ልጆች ፊደል ተምረው ከጨረሱ በሂላ የሚማሩት የዮሃንስ መልእክት::

**ገበታ ራስ** ስ (ስድብ) ራሱ ትልቅና ጠፍጣፋ የሆነ (ሰው)::

**ገበቴ** ስ ከእንጨት የሚሰራ ሰፊና ጎድጓዳ የሆነ የቤት እቃ፤ ቆሬ::

***ገበዘ**

**ግብዝ** ቅ 1. ያልሆነውን እንደሆነ+ የማይችለውን እንደሚችል ወይም ያላደረገውን እንዳደረገ አድርጎ የሚያስብና ያላግባብ ለራሱ ከፍተኛ ግምት የሚሰጥ (ሰው):: 2. ጥንካሬ የሌለው መናኛ ስራ::

**ተገበዘ** ግ ግብዝ ሆነ::

**ገበዝ (ቄስ ገበዝ)** ስ ( ኢ . ኦ. ተ. ቤ.) በቤተክርስቲያን ቅፅረ ግቢ ውስጥ ያለውን የቤተ ክርስቲያን ንብረት የመጠበቅና የመንከባከብ ሃላፊነት የተሰጠው ካህን::

**ግብዝና** ስ የገበዝነት ስራ::

**ገበየ** ግ ገዛ+ ሸመተ::

**ገበያ** ስ 1. የንግድ ልውውጥ የሚካሄድበት ቦታ:: 2. (ዘይ.) ሰው የበዛበት+ ጫጫታና ሁካታ የሞላበት ስፍራ:: 3. ቶሎ የመሸጥ+ የመግዛት ሁኔታ+ ተፈላጊነት:: *ዝሆ ለለው/ዝዖው ሞቷል::*

**ለገበያ ቀረበ** ለሽያጭ ቀረበ::

**[ከ] ገበያ ላይ ዋለ** ዝ.ክ.

**ገበያ ቆመ** መሸጥና መለወጥ ተጀመረ (በገበያ ቦታ) ::

**ገበያ አወጣ** በጥሩ ዋጋ ተሸጠ::

**ገበያ ያውቃል** ጥሩ እቃ መርጦ መግዛት ወይም በደህና ዋጋ መግዛትና መሸጥ ያውቃል::

**ገበያው ተፈታ** ገበያው ተበተነ ወይም አበቃ::

**ገበያው አበደ** በገበያ ላይ ለሽያጭ የቀረበው እቃ ተወደደ::

**ገበያው ጠገበ** ገበያው ላይ የሚሸጠውና የሚለወጠው ነገር ተትረፈረፈ::

**ገበያተኛ** ስ ገበያ ተገኝቶ የሚሸጥ ወይም የሚገዛ ሰው::

**ግብይት** ስ የመሸጥና የመግዛት ተግባር::

**ተገበያየ** ግ የመሸጥና የመግዛት ተግባር አከናወነ+ ተሻሻጠ+ ተገዛዛ::

**ገበደ** ግ ግንድን ወይም እንጨትን በወፍራሙ ፈለጠ::

**ግብዳ** ቅ 1. በወፍራሙ የተፈለጠ (እንጨት):: 2. (ዘይ.) በጣም ትልቅ+ ግዙፍ::

***ገበደደ**

**ተገባደደ** ግ ሊያልቅ ተቃረበ+ጥቂት ቀረ::

**አገባደደ** ግ ሊጨርስ ተቃረበ+ ጥቂት ቀረው::

***ገበገበ**

**ገብጋባ** ቅ (ስድብ) ንፉግ+ ስስታም::

**ግብግብ አለ** ግ ተንገበገበ::


**ተንገበገበ** ግ 1. ተንሰፈሰፈ+ ተስገበገበ:: 2. ንፉግ+ ስስታም ሆነ:: 3. ከፍተኛ የሆነ ስሜት ተሰማው (የሃዘን+ የቁጭት+ የንዴት+ የፍቅር+ ...):: 4. በጣም ተቃጠለ+ ተለበለበ (ለምሳሌ በሀሙም) ::

**አንገበገበ** ግ 1. አንሰፈሰፈ+ አስገበገበ:: 2. ንፉግ+ ስስታም አደረገ:: 3. አበገነ+ አቃጠለ (ነገር+ ሃዘን+ ፍቅር+...):: 4. በጣም አቃጠለ+

ለበለበ።

**አንገብጋቢ** ቅ አስቸኳይ፥ አጣዳፊ፤ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ።

**ገበጣ** ስ 1. ዝርግ ሆኖ የጠጠር ማስቀመጫ የሚሆኑ አስራ ሁለት ትናንሽና ክብ ጉድጓዶች ያሉት፥ ከእንጨት ወይም ከድንጋይ፥... የሚሰራ መጫወቻ፤ ገበታም ይባላል።



ገበጣ 1ኛ ፍቺ

2. በገበጣ መጫወቻ ላይ ባሉ 12 ጉድጓዶች ውስጥ በሚጨመሩ 48 ጠጠሮች አማካኝነት የሚካሄድ ጨዋታ።

**ገቢር** "*ገበረ[1]" ስር ተመ.

**ገባ** ግ 1. ወደ ውስጥ ጠለቀ፥ ሰጠመ፥ ዘለቀ። 2. አንድ ላይ ሆነ፥ ተባበረ፤ አባል ወይም ተሳታፊ ሆነ፥ በአንድ ስራ ወይም ድርጊት ላይ ተሰማራ። *እድር ገባ /ትምህርት ቤት ገባ / ዘበኝነት ገባ።* 3. ተጨመረ፥ ተቀላቀለ። *ወጡ ጨው ገብቶበታል።* 4. ጀመረ (ክረምት፥ ዘመን፥...)። 5. ተቀጠረ፥ ጀመረ። *ስራ ገባ።* 6. መጣ ወይም ሄደ፥ ደረሰ ። *ሳሚ ለ ሳቦ በሳሰት ሰሳት ገባ።* 7. ተቀጠለ፥ መስመር ተዘረጋ። *መብራት ገባ።*

**ገባው** አወቀ፥ ተረዳ።

**ያገባኛል** (ጉዳዩ) ይመለከተኛል።

**ግቢ ነፍስ ውጪ ነፍስ** ስቃይ፥ ጣር፥ ጭንቅ።

**ግባ በገመዴ** እኔ በሰራሁት ጥፋት አንተ ተቀጣ፤ ተጠየቅ።

**መግቢያ** ስ 1. ወደ ውስጥ የሚታለፍበት በር። 2. መጠጊያ፥ መጠለያ፥ መሄጃ። *እሁቴ ከምታች ሌላ መግቢያ የለኝም።* 3. የሚደረገውን ነገር ለማየት ወይም በሚከናወነው ድርጊት ላይ ተሳታፊ ለመሆን የሚያስችል (ትኬት፥ ካርድ፥...)። 4. አንድ በስፋት ወይም በዝርዝር ሊቀርብ ለታሰበ ነገር (መፅሃፍ፥ ንግግር) እንደ ማስተዋወቂያ ወይም መንደርደሪያ ነጥብ ሆኖ የሚቀርብ ፅሁፍ፥ ንግግር፥...። 5. መጀመሪያ። *ክረምቱ መግቢያ ላይ ይመጣል።*

**መግቢያ ዋጋ** ስ ትያትር፥ ሲኒማ፥ ስፖርት፥... ለማየት የሚከፈል ገንዘብ።

**ይግባኝ** ስ (ህግ) በተሰጠ ውሳኔ (ፍርድ) ቅር የተሰኘ ወገን ጉዳዩ በበላይ አካል እንደገና እንዲታይ የሚያቀርበው አቤቱታ፥ ጥያቄ ።

**ይግባኝ ሰሚ** (ህግ) የይግባኝ ጥያቄን የማየት ስልጣን ያለው የበላይ አካል።

**ገቢ** ስ 1. ለኑሮ ወይም ለመተዳደሪያ የሚሆን ገንዘብ። 2. በእለት፥ በወር፥... ከሽያጭ ወይም ከሌላ የገቢ ምንጭ የሚገኝ ገንዘብ።

**የገቢ ምንጭ** ስ ለኑሮ ለመተዳደሪያ፥... የሚሆን ገንዘብ የሚገኝበት መንገድ፥ ዘዴ፥ ስራ።

**ጋብቻ** ስ 1. አንድ ወንድና አንዲት ሴት በትዳር (ባልና ሚስት ሆነው) ለመኖር እንዲችሉ የሚፈፅሙት ስነስርአት፥ ቃል ኪዳን። 2. ትዳር። አንድ ወንድና ሴት ህጋዊ በሆነ መንገድ አብረው ለመኖር የሚያስችላቸው የኑሮ ትስስር፤ ትዳር።

**የጋብቻ ቀለበት** ስ ባልና ሚስት በተጋቡ እለት ወይም እጮኛሞች በተጫጩ እለት አንዳቸው ላንዳቸው የሚያደርጉት የቃል ኪዳን ምልክት የሆነ ቀለበት።

**ግቢ** ስ 1. ጋብቻ። 2. መኖሪያ ቤት፥ መስሪያ ቤት፥... ያለበትና ዙሪያውን በአጥር የተከለለ ቦታ። 3. እንደ ቤተ መንግስት፥ ዩኒቨርሲቲ ያለ ቦታ።

**ግባተ መሬት (ግብአተ መሬት)** ስ 1. ሬሳ ወደ መቃብር ሲወርድ ወይም ሲገባ የሚደረገው ስነስርአት፥ ፀሎት። 2 (ዘይ.) የአንድ ነገር ማብቂያ ወይም ፍፃሜ ።

**ግብ** ስ 1. በእግር ኳስ፥ በእጅ ኳስ፥ በገና ጨዋታ፥... ላይ ኳሷ ወይም እሩሯ በአጥቂው ቡድን ተመትታ ወይም ተወርውራ የምታርፍበትና ነጥብ የምታስቆጥርበት ቦታ፤ ጎል። 2. በእግር ኳስ፥ በእጅ ኳስ፥ በገና ጨዋታ፥... ላይ ኳሷ ወይም እሩሯ በአጥቂው ቡድን ተመትታ ጎል ውስጥ መግባት። 3. አላማ።

**ግቡን መታ** የታቀደው ወይም የታለመው ተፈፀመ፥ ተሳካ ወይም ያቀደውን ወይም ያለመውን ፈፀመ፥ አሳካ።

**ግብ አስቆጠረ** ጎል ወይም ግብ አገባ።

**ግበቡ(ግቡቡ)** ቅ ተግባቢ፥ ተስማሚ። *ከብዙ ሰው ጋር ግቡቡ ነው።*

**በሚገባ** በደንብ፥ በትክክል።

**በተገባ** ግ ተገቢ በሆነ። *ጉዳዩን ሳስቀድመህ ልትነግረኝ በተገባ ነበር።*

**አይገባም** አያስፈልግም፥ መሆን የለበትም።

**የሚገባ** አስፈላጊ፥ ትክክል።

**የተገባ** ዝ.ከ.

**ተገቢ** ቅ መሆን ያለበት፥ የሚገባ፥ ትክክል።

**ተጋባ** ግ 1. በአንድ እቃ ውስጥ የነበረው ነገር ወደ ሌላ ቦታ ወይም እቃ ተዛወረ፥ ተገለበጠ። 2. ባዶ ሆነ (ውስጡ የነበረው ነገር ወደ ሌላ እቃ ስለተዛወረ ወይም ስለተገለበጠ)። 3. ተላለፈ፥ ተዛመተ (ለምሳሌ በሽታ)። 4. ጋብቻ ፈፀመ። 5. በጋብቻ ዝምድና ተሳሰረ፥ ተዛመደ።

**ተጋቦ** ስ የበሽታ ከአንዱ ወደ ሌላው ሰው መተላለፍ።

**ተግባባ** ግ ተስማማ፤ ተወዳጀ፥ ተለማመደ።

**ተግባቢ** ቅ ከሰው ጋር ቶሎ የሚወዳጅ፥ የሚግባባ።

**አገባ** ግ 1. ውጭ የነበረውን ወደ ውስጥ አደረገ፥ ከተተ፥ ጨመረ። 2. ትዳር ያዘ፥ ጋብቻ ፈፀመ።

**ኢያገባህም** ጉዳዩ ኢይመለከትህም፣ ሊያሳስብህ ወይም ልትሳተፍበት ኢያስፈልግም።

**ኢጋባ** ግ 1. ጋብቻ እንዲፈፅም ኣደረገ። 2. ኣስተላለፈ፣ ኣዛመተ (ለምሳሌ በሽታን)። 3. ኣንድን ነገር ከኣንድ እቃ ወደ ሌላ በመገልበጥ ወይም በማዛወር እቃውን ባዶ ኣደረገ ወይም ወደ ሌላ እቃ ገለበጠ፣ ኣዛወረ።

**ኣግባባ** ግ 1. ኣወዳጀ፣ እንዲቀራረብ ምክንያት ሆነ። 2. ኣባበለ፣ ገፋፋ። *ኣብሬው እንድሄድ ኣግባባኝ።*

**ኣግባብ** ስ 1. እውቂያ፣ ወዳጅነት። 2. ስነስርኣትን ወይም ደንብን የተከተለ ወይም ተገቢ የሆነ። *ኣግባብ ባለው መንገድ ኣልተሰራም።* 3. ግንኙነት። *ከጉዳዩ ጋር ኣግባብ ያለው መስሪያ ቤት።*

**ገባሬ ሰናይ** “*ገበረ[1]” ስር ተመ.

**ገባር** “ገበረ[1]” ስር ተመ.

**ገብረ ጉንዳን** ስ ጉንዳን።

**ገብስ** ስ ለእንጀራ፣ ለጠላ፣...የሚሆን የብርእ እህል።

**ገብስ ነው** ገራገር ነው፤ ክፋት የለውም፤ ቀላል ነው።

**ገብስማ** ቅ ኣልፎ ኣልፎ የነጭ ሰብጥር ያለበት ጥቁር ቀለም፣ የመልክ ኣይነት(ብዙውን ጊዜ ለጾር)።

**ገብጋባ** “ገበገበ” ስር ተመ.

**የገቦ ነገር** ኣድራጊው ወይም ኣስደራጊው የማይታወቅ።

**የገቦ [እህል]** ስ ሰብል በሚሰበሰብበት ጊዜ ማሳው ላይ ረግፎ የሚቀረውና እንደገና እዚያው ማሳ ላይ በቅሎ የሚገኝ እህል።

***ገተለተለ**

**ግትልትል** ስ የተያያዘ፣ ቅጥልጥል፣ ቁጥርጥር፣ ዝባዝንኪ ነገር።

**ግትልትላም** ቅ (ስድብ) ኮተታም፣ ዝግንትላም።

**ግትልትል ኣለ** ግ ተግተለተለ።

**ግትልትል ኣደረገ** ግ ኣግተለተለ።

**ተግተለተለ** ግ በብዛት ሆኖ ኣንዱ ኣንዱን እየተከተለ ተጓዘ፣ ተንጋጋ።

**ኣግተለተለ** ግ በብዛት ሰበሰቦ ኣመጣ ወይም ወሰደ፤ ኣንጋጋ።

**ገተመ** ግ እያፈሰ ቃመ ( ቆሎን፣ ንፍሮን፣..) ።

**ገተረ** ግ 1. ወጠረ፣ ለጠጠ። 2. (ነውር) ኣቆመ፣ ቀሰረ (የወንድን ብልት)። 3. ያዘ፣ ኣስጨነቀ (በነገር፣...)። 4. ለረጅም ጊዜ ኣቁሞ ኣቆየ። *እመጣለሁ ብሎ ገትሮኝ ቀረ።* 5. ተቋቋመ፣ ኣልሸነፍ ኣለ። 6. ወደ መሬት ያለው ቀጥታነት የበዛ ሆነ፣ ጋደም ሳይል ቀረ (ከሞፈር ጋር ለተዋደደ ማረሻ፣ ለዶማ፣...)።

**መገተሪያ** ስ በውስጡ ቀጫጭን ሽቦዎች የተሰፉበት ወይም በሌላ ዘዴ ደርቆ እንዲል ተደርጎ የተሰራና የሙሽራ ልብስ ወይም ሌላ የሴት ቀሚስ ቡፍ ብሎ እንዲታይ የሚያደርግ ገበር፤ ቡፋንቲ።

**ገታራ** ቅ ግትር።

**ግትር** ቅ 1. ያልሰላ፣ በትክክል ያልተገጠመ፣ ወደ ውስጥ የሚወጋ (ማረሻ፣ እርፍ፣...)። 2. ሃሳቡን በቀላሉ የማይለውጥ ወይም የሌላውን ሃሳብ በቀላሉ የማይቀበል (ሰው)።

**ተገተረ** ግ 1. ቀጥ ብሎ ቆመ። 2. ሳያልቅ ቀረ (የቤት፣ የኣጥር፣...ስራ)።

**ተገትራ ቀረች** ሳታገባ ጊዜዋ ኣለፈባት።

**ተጋተረ** ግ ተያያዘ፣ ተጋፈጠ። *ስራውን ተጋትሮታል።*

**ተግተረተረ** ግ 1. ተውተረተረ፣ ተንገዳገደ። 2. ቆመ፣ ተገተረ (የደም ስር)።

**ኣግተረተረ** ግ 1. ኣውተረተረ፣ኣንገዳገደ። 2. ኣቆመ፣ ገተረ(የደም ስርን)።

**ገተተ** ግ 1. ተቦጫጨቀ፣ ተበጣጠሰ (በእርጅና ምክንያት)። 2. ጎተተ።

**ገታታ** ቅ 1. (ስድብ) ከርፋፋ፣ ቂል፣ሞኝ። 2.ጎታታ።

**ግተት** ስ 1. ያረጀ ወይም ያለቀ የስፌት እቃ፤ ግትቻ። 2. (ስድብ) ጎታታ፣ ከርፋፋ፣ ሞኝ።

**ግትት** ዝ.ከ.

**ግትቻ** ስ 1. ያረጀ ወይም ያለቀ የስፌት እቃ። 2. (ስድብ) ሀ. የሸመገለ፣ ያረጀ (ሰው)። ለ.ቀርፋፋ፣ ገልጃጃ።

**ተንጋተተ** ግ ተንከረፈፈ።

**ኣንጋተተ** ግ ኣንከረፈፈ።

**ገተገተ** ግ 1. ቆረጠመ፣ኣኘከ (ህመም ሰውነትን)። 2. መጠመጠ፣ መገመገ፣ ጠባ (ጡትን)።

***ገተገተ**

**ገትጋታ(ገተገት)** ቅ 1.የያዘውን (ነገር፣ሃሳብ፣ እምነት፣...)የማይለቅ፣ነዝናዛ፣መንቻካ። 2.ቀብቃባ።

**ተንገታገተ** ግ 1.የያዘውን (ነገር ሃሳብ፣ እምነት፣...) ላለመልቀቅ ባለው ኣቅም ተፍጨረጨረ፣ ተጣጣረ። 2.ተንቀበቀበ።

· **ገታ** ግ 1. ኣቆመ፣ ኣገደ፣ ከለከለ፣ እንዳይቀጥል ኣደረገ። 2. ተወ፣ ኣቋረጠ።

**ግት** ስ የተገታ፣ የታደገ፣ እግድ።

**ተገታ** ግ 1. ታገደ፣ ተከለከለ፣ እንዳይቀጥል

ተደረገ፣ ቆመ። 2. ተቆጠበ፣ ተወ።
**ገታራ** "ገተረ" ስር ተመ.
**ገታታ** "ገተተ" ስር ተመ.
**ገትጋታ** "*ገተገተ" ስር ተመ.
***ገቸገቸ**
**ገችጋቻ** ቅ የማይስግር ወይም መጋገ የሆነ (በቅሎ፣ ፈረስ)።
**ተንገቸገቸ** ግ ዘከዘከ ወይም ዘጥ ዘጥ አለ።
**አንገቸገቸ** ግ አንገጫገጨ፣ ነቀነቀ።
**ገች** ስ 1. ጠላ የሚሞላበት ወይም የሚሾምበት ትልቅ ጋን። 2. ትልቅ ድልብ ስንጋ፣ ፍሪዳ።
***ገነበጠ**
**ግንብጥ** ስ ገና ያልጠና ወይም ያልዘረዘረና ብቅ ብሎ የሚታየው የበቆሎ ወይም የብርእ እህል ፍሬ።
**አገነበጠ** ግ 1. በጎኑ ላይ ፍሬ ሻጠ፣ አዘለ(የበቆሎ አገዳ)። 2. አገነደረ፣ ወገቡ ላይ ታጠቀ (ለምሳሌ ጎራዴን)።
**ገነባ** ግ 1. አነፀ፣ ግንብ ሰራ። 2. አዳበረ፣ አበለፀገ።
**ገንቢ** ቅ ጠቃሚ፣ ለእድገት የሚረዳ (አስተያየት፣ ሃሳብ፣...) ።
**ገንቢ ምግብ** ቅ ሰውነትን ለመገንባት ወይም ለማደርጀት የሚያገለግል ፕሮቲንነት ያለው የምግብ አይነት።
**ግንብ(ግምብ)** ስ በድንጋይ፣ በኮረት፣ በአሸዋና በሲሚንቶ፣... የታነፀ ወይም የተሰራ (ቤት፣ አጥር፣ ህንፃ፣...)።
**ግንበኛ(ግምበኛ)** ስ የግንብ ስራ ባለሙያ።
**ግንባታ (ግምባታ)** ስ 1. የልማት፣ የእድገት እንቅስቃሴ። *የኢኮኖሚ ግንባታ።* 2. የማነፅ፣ የመገንባት ስራ።
**ተገነባ** ታነፀ፣ ተሰራ።
**ገነተረ** ግ 1. በደንብ ሳይሆን ላይ ላዩን በሰለ (ስጋ) ። 2. አልታኘክ አለ፣ አኞ ሆነ (ስጋ)። 3. (ዘይ.) ሃሳቡን አልቀይር አለ፣ እምቢ አለ።
**ገንታራ** ቅ 1. በሚገባ ያልበሰለ ወይም የገነተረ (ስጋ) ስ 2.(ዘይ.) ሃሳብ ግትር።
**ግንትር** ቅ በሚገባ ያልበሰለ (ስጋ)።
**አገነተረ** ግ 1. በደንብ ሳያበስል ቀቀለ፣አገነፈለ (ስጋን)። 2. ነገር እንዲባባስ ወይም እንዲጠነክር አደረገ።
**ገነት** ስ 1. በአሪት ዘፍጥረት ምእራፍ 3. ላይ እንደተገፈው አዳምና ሄዋን የፈጣሪያቸውን ትእዛዝ ተላልፈው ከመባረራቸው በፊት ይኖሩበት ነበር ተብሎ የሚታመንበትና በተለያዩ ተክሎች የተዋበ አስደሳች ቦታ። 2. እንደ ክርስትና ባሉ ሃይማኖቶች እምነት መሰረት ፃድቃን ወደ መንግስተ ሰማያት ከመግባታቸው በፊት ወይም እስከ እለተ ምፅአት የሚቆዩበት ሰማያዊ ቦታ።3 (ዘይ.) በሁሉም ረገድ በጣም አስደሳች የሆነ ስፍራ፣ አካባቢ፣ ሃገር ።
**የገነት ወፍ** ስ 1. ጅራቷ ረጅም፣ መጠኗ ትንሽና መልኳ ሽልምልም የሆነ፣ በወንዝ አካባቢ የምትገኝ በመስከረምና በጥቅምት ወራት ብቻ የምትታይ ወፍ። 2. "ጣዎስ" ን ተመ.
**ገነታ** ግ በቁጣ ወይም በንዴት አነጋገር ጊዜ ድምፅ የተለመደ ቃናውን ለወጠ፣ ከረረ።
**ገነነ** ግ 1. ከፍ ከፍ አለ፣ በጣም ታወቀ፣ ዝነኛ ወይም ታዋቂ ሆነ። 2. አየለ፣ በረታ (ህመም፣ ነገር፣...)። 3. ጎልቶ ቷወቀ ወይም ተሰማ(ጣእም)። 4. ለመለመ፣ አደገ (ተክል)።
**ገናና** ቅ ዝነኛ፣ ታዋቂ፣ ስመጥር።
**ግነት** ስ በልዩ ልዩ የፈጠራ ስራዎች (በስነፅሁፍ፣ በኪነጥበብ፣...) ውስጥ ደራሲው ሊያስተላልፍ የፈለገውን ሃሳብ ተደራሲው በደንብ እንዲረዳው ወይም እንዲሰማው ለማድረግ ሲባል አንድን ድርጊት ወይም ሃሳብ አጋኖ የማቅረብ ቴክኒክ ወይም ዘዴ ።
**ተጋነነ** ግ አንድ ነገር ከሚገባው ወይም ከሆነው በላይ (የተሻለ ወይም መጥፎ፣ ትልቅ ወይም ትንሽ፣...) እንደሆነ ተደርጎ ቀረበ።
**አገነነ** ግ 1. በጣም ትልቅ፣ ዋና፣... አድርጎ አቀረበ(ሰውን)። 2. ጎልቶ እንዲታወቅ ወይም እንዲሰማ አደረገ(ጣእምን)።
**አጋነነ** ግ አንድን ነገር ከሚገባው ወይም ከሆነው በላይ የተሻለ ወይም መጥፎ፣ ትልቅ ወይም ትንሽ፣... እንደሆነ አድርጎ አቀረበ።
***ገኘ**
**ግንኙነት** ስ 1. ተመሳሳይነት። 2.ዝምድና፣ ቀረቤታ። 3. የተለያዩ ወገኖች ለተለያዩ አላማዎች (አብሮ ለመስራት፣ በአንድ የተወሰነ ጉዳይ ላይ ሃሳብ ለመለዋወጥ፣ ንግድ ለማካሄድ፣...) ሲሉ በመካከላቸው የሚፈጥሩት ቀረቤታ። 4. ወሲብ ወይም የግብረ ስጋ ድርጊት።
**ግኝት** ስ ስለአንድ ነገር ተፈጥሮ፣ ምንነት፣ አሰራር፣ ጥቅም፣... ምርምር ወይም ጥናት በማድረግ የታወቀ አዲስ መረጃ ወይም የተደረሰበት አዲስ ውጤት።
**ተገኘ** ግ 1. ጠፍቶ፣ ተደብቆ፣ ተረስቶ፣...የነበረው ወይም የሚፈለገው ነገር ወጣ፣ ተከሰተ፣ ተያዘ፣ በእጅ ተደረገ። 2. በአንድ የተወሰነ ቦታ፣ ድርጊት፣... ላይ ተሳታፊ ሆነ። *ስብሰባው ላይ ብዙ ሰው ተገኘ።*
**የማይገኝ** በጣም ጥሩ፣ ጥራት ያለው፣ ምርጥ፣ እንደልብ የሌለ። *የገዛሁልኝ ሱሪ የማይገኝ ነው።*

**የተገኘውን** ማንኛውንም÷ የሆነውን:: *የተገኘውን ልብስ ሰጠኝ::*

**ተገናኘ** ግ 1. አብሮ ለመስራት ወይም በአንድ የተወሰነ ጉዳይ ላይ ሃሳብ ለመለዋወጥ÷... ሲል ከሌላ ወገን ጋር አንድ ቦታ ላይ ተሰባሰበ:: 2. በአካል ተቀራረቦ ተያየ÷ ተነጋገረ ወይም ተገጣጠመ:: *ከስራ ባልደረባዬ ጋር ተገናኘ::* 3. ተያያዘ:: 4. ወሲብ ወይም ሩካቤ ስጋ ፈፀመ::

**መገናኛ** ስ 1. በተለያዩ ወይም በተራራቁ ቦታዎች ላይ የሚገኙ ክፍሎችን ለማገናኘት የሚረዳ እንደ አይሮፕላን÷ መኪና÷ ሬድዮ÷ ስልክ÷ ፋክስ÷... ያለ መሳሪያ:: 2. አንዱን ቦታ ከሌላው የሚያገናኝ መንገድ÷ መስመር:: 3. ከተለያየ አቅጣጫ የሚመጡ መንገዶች የሚገጣጠሙበት ቦታ ወይም ስፍራ:: ቅ 4. ግንኙነት ለማድረጊያ ወይም ለመሰባሰቢያ የሚሆን (ቦታ÷ ጊዜ÷ ምክንያት÷...)::

**መገናኛ ብዙሃን** ስ የተለያዩ መረጃዎችን÷ ዜናዎችን÷...በአንድ ጊዜ ለብዙ ሰው ለማሰራጨት የሚያገለግሉ እንደ ጋዜጣ÷ ሬድዮ÷ ቴሌቪዥን ያሉ የማሰራጫ አውታሮች ÷ መሳሪያዎች::

**አገኘ** ግ 1. ጠፍቶ÷ ተደብቆ÷ ተረስቶ÷... የነበረን ነገር በእጁ አደረገ÷ ያዘ አስገባ÷ ጨበጠ:: 2. የ__ባለቤት ሆነ:: *ሃብት አገኘ::* 3. አንድ የተወሰነ ቦታ ላይ ተገጣጠመ÷ ተያየ÷...:: *ትላንት ሲኒማ ቤት አገኘሁት::* 4. አወቀ÷ ደረሰበት:: *የጠፋን መንገድ አገኘው::* 5. አጋጠመ:: *ችግር አገኘው::*

**አገናኘ** ግ 1. ግንኙነት እንዲኖራቸው አደረገ(ለስራ÷ አንድ የተወሰነ ጉዳይ ላይ ለመነጋገር ወይም ለሌላ አላማ):: 2. ተለያይቶ ወይም ተራርቆ የነበረው እንዲቀራረብ አደረገ:: 3. ተለያይቶ የነበረውን አያያዘ÷ አጣበቀ (ለምሳሌ የኤሌክትሪክ ሽቦን)::

**አስገኘ** ግ 1. በፊት የሌለ ወይም ያልነበረ ነገር እንዲኖር አደረገ:: 2 እንዲገኝ አደረገ::

**ገነዘ** ግ ከፈነ::

**መግነዝ** ስ ከፈን::

**ግንዘት** ስ (ኢ.ኦ.ተ.ቤ .) ለሞተ ሰው ፍትሃት ወይም ፀሎት የሚደረግበት የፀሎት መፅሃፍ::

**ግንዝ** ቅ የተገነዘ (ሬሳ)::

***ገነዘበ**

**ግንዛቤ** ስ 1. ልብ ማድረግ÷ መረዳት:: 2. እውቀት:: *ከሴሚናሩ ጥሩ ግንዛቤ ይገኛል::*

**ተገነዘበ** ግ ልብ አደረገ÷ አስተዋለ÷ ተረዳ÷ አወቀ::

**ተገናዘበ** ግ ተነፃፀረ÷ ተመሳከረ::

**አገናዘበ** ግ 1.አስተዋለ::2.አነፃፀረ÷ አመሳከረ::

**አገናዛቢ አፀፋ** ስ (ሰዋ.) ባለቤትነትን የሚያመለክት ተውላጠስም (ምሳሌ÷ ቤት ___ ቤትህ /አባት ___ አባቷ::

**አስገነዘበ** ግ 1. አሳወቀ÷ አስረዳ:: 2. አስታወቀ÷ አሳሰበ::

**ማስገንዘቢያ** ስ 1.ማሳሰቢያ::2.ማስገንዘቢያ::

***ገነደረ**

**አገነደረ** ግ ታጠቀ÷ አገነበጠ (ለምሳሌ ጎራዴን)::

**አጋንዱር** ቅ 1. ወደል÷ ጠብደል:: 2. ዘርጣጣ÷ እንቅብ ሆድ::

**ገነደሰ** ግ 1. ቆርጦ ጣለ÷ ገረሰሰ (ዛፍን):: 2. አጋደመ፥ ደበለለ፥ አስተኛ::

**ገንዳሳ(ግንድስ)** ቅ (ስድብ) መተኛት የሚያበዛ÷ እንቅልፋም::

**ገንደሰ ገንደሰ አለ** ግ ፈንደስ ፈንደስ እያለ ቀስ ብሎ ተራመደ (ወፍራም ሰው)::

**ተገነደሰ** ግ 1.ተቆርጦ ወደቀ÷ ተገረሰሰ (ዛፍ):: 2. ተንደባለለ÷ ወደቀ:: 3. ተጋደመ÷ ተኛ::

**ገነገነ** ግ ጠረጠረ፣ ሰጋ::

**ገንጋና** ቅ ጠርጣሪ::

**ገንጋኝ** ዝ.ከ.

**ግንገና** ስ ጥርጣሬ÷ ፍርሃት፣ ስጋት::

**አገነገነ** ግ ገነገነ::

**ገነጠለ** ግ 1. ዘነጠለ÷ ዘነጠፈ÷ ለየ (ለምሳሌ የዛፍ ቅርንጫፍን):: 2. ተያይዘው ወይም ተጣብቀው የነበሩትን ለያየ÷ ነጠለ÷ ቀደደ (÷ ገፅን የመፅሃፍ ሽፋንን÷...ከጥራዙ ላይ):: 3 አንድ የነበረውን ለያየ÷ ከፋፈለ (ለምሳሌ ሃገርን)::

**ገንጣይ** ቅ 1. ተገንጣይ:: 2. የሃገርን የተወሰነ ክፍል ለመገንጠል ወይም ለመለየት የሚታገል ወይም ይህ አላማ ያለው (ድርጅት÷ቡድን÷...)::

**ግንጣይ** ቅ ከዋናው ዛፍ ወይም ከግንዱ የተቆረጠ÷የተለየ÷...ቅርንጫፍ::

**ግንጥል** ቅ ከመሰሉ÷ ከወገኑ የተለየ ወይም የተገነጠለ::

**ግንጥል ጌጥ** ስ አብሮት ካለው ጋር የማይስማማ ወይም ያልተሟላ ጌጥ::

**ተገነጠለ** ግ 1. ተዘነጠለ÷ ተዘነጠፈ÷ ተለያየ (ለምሳሌ የዛፍ ቅርንጫፍ):: 2. ተለያየ÷ ተላቀቀ÷ ተቀደደ (ገፅ÷ የመፅሃፍ ሽፋን÷...):: 3.ተለየ ብቻውን ሆነ ወይም ብቻውን መተዳደር ጀመረ:: 4. ተለያየ (መንገድ)::

**ተገንጣይ** ቅ ከአንድ አገር ውስጥ የተወሰነውን ክፍል ወይም አካባቢ ነጥሎ ወይም ለይቶ ለብቻ የማድረግና ሌላ መንግስት የመመስረት አላማ ያለው ድርጅት ወይም ቡድን::

**ገነፈለ** ግ 1. ፈልቶ ፈሰሰ። 2. *ታምቆ፣ ታግዶ* የነበረው ፈንቅሎ ወጣ (እንባ፣እምባ፣...)። 3.(ዘይ.)ተቆጣ፣ ቱግ አለ።

**ተገነፈለ** ግ በደንብ ሳይበስል በውሃ ብቻ ተቀቀለ (ለምሳሌ ስጋ፣ የራስ ባቄላ) ።

**አገነፈለ** ግ በደንብ ሳያበስል በውሃ ብቻ ቀቀለ።

***ገነፋ**

**ገንፎ** ስ የገብስ ወይም የስንዴ፣... ዱቄት የፈላ ውሃ ውስጥ ተወምሮ በማማሰያ በወፍራሙ እየታሸ ከበሰለ ቢሃላ በቅቤ፣ በዘይት፣ በብጥብጥ ተልባ፣... የሚበላ ምግብ።

**ተገነፋ** ግ 1. ገንፎ ተሰራ። 2. እንደ ገንፎ ሆኖ ተሰራ።

**አገነፋ** ግ 1.ገንፎ አዘጋጀ። 2. እንደ ገንፎ አድርጎ ሰራ። 3. በማማሰያ አሸ፣ ላገ (ገንፎን)።

**ገና** ተው.ግ ያልተፈፀመን፣ ያልተደረገን፣ ያልደረሰን፣ያልተሟላን፣...ወይምወደፊት የሚፈፀምን፣ የሚደረግን፣ የሚሆንን ነገር፣ ጉዳይ፣...ለማሳየት ወይም ለመግለፅ የሚያገለግል ቃል። *ምሳዬን ገና አልበላሁም /ሁለተኛ ደረጃን ገና አልጨረሰም።*

**ገና ለገና** ምን አልባት፣ ወደፊት።

**ገና** ስ 1. በክርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድ ታህሳስ 29 ወይም በየአራት አመቱ በዘመነ ዮሃንስ ብቻ ታህሳስ 28 ቀን የሚከበር፣ ኢየሱስ ክርስቶስ የተወለደበት ቀን፤ ልደት። 2. የገና ጨዋታ።

**ገና መምቻ** ስ 1. ሩር ወይም ጥንግ የሚመታበት፣ በአንድ በኩል ከጫፉ ቀልበስ ያለ ብትር። 2. የገና መጫወቻ ሜዳ ክልል።

**ገና ተሳዳቢ** ስ የገና እለት የገና ጨዋታ ተሸናፊውን ወገን በሆታና በግጥም የሚሳደብ የአሸናፊው ወገን አቀንቃኝ።

**የገና ጀንበር** ስ ቀኑ አጭር ሌሊቱ ደግሞ ረዥም የሚሆንበት ወቅት።

**የገና ጨዋታ** የገና እለት ወንዶች በሁለት ቡድን ተከፋፍለው ሩርን ወይም ጥንግን በገና መምቻ እየመቱና ግብ አግብተው አሸናፊ ለመሆን የሚወዳደሩበት ጨዋታ።

**ገናና** "ገነነ" ስር ተመ.

**ገንቢ** "ገነባ" ስር ተመ.

**ገንባሌ** "ገምባሌ" ን ተመ.

**ገንቦ (ገምቦ)** ስ ከአንስራ አነስ፣ ከምንቸት ከፍ የሚልና ከሸክላ የሚሰራ የጠላ፣ የጠጅ፣የውሃ፣... መያዣና ማቅረቢያ እቃ (ሸክላ ስር ተመ) ።

**ገንቦሬ** "ጎምቦሬ" ን ተመ.

**ገንታራ** "ገነተረ" ስር ተመ.

**ገንዘብ** ስ 1. በመግዛትና በመሸጥ ሂደት ውስጥ ሻጭና በገዥ መካከል ተቀባይነት ያለው ለመክፈያ የሚያገለግል ነገር፣ አብዛኛውን ጊዜ ከመዳብ ፣ ከብር ወይም ከወርቅ፣... የሚሰራና የተወሰነ ልኩ ላዩ ላይ የታተመበት የሳንቲም ወይም የወረቀት መክፈያ። 2. ንብረት።

**ገንዘቤ ነው** የግሌ፣ ንብረቴ ነው።

**ገንዘብ ቋጠረ** ገንዘብ አጠራቀመ።

**የገንዘብ ቅጣት** ስ የተወሰነ ገንዘብ በማስከፈል የሚፈፀም የቅጣት አይነት።

**ገንዘብ ቤት** ስ 1. በአንድ መስሪያ ቤት ወይም ድርጅት ውስጥ ገንዘብ የሚቀመጥበት ክፍል። 2. ገንዘብ ያዥ።

**ገንዘብ ከፋይ** ስ በአንድ መስሪያ ቤት ወይም ድርጅት ውስጥ ደመወዝ ወይም ሌላ ወጭን የመክፈል ስራ የሚሰራ ሰው።

**ገንዘብ ያዥ** ስ በአንድ መስሪያ ቤት፣ ድርጅት ወይም እንደ እድር፣ ማህበር ባሉ ማህበራዊ አካላት ውስጥ ተቀማጭ ወይም ተንቀሳቃሽ የሆነውን ገንዘብ በሃላፊነት ተረክቦ የሚይዝ ሰው።

**ገንዳ** ስ 1. ወፍራም ግንድን አግድም በመቦርቦር የሚዘጋጅና ለከብቶች ውሃ መጠጫነት የሚያገለግል እቃ። 2. ሰው ውስጡ ገብቶ ሊታጠብበት የሚችል በባኞ ቤት ውስጥ የሚገኝና ከሸክላ ወይም ሲራሚክስ፣... የሚሰራ እቃ።

**ገንዳሳ** "ገነደሰ" ስር ተመ.

**ገንገበት** ቅ 1. (ስድብ) ያልሰለጠነ፣ ከርፋፋ። 2. ገብጋባ፣ስስታም።

**ገንጋና** "ገነገነ" ስር ተመ.

**ገንጋኝ** ዝ.ከ.

**ገንጣይ** "ገነጠለ" ስር ተመ.

**ገንፎ** "*ገነፋ" ስር ተመ.

***ገወለለ**

**ተንገዋለለ (ተንጓለለ)** ግ 1. ቆሻሻው ከደህናው ወይም ደህናው ከቆሻሻው በሰፌድ ወይም በወንፊት፣... አማካይነት ተለየ (ለምሳሌ ቆሻሻ ያለበት እህል)። 2. (ዘይ.) ስራ ፈቶ ዞረ፣ ተንገላወደ።

**አንገዋለለ** ግ 1. ቆሻሻውን ከደህናው ወይም ደህናውን ከቆሻሻው ለመለየት በሰፌድ ወይም በወንፊት ላይ አድርጎ ሰፌዱን ወይም ወንፊቱን ወደፊትና ወደሃላ አንቃነቀ ወይም አዞረ (ብዙውን ጊዜ ለእህል)። 2. አገለለ፣ ለየ። 3(ዘይ.)አዞረ፣ አንከራተተ።

**እንግውላይ** ስ ከተፈለገው እህል ወይም ጥራጥሬ ላይ ተለይቶ የሚቀረውና የማይፈለገው የእህሉ ወይም የጥራጥሬው ክፍል ወይም ቆሻሻ፣

ብጣሪ::

**ገውዝ [ንፋስ]** ስ በግንቦት የሚወጣ የኮከብ ስም:: በተጨማሪ "**ኮከብ ቆጠራ**"ን ተመ.

**ገውጋዋ** ቅ 1. ሞኝ፥ ቂል:: 2. ዘዋሪ፥ ቀውላላ::

**ገዘረ** "**ገረዘ**"ን ተመ

**ገዘተ** ግ አንድ የተወሰነ ድርጊት እንዳይደረግ ከለከለ፥ አወገዘ(የክህነት ስልጣን ያለው ሰው)::

**ግዝት** ስ እንዳይደረግ ካህን የከለከለው ነገር::

**ተገዘተ** ግ 1. አንድን የተወሰነ ድርጊት እንዳያደርግ ተከለከለ፥ ተወገዘ (በካህን):: 2. ማለ::

**ገዘገዘ** ግ 1. ለመቁረጥ ከረከረ:: 2. ቀስ በቀስ አዳከመ፥ አቅም አሳጣ፥ ውስጥ ውስጡን ቦረቦረ:: *የነበረውን መንግስት ተቃዋሚዎቹ ገዝግዘው ጣሉት /በሽታ ገዝግዞ ገደለው::*

**ተገዘገዘ** ግ 1. ተከረከረ:: 2. ተዳከመ፥ አቅም አጣ፥ ተቦረቦረ::

***ገዘገዘ**

**ገዝጋዛ (ገዘገዘ)** ቅ 1. ነገር የማይቆርጥ፥ ጨቅጫቃ፥ ነዝናዛ:: 2. ሲናገር ወይም ሲያነብ ድምፁ የሚንቀጠቀጥ:: 3. አንድን ስራ በቅልጥፍና የማይሰራ፥ ቀርፋፋ::

**ተንገዛገዘ** ግ 1. ተንገዳገደ:: 2.ፊደሎችን እየቆጠረና እየጎተተ አነበበ ወይም ተናገረ::

**አንገዛገዘ** ግ አንገዳገደ::

**ገዘፈ** ግ 1. በጣም ወፈረ፥ ደነደነ:: 2. ረቂቅ የነበረው በአካል ወይም በቅርፅ ጎልቶ ታየ፥ ተከሰተ:: 3. አጓራ (በዛር ምክንያት)::

**ግዙፍ** ቅ በጣም ወፍራም ወይም ትልቅ::

**ግዝፈት** ስ ውፍረት::

**አገዘፈ** ግ ትልቅ፥ ጉልህ ሆኖ እንዲታይ አደረገ::

**ገዛ** ግ 1. ገበየ፥ ሸመተ:: 2. አስተዳደረ፥ መራ (መሪ፥ ባለስልጣን):: 3. አፈራ፥ አበጀ:: *በገንዘቡ ወዳጅ ገዛ::*

**በገዛ እጁ** በሌላ ሳይሆን እራሱ በራሱ:: *በገዛ እጁ ተሰቀለ::*

**የገዛ ራሱ** የራሱ፥ የግሉ::

**መግገዣ** ስ መገብያ ገንዘብ::

**ገዢ** ስ የበላይ አስተዳዳሪ፥ ባለስልጣን(ለምሳሌ አገረ ገዢ፥ የባንክ ገዢ)::

**ግዛት** ስ 1. የተወሰነ የአስተዳደር ክልል:: 2. ክልል::

**ግዢ** ስ የመግዛት ተግባር::

**ተገዛ** ግ 1. ተገበየ፥ ተሸመተ:: 2. ተመራ፥ ተዳደረ::

**አገዛዝ** ስ አስተዳደር::

**ገዝጋዛ** "***ገዘገዘ**" ስር ተመ.

**ገዠሞ** "**ገጀሞ**" ን ተመ.

**ገዢ** "**ገዛ**" ስር ተመ.

***ገየጠ**

**ጌጥ** ስ አንድን ነገር ለማስዋብ የሚያገለግል እንደ ወርቅ፥ ብር፥ አልማዝ፥ ጥልፍ፥... ያለ ነገር::

**ጌጠኛ** ቅ በጌጥ የተዋበ::

**ጌጣጌጥ** ስ ልዩ ልዩ አይነት ጌጥ::

**ተጌጠ** ግ በጌጥ ተዋበ፥አማረ::

**ተጊያጊያጠ** ግ ተሽቀረቀረ፥የተለያዩና የሚያሳምሩ ነገሮችን በመጠቀም ተዋበ::

**አጌጠ** ግ ተሽላለመ፥ አማረ፥ ተዋበ::

**አስጌጠ** ግ በጌጥ እንዲያምር ወይም እንዲዋብ አደረገ::

**ገደቢስ** "**ገድ**" ስር ተመ.

**ገደለ** ግ 1. ህይወት አጠፋ፥ እንዲሞት አደረገ:: 2. እንዳይኖር አደረገ፥ አጠፋ (ስሜትን፥ ሞራልን፥...):: 3. እንዳይከናወን አደረገ:: *ስራውን ገደለው::* 4. ጎዳ፥ አደከመ:: *ፀሃዩ ገደለው::*

**ገዳይ** ቅ የሰው ህይወት ያጠፋ(ሰው):: 2. አዳኝ:: *ገዳዩ ዝሆን ገድሉ ተመለሰ::*

**ግዳይ** ስ በጦርነት የተሳተፈ ሰው ጠላት ለመግደሉና የጀግንነት ስራ ለመፈፀሙ የሚጠቅሰው ማስረጃ፥ የሚያቀርበው ምርኮ ወይም አዳኝ አድኖ የሚያቀርበው አውሬ፥ እንስሳ ወይም ከታደነው እንስሳ ወይም አውሬ አካል ላይ ተወስዶ ለማስረጃነት የሚቀርብ ምልክት::

**ግዳይ ጣለ** በጦርነት የተሳተፈ ሰው ስለፈፀመው ጀብድ ምስክር በመጥቀስ በሽለላና በፉከራ ተናገረ ወይም ምርኮውን አቀረበ ወይም አዳኝ ያደነውን አቅርቦ አሳየ::

**ግድያ** ስ 1. የመግደል ተግባር:: 2. ሽሚያ፥ ርብርቦሽ፥ ትግል:: *እቃውን ያገኘሁት በስንት ግድያ ነው::*

**ተገደለ** ግ እንዲሞት ተደረገ::

**ተጋደለ** ግ አንድ ነገር ለማግኘት ወይም ለመፈፀም ከፍተኛ ጥረት አደረገ፥ በጣም ታገለ፥ ተሟሟተ::

**ተጋዳይ** ቅ ለአገር ነፃነትና ለክብር ወይም ለቆመለት አላማ ሲል ህይወቱን አሳልፎ የሚሰጥ::

**ተጋድሎ** ስ አንድን አላማ ለማሳካት የሚደረግ ከፍተኛ ትግል::

**አጋደለ** ግ አሻማ፥ አራከተ፥ አታገለ::

**ገደል** ስ 1. ውሃ ወይም ሌላ ነገር የቦረቦረውና ወደታችና ወደጎን ርዝመት ያለው ቦይ፥ አዘቅት:: 2. ከተራራ ጫፍ እስከ ግርጌ ያለ የመሬት አካል::

**ገደል ገባ** 1. ተበላሸ፡ ያለውጤት ቀረ:: 2. ትልቅ ችግር ላይ ወይም ስህተት ላይ ወደቀ:: 3. ከገደል ጫፍ ላይ ወደ ታች ወደቀ::

**ገደላገደል** ገደል የበዛበት::

**የገደል ማሚቶ** ስ 1. በገደል ወይም እንደ ገደል ባለ ነገር አካባቢ ሲጮሁ ከገደሉ ጋር ተጋጭቶ የሚመመለስና በተመሳሳይ መልክ የሚሰማ ጩሀት፤ ድምፅ:: ቅ 2. (ዘይ.) የራሱን ሳይሆን የሌላ ሰው ሃሳብ የሚያስተጋባ (ሰው)::

**ገደላማ** ቅ ገደላገደል::

**ገደመ** ግ ገዳም እንዲሆን አደረገ::

**ገዳም** ስ መነኮሳት ከአለማዊ ኑሮ ተገልለው በሃይማኖታዊ ስርአትና ደንብ እየተዳደሩ የሚኖሩበት ቤተክርስቲያን ያለበት ቦታ::

**ገዳም ገባ** አለማዊ ኑሮን በመተው መንፈሳዊ ኑሮን ለመኖር ገዳም ውስጥ መቀመጥ ጀመረ፤ መነነ::

**የገዳም አባት** ስ የገዳም ሹም፥ የመነኮሳት አስተዳዳሪ፤ አበምኔት::

**ተገደመ** ግ ገዳም ሆነ::

**አስገደመ** ግ ገዳም እንዲሆን አስደረገ::

*ገደመ

**ገደማ** ስ አካባቢ:: *ወደ ሁለት ሰአት ገደማ ይመጣል / ቤቱ ወደ ፒያሳ ገደማ ነው::*

**ጋድሚያ** ቅ (ስድብ) እንቅልፋም፤ ሰነፍ::

**ጋድም** ስ ርብራብ::

**ግድም** ስ ገደማ::

**ተጋደመ** ግ 1. ወደ ጎን በቁመቱ ተዘረጋ:: 2. ተኛ::

**ተገዳደሙ** (ነውር) የግብረ ስጋ ግንኙነት ፈፀሙ::

**አጋደመ** ግ በቁመቱ አስተኛ፥ ዘረጋ::

**አጋደመው** 1. ዘረጋው፥ በቁመቱ አሰተኛው:: 2. ጣለው፥ ዘረረው::

**አግዳሚ** ስ 1. አግዳሚ ወንበር:: 2. ወደጎን በቁመቱ ተዘርግቶ የሚቀመጥና ለተለያየ ግልጋሎት የሚውል (አጣና፥ብረት፥...) ::

**አግዳሚ ወንበር** ስ ወደ ጎን ቁመቱ ረዥም ሆኖ ብዙ ሰው ሊያስቀምጥ የሚችል ወንበር::

**አግድመት** ስ ሽቅብ ወይም ቁልቁል ሳይሆን በጎን በኩል የሚያስኬድ መንገድ::

**አግድም** ቅ ቀጥ ብሎ ሳይሆን ወደጎን:: *የዛፉ አበቃቀል አግድም ነው::*

**አግድም አየ** በንቀት አየ ወይም ተመለከተ::

**አግድም አደግ** (ስድብ) ሳይቀጣ ያደገ፥ ባለጌ::

**አግድሞሽ** ስ 1.አግድመት:: 2. ወደ ጎን::

*ገደረ

**ተገደረ** ግ ታበየ፥ በኩራት ተወጠረ::

**ተገዳደረ** ግ 1. ዝ.ከ. 2. ተፎካከረ(እኔ እበልጥ እኔ እበልጥ በማለት)::

**ተግዳሮት** ስ 1. ትእቢት፥ ማንአለብኝነት:: 2. ሽሙጥ::

*ገደረደረ

**ግድርድር(ገደርዳራ)** ቅ አንድን ነገር ለማድረግ፥ ለማግኘት፥... እየፈለገ እንደማይፈልግ መስሎ የሚቀርብ፥ ፍላጎቱን የሚደብቅ ወይም አቅሙ ከሚፈቅድለት በላይ ለማድረግና ያለው ለመምሰል የሚሞክር::

**ተግደረደረ** ግ 1. አንድን ነገር ለማድረግ ወይም ለማግኘት እየፈለገ እንደማይፈልግ መስሎ ቀረበ፥ ፍላጎቱን ደበቀ:: 2 ሳይኖረው እንዳለው መስሎ ቀረበ (ሃብት፥ ንብረት)::

**ተግደርዳሪ** ቅ ግድርድር::

**አግደረደረ** ግ 1. በልቡ እየፈለገ በአፉ አልፈልግም ወይም አላደርግም የሚልን ሰው እሺ እንዲል ደጋግሞ ለመነ፥ ጠየቀ:: 2. ለተወሰነ፥ ለጥቂት ጊዜ አቆየ:: *ያለኝ ገንዘብ እስከ ደመወዝ ያግደረድረኛል::*

**አያግደረድርም** 1. ያለው አነስተኛ ነው፤ ለብዙ ጊዜ አይበቃም:: 2. አያኮራም::

**ገደበ** ግ 1. አገደ፥ ገታ፥ ከለከለ:: 2. ወሰነ፥ ገደብ አበጀ:: 3. ግድብ ሰራ፥ ከተረ::

**ገደብ** ስ 1. ልክ፥ መጠን፥ ወሰን(የጊዜ፥ የውለታ፥...):: 2. ማእቀብ::

**ገደቡ ተነሳ** ታግዶ ወይም ተከልክሎ የነበረው ነገር እንዲካሄድ፥ እንዲከናወን ተፈቀደ::

**በገደብ** 1. ልቅ ባልሆነ ሁኔታ፥ በውሱን (የጊዜ፥ የግንኙነት):: 2 በተወሰነ ውለታ:: *ባሏ ሁለተኛ ሲጋራ ላያጨስ ቃል ገብቶ በገደብ ታረቁ::*

**ግድብ** ስ ውሃ መጠኑና ከፍታው ጨምሮ ጉልበት ኖሮት ለሃይድሮ ኤሌክትሪክ ሃይል ማመንጫነት እንዲያገለግል ወይም የውሃ እጥረት በሚኖርበት ወቅት ውሃ አጠራቅሞ ለማቆየት ሲባል ወይም ውሃ ወደ አልተፈለገ አቅጣጫ እንዳይፈስ ለማድረግ ወይም ውሃውን ለእርሻ ስራ ለማዋል በአፈር፥ በአሸዋ ወይም በድንጋይ ወይም በሲሚንቶ ተገንብቶ የሚሰራ መከለያ፥ ማገጃ፥

መከተሪያ::

**ተገደበ** ግ ግድብ ተሰራለት (ውሃ)::

**ገደደ**[1] ግ ጠመመ፥ ዘመመ::

**ገዳዳ** ቅ ጠማማ፥ ወልጋዳ፥ ዘመም ያለ::

**ተንጋደደ** ግ ተጣመመ፥ ዘመም አለ::

**አንጋደደ** ግ 1. ተንጋደደ:: 2. አጣመመ፥ ዘመም አደረገ::

**ገደደ**[2] ግ ቸገረ:: *የሱ ነገር መቶ ገደደኝ::*

**ግዳጅ** ስ 1. ከራስ ስሜትና ፍላጎት ውጪ በሆነ ተፅእኖ አንድን ተግባር የማከናውን ሁኔታ :: 2. በመንግስት፥ በፖለቲካ ድርጅት፥...ትእዛዝ መሰረት የሚፈፀም የጦርነት፥ የአሰሳ፥ የጥበቃ፥... እንቅስቃሴ::

**ግዳጅ ሄዷል (ግዳጅ ላይ ነው)** ለውጊያ ወደ ጦር ሜዳ ሄዷል::

**ግዴታ** ስ 1. መሆን ወይም መፈፀም ያለበት፥ የማይቀር ነገር:: 2. ሃላፊነት:: *ልጆን የማሳደግ ግዴታ* አለበት:: 3. ግዳጅ::

**ግዴታ ገባ** አንድን ነገር ሊፈፅም ወይም ሊያደርግ ተዋዋለ፥ተስማማ፤ ቃል ገባ::

**ግድ** 1. ውዴታና ፈቃደኝነት የሌለበት:: 2. መሆን ወይም መፈፀም ያለበት፥ የማይቀር፥ አስፈላጊ:: *ግድ ሆኖብኝ እንጂ ላልመጣም ነበር /የሱ መምጣት ግድ ነው::*

**በግድ** ያለፍላጎት፥ በማስገደድ::

**የግዱን** ሳይፈልግ፥ አማራጭ ሲያጣ::

**ግድ አለ** አስቸገረ፥ አስጨንቆ ያዘ:: *ከሱ ጋር እንድሄድ ግድ አለኝ::*

**ግድ የለም** 1. የዘቻ አነጋገር:: *ግድ የለም አሁን ብታመልጠኝ በሂላ ላገኝሃለሁ::* 2. ይሁን፥ ምንም አይደለም (መስማማትን፥ ቅር አለመሰኘትን ለመግለፅ):: 3. አታስብ፥ አትጨነቅ እኔ እፈፅመዋለሁ ለማለት የሚነገር::

**ግዴለሽ** ቅ ችላ ባይ፥ ቸልተኛ፤ ሃሳብ የለሽ::

**ተገደደ** ግ ያለፍላጎቱ፥ በሃይል ወይም በትእዛዝ እንዲያደርግ ሆነ::

**አስገደደ** ግ ያለፍላጎት፥ በሃይል ወይም በትእዛዝ እንዲፈፀም ወይም እንዲከናወን አደረገ::

**ገደገደ (ገረገደ)** ግ 1. አቆመ፥ ተከለ (የእንጨት አጥርን ወይም ግድግዳን):: 2. አቆመ፥ ገተረ(ባልሆነ ቦታ ወይም ሁኔታ):: 3. ቆዳን ወጥሮ በችካል መታ::

**ግድግዳ** ስ ወደ ላይ ቁመት ወደ ጎን ርዝመት እንዲኖረው ተደርጎ ከእንጨት ወይም ከጡብ ወይም ከብሎኬት፥... የሚሰራ የቤት ወይም የህንፃ ጎንና ቁመት ወይም ክፍሎችን ለመከፋፈል፥ ለመለያየት ወይም አንድን ነገር ከሌላው ለመለየት የሚያገለግል መከለያ::

**የግድግዳ ሰአት** ስ ግድግዳ ላይ የሚሰቀል ትልቅ ሰአት::

**የግድግዳ ወረቀት** ስ በቤት ውስጥ ግድግዳን ለማስጌጥ ሙሉ በሙሉ ግድግዳው ላይ የሚለጠፍ ወረቀት::

**ተገደገደ** ግ 1. ቆመ፥ ተተከለ(የአጥር ወይም የግድግዳ እንጨት):: 2. ቆመ፥ ተገተረ (ባልሆነ ቦታ ወይም ሁኔታ):: 3. ተወጠረ(ቆዳ በችካል)::

***ገደገደ**

**ግድጋዳ** ቅ 1. ቀጥ ብሎና ሚዛኑን ጠብቆ መቆም ወይም መራመድ የማይችል፤ የሚወዛወዝ:: 2. ፊደሎችን እየቆጠረና እየጎተተ የሚያነብ ወይም የሚናገር::

**ተንገዳገደ(ተንገደገደ)** ግ ቀጥ ብሎና ሚዛኑን ጠብቆ መቆም ወይም መራመድ ተሳነው፥ ተውተረተረ::

**አንገዳገደ(አንገደገደ)** ግ ቀጥ ብሎና ሚዛኑን ጠብቆ መቆም ወይም መራመድ እንዳይችል አደረገ፥ አውተረተረ::

**ገደፈ**[1] ግ 1. ያም ፈታ ወይም ፈሰከ ወይም ጊዜው ሳይደርስ ያምን ሻረ፥ በላ:: 2 ሲያነብ ወይም ሲፅፍ ፊደልን ወይም ቃልን ተወ፥ ዘለለ::3. በኮከብ ቆጠራ ጊዜ አንድን የተወሰነ ቁጥር ለሌላ ለተወሰነ ቁጥር አካፍሎ ቀሪውን ያዘ::

**ግዱፍ** ቅ ተቀንሶ እንዲወገድ የተደረገ የቁጥር መጠን (በኮከብ ቆጠራ ስሌት ጊዜ)::

**ግድፈት** ስ በመፃፍ ወይም በማንበብ ጊዜ ፊደልን ወይም ቃልን በመርሳት ወይም በመዝለል የሚፈፀም ስህተት ወይም ሌላ ማንኛውም ስህተት::

**ተገደፈ** ግ 1. በንባብ ወይም በፅሁፈት ጊዜ ፊደል ወይም ቃል ተዘለለ ወይም ተተወ:: 2. አንድ ቁጥር ለሌላ ቁጥር ተካፈለ (የኮከብ አቆጣጠር ስሌት)::

**አገደፈ** ግ እንዲፈስክ ወይም ያም እንዲፈታ አደረገ (ምግብ በማቅረብ፥ በመስጠት)::

**አስገደፈ** ግ 1. ጊዜው ሳይደርስ ያምን አስትቶ አስበላ፥ አስሻረ:: 2. አገደፈ::

**ገደፈ**[2] **"ደገፈ"**ን ተመ.

**ገዲ "ገዴ"**ን ተመ.

**ገዳም "ገደመ"** ስር ተመ.

**ገዳም "ገድ"** ስር ተመ.

**ገዳይ "ገደለ"** ስር ተመ.

**ገዳዳ "ገደደ"** ስር ተመ.

**ገዴ (ገዲ)** ስ ደረቱ ነጭ፥ጀርባው ጥቁር፥ ጥፍሩ ቆላፋ የሆነና እንደ እባብ፥ አይጥ፥...

የመሳሰሉትን የሚመገብ የአሞራ አይነት (ስእሉን አሞራ ስር ተመ.)።

**ገድ** ስ ጥሩ እድል ወይም ጥሩ አጋጣሚ።

**ገድ በለኝ** የሚቀጥለው አጋጣሚ፥ እንቅስቃሴ፥ ... የተቃና ወይም የተሳካ እንዲሆን ጀምርልኝ (ምግብ ወይም መጠጥ በመጋበዝ ወይም የሚሸጠውን እቃ የመጀመሪያ ገገር ሆኖ በመግዛት፥...)።

**ገደቢስ** ቅ እድለ ቢስ።

**ገዳም** ቅ ጥሩ እድል የሚያጋጥመው፥ እድለኛ።

**ገድል** ስ 1. (ክር.) ፃድቃን ወይም ሰማእታት ስለሃይማኖታቸው የተቀበሉት ችግር፥ ፈተና፥...። 2. ፃድቃን ወይም ሰማእታት ስለሃይማኖታቸው የተቀበሉት ችግር ፈተናና የህይወት ታሪካቸው የተፃፈበት መፅሃፍ።

**ገድለኛ** ቅ የሚያስገርም፥ የሚያስደንቅ፥ ተአምር፥... ስራ የሚሰራ፤ ተአምረኛ፡

**ገድል ተሰራ** ተአምር ተሰራ ወይም ታየ።

**ገድጋዳ** "*ገደገደ" ስር ተመ.

**ገጀራ** ስ ቆንጨራ።

**ገገመ** ግ (ያራዳ አነ.) ችክ አለ፥ ድርቅ አለ።

**ግግማ** ቅ 1. ደረቅ፥ ችክ። 2. ያልሰለጠነ።

***ገገመ**

**ገመምተኛ(ገገምተኛ)** ቅ በቅርብ ጊዜ ታሞ የነበረና እየተሻለው ወይም እየዳነ ያለ በሽተኛ።

**አገገመ** ግ ተሻለው፥ እየዳነ ነው (በሽተኛ)።

**ማገገሚያ** ስ ታሞ የነበረ ሰው በደንብ እስኪድን ድረስ የሚያስፈልገው የምግብ አይነት ወይም የሚቆይበት ቦታ።

**ገገረ** ግ ፈሳሽ የነበረው ነገር ረጋ፥ ጠጣር ሆነ።

**ግግር** ቅ 1. ፈሳሽ የነበረና ወደ ጠጣርነት የተለወጠ፥ የረጋ (ለምሳሌ ግግር በረዶ)። 2. (ዘይ.) ዝምታ የሚያበዛ።

**ገጠመ** ግ 1. ከደነ፥ ዘጋ። 2. ልክክ አለ፥ በደንብ ተከደነ። 3. ተለያይቶ የነበረውን የአንድ አካል ክፍል አያያዘ፥ ሰካ፥ አንድ አደረገ። *የመኪናውን አካል ገጠመ።* 4. ተስማማ፥ አንድ ሆነ፥ ልክ ሆነ። 5. ተወዳጀ፥ ጓደኛ ሆነ። 6. አገኘ፥ ደረሰ፥ አጋጠመ። *እንዲህ አይነት ነገር ገጥሞኝ አያውቅም።* 7. ጠርነት፥ ሙግት፥ ትግል፥ ስድብ፥... (ከተቃራኒው ወይም ከተፎካካሪው ወገን ጋር) አካሄደ። 8.ግጥም ደረሰ። 9. ቤት መታ(ግጥም)።

**ገጣሚ** ስ ግጥም የሚደርስ።

**ገጠመኝ** ስ ያለፈ የኑሮ ወይም የህይወት ልምድ፤ ተሞክሮ።

**ግጥሚያ** ስ ውድድር፥ ፉክክር(ለምሳሌ የእግር ኳስ ግጥሚያ)።

**ግጥም** ስ 1. ስምም ወይም አንድ መሆን። *ከልጁ ጋር ግጥም ናቸው።* 2. ዝግ፥ ቁልፍ፥ እሽግ። 3. በስንኝ በስንኝ እየሆነና ቤት እንዲመታ እየተደረገ የሚዘጋጅ ንግግር ወይም ፅሁፍ።

**ግጥም ደረደረ** ግጥም ደረሰ።

**ግጥም ደርዳሪ** ገጣሚ።

**ግጥም አለ** ግ 1. ሞላ፥ ጢም አለ። 2. ድንገት ተገናኘ። 3. ነፍሱ ከስጋው ተለያየ ወይም የሞተ ያህል ራሱን ሳተ።

**ግጥም አድርጎ** በደንብ አድርጎ። *ግጥም አድርጎ በላ/ግጥም አድርጎ አሰረ / ግጥም አድርጎ ጠጣ።*

**ግጥምጥም አለ** ግ 1. ድንገት ተገናኘ። *ዝያ ላይ ድንገት ከድሮ ጓደኛዬ ጋር ግጥምጥም አልን።* 2. ተሳካ (ለአንድ ጉዳይ የሚያስፈልጉ የተለያዩ ነገሮች በተመሳሳይ ጊዜ በመገኘትና በመከናወን)።

**ተገጣጠመ** ግ 1. ድንገት ተገናኘ። 2. አንድን የተወራ ውሸት፥ ሃሜት፥... ለማጣራት ወሬውን ወይም ሃሜቱን ካወራው ሰው ጋር የተወራበት ሰው ፊት ለፊት ተገናኝቶ ተነጋገረ። 3. የተለያዩ ነገሮች ወይም ሁኔታዎች በተመሳሳይ ጊዜ ወይም ሁኔታ ተፈፀሙ። 4. ተሳካ (ለአንድ ጉዳይ የሚያስፈልጉ የተለያዩ ነገሮችን በተመሳሳይ ጊዜ ማከናወን ተቻለ)።

**ተገጣጣሚ** ቅ ተሰካክቶ አንድ አካል የሚሆን ወይም ሊፈታቱና ሊለያዩ የሚችሉ ትናንሽ ክፍሎች ያሉት። *ተገጣጣሚ አልጋ/ ተገጣጣሚ ቤት።*

**ተጋጠመ** ግ 1.ተፋለመ፥ ተዋጋ። 2. (ስፖ.) ተወዳደረ፥ ተፎካከረ፤ ተጫወተ።

**ተጋጣሚ** ስ ተወዳዳሪ፥ ተፎካካሪ (በስፖርት ጨዋታዎች)።

**አገጣጠመ** ግ 1. አገናኘ፥ ፊት ለፊት አቀራረበ(የተወራን ሃሜት ወይም ውሸት፥... ለማጣራት ሲባል አውሪውንና የተወራበትን ሰው)። 2. የ "**አጋጠመ**"ን 2ኛ ፍቺ ተመ.

**አጋጠመ** ግ 1. አገናኘ፥ ፊት ለፊት አቀራረበ (የተወራን ሃሜት ወይም ውሸት ለማጣራት ሲባል አውሪውንና የተወራበትን ሰው)። 2. አንድ ድርጊት፥ ሁኔታ ድንገት ሆኖ ደረሰ። *ችግር አጋጠመው /እድል አጋጠመው።* 3. የሞተ ሰውን ገነዘ፥ አስተካከለ (አይኑን፥ አፉን፥... በመዝጋት)።

**አጋጣሚ** ቅ ሳይታሰብ በድንገት የሚደርስ፥ የሚሆን፥ የሚገኝ (ጥሩ ወይም መጥፎ ነገር)።

**ገጠር** ስ ከከተማ ውጪ የሆነ ቦታ፤ ባላገር።

**ገጠሬ** ስ በገጠር ኗሪ የሆነ፣ ባላገር::

**ገጠበ** ግ 1. በመምለጥ ወይም በመላጥ አቆሰለ:: 2. ወጣ ገባ አድርጎ ቆረጠ ወይም ላጨ(ለምሳሌ ፀጉርን):: 3. ከመጠን በላይ ቆረጠ፥ነጨ(ለምሳሌ ሳርን):: 4. ገረፈ፥ ደበደበ፥ መታ(በአለንጋ፥ በጅራፍ፥...)::

**ገጣባ** ስ 1. የጋማ ከብት ጀርባ ላይ የሚገኝ ቁስል:: ቅ 2. ጀርባው ላይ የተላጠ ወይም ቁስል ያለበት(የጋማ ከብት):: 3. (ስድብ) መላጣ::

**ግጥብ** ቅ 1. ተልጦ የቆሰለ (የጋማ ከብት ጀርባ):: 2. ሳርና ቅጠል፥... የሌለበት ወይም የተመለጠ (መሬት)::

**ገጠገጠ**[1] ግ በብዛት ደረደረ:: *ላምባቱም ማቶጂ ላይ ቀለበት ገጥግጣለች::*

**ተገጠገጠ** ግ 1. በብዛት ተደረደረ፥ ተከማቸ *ተማሪው ላዳራሹ ውስጥ ተገጥግጧል::* 2. ግጥም ብሎ ሞላ፥ ጢም አለ:: *ላዳራሹ በሰው ተገጥግ ጧል::*

**ገጠገጠ**[2] ግ ጠባ፥ መጠመጠ (ጡትን፥ ጡጦን፥...)::

**ገጠጠ** ግ 1. አፈንግጦ ወይም ወደ ውጪ ወጣ ብሎ ታየ (ለምሳሌ ጥርስ):: 2. (ዘይ.) ግልፅ ሆኖ ወይም ፈጦ ታየ::

**ገጣጣ** ቅ 1. ጥርሱ ወደ ውጪ ወጣ ብሎ የሚታይ:: 2. መሳቅ የሚያበዛ፣ መገለጢጥ::

**አገጠጠ** ግ 1. ገጠጠ:: 2. ሳቀ፥ ገለፈጠ::

***ገጠጠ**

**ተንጋጠጠ** ግ ወደ ላይ ቀና አለ (አንገት)::

**አንጋጠጠ** ግ 1. ወደ ላይ ቀና አለ፤ ወደ ሰማይ አየ:: 2. አንገቱን አሰገገ፥ አረዘመ (ለማየት)::

**ገጣሚ** "ገጠመ" ስር ተመ.

**ገጣባ** "ገጠበ" ስር ተመ.

**ገጣጣ** "ገጠጠ" ስር ተመ.

**ገጥ** "ገፅ"ን ተመ.

**ገጨ** ግ 1.መታ፥ ለተመ፥ አላተመ:: 2. የግጭት አደጋ አደረሰ::

**ግጭት** ስ 1. ጥል፥ ጠብ:: 2. አንድ ተሽከርካሪ ሌላ ተሽከርካሪን ወይም ሰውን፥ እንስሳን፥ ንብረትን፥... በመግጨቱ የተነሳ የሚፈጠር አደጋ::

**ተገጨ** ግ የግጭት አደጋ ደረሰበት::

**ተጋጨ** ግ 1. ተላተመ፥ የግጭት አደጋ አደረሰ ወይም ደረሰበት:: 2. ተጣላ::

**አጋጨ** ግ 1. አላተመ፥ እንዲጋጭ አደረገ:: 2. መታ:: 3. አጣላ፥ አራበሸ::

***ገጨገጨ**

**ተንገጨገጨ(ተንገጫገጨ)** ግ ሲወዛወዝ ወይም ሲነቃነቅ ድምፅ አሰማ::

**አንገጨገጨ(አንገጫገጨ)** ግ ወዘወዘ ወይም አነቃነቀ (ለምሳሌ በኮረኮንች ላይ የሚሽከረከር መኪና)::

**ገፅ (ገጥ)** ስ 1. ፊት፥ መልክ:: 2. በፊት በኩል (የጀርባ ተቃራኒ) :: 3. የመፅሃፍ፥ የጋዜጣ ቅጠል ወይም ወረቀት ወይም የአንድ ቅጠል ወረቀት አንደኛው ወገን::

**ገፀ በረከት** ስ ስጦታ፥ እጅ መንሻ፥ መታያ::

**ገፀ ባህርይ** ስ በልቦለድ፥ በትያትር፥...ድርሰት ውስጥ የሚገኝ ሰው( ለምሳሌ ፍቅር እስከ መቃብር በተባለው መፅሃፍ ውስጥ ከሚጠቀሱት ሰዎች መካከል ጉዱ ካሳ አንዱ ገፀ ባህርይ ነው)::

***ገፈለለ**

**ተንገፈለለ** ግ 1. በጣም ረዥም ሆነ፥ ተንቀዋለለ:: 2. ቁመቱ ከሚገባው በላይ የረዘመ ሆኖ ፍሬ ሳይዝ ቀረ (ለምሳሌ በቆሎ)::

***ገፈለፈለ**

**ግንፍልፍል(ግፍልፍል)** ስ እየፈላ ባለ ወጥ ውስጥ እንጀራ በትላልቁ ቆረስ ቆረስ አድርጎ በመጨመርና በማደባለቅ የሚዘጋጅ ምግብ::

**ተግፈለፈለ** ግ 1. ተፍለቀለቀ፥ ተንተከተከ (ወጥ):: 2. ግንፍልፍል ተዘጋጀ::

**አግፈለፈለ** ግ 1. አፈላ፥ አንተከተከ(ወጥን፥ ግንፍልፍልን):: 2. ግፍልፍል አዘጋጀ::

**ገፈራ** ስ የፈረስና የበቅሎ መኖ::

**ገፈተረ** ግ በሃይል ገፋ፥ አሽቀነጠረ::

**ገፈት(ገፈታ)** በጠላ ላይ የሚንሳፈፍ የአሻሮ፥ የብቅል፥ የጌሾ ያልደቀቀው ክፍል፥ ቁርጥራጭ::

**ገፈት ቀማሽ** የአንድ ችግር፥ መከራ፥... የመጀመሪያው ተጠቂ፥ አሳር ቀማሽ::

**ገፈታም** ቅ (ስድብ) ሰካራም::

**ገፈገፈ** ግ ለረዥም ጊዜ ሳያቋርጥ ከፈለ(እዳን፥ ክፍያን፥...)::

***ገፈገፈ**

**ግፍግፍ አለ** ግ ተንገፈገፈ::

**ግፍግፍ አደረገ** ግ አንገፈገፈ::

**ተንገፈገፈ** ግ ተማረረ፥ ተንገሸገሸ፥ ሰለቸ::

**አንገፈገፈ** ግ አንገገሸገሸ፥ አሰለቸ::

***ገፈጠጠ**

**ግፍጥጥ(ገፍጣጣ)** ቅ (ስድብ) ሆዱ የተንዘረጠጠ ወይም ትልቅ የሆነ::

**ግፍጥጥ አለ** ግ ተንገፈጠጠ::

**ግፍጥጥ አደረገ** ግ አንገፈጠጠ::

**ተንገፈጠጠ** ግ ተንዘረጠጠ ወይም ትልቅ ሆነ (ሆድ)::

**አንገፈጠጠ** ግ አንዘረጠጠ (ሆድን)::

**እንግፍጥ** ቅ ሆዱ የተንዘረጠጠ::

**ገፈፈ** ግ 1. ቆዳን ከስጋ ለየ:: 2. ልብስን ከሰውነት ላይ አነሳ:: 3. ቀማ፥ ዘረፈ:: 4. ለቀቀ፥ ደበዘዘ(ቀለም):: 5. ገለጠ(ዳመና)::6. ስልጣንን ወይም ማእረግን ቀማ፥ ሻረ::

**ገፈፋ** ስ ዝርፊያ፥ ቅሚያ::

**ገፋፊ** ቅ ቀማኛ፥ ዘራፊ::

**ገፋ** ግ 1. ገፈተረ፥ ወረወረ:: 2.ፎቀቅ አደረገ፥ወደፊት አስጠጋ:: 3. ናጠ፥ ወዘወዘ (ወተት ያለበትን እቃ )::4. ወደ ፊት አመራ፥ ሄደ:: 5.እየተሰራ ወይም እየተከናወነ ሄደ (ስራ):: 6.እየጨመረ ወይም እየተለቀ ሄደ(ሆድ):: 7.ረዘመ:: *ክረምቱ ገፋ::* 8. በደለ፥ አንገላታ:: 9. ጨመረ:: *እድሜው እየገፋ ሄደ::*

**ገፍቶ መጣ** ሳይፈለግ በራሱ መንገድና ሁኔታ ሆነ ወይም መጣ::

**ግፋ ቢል** ቢበዛ፥ ቢጨምር፥ የባሰ ቢመጣ::

***መግፊያ*** ስ የወተት መናጫ::

**ገፊ** ቅ አደጋ ወይም ችግር የደረሰው እሱ በአካባቢው በመኖሩ ወይም በመገኘቱ ምክንያት ነው ተብሎ የሚታመንበት ነገር ወይም ወላጆቹ፥ ዘመዶቹ፥... በሞት አልቀውበት ብቻውን የቀረ ፤ ገደ ቢስ ::

**ግፊያ** ስ ከሰው ብዛትና ከመጣበብ የተነሳ የሚፈጠር ትርምስ፥ ትንቅንቅ::

**ግፊት** ስ ጉትጎታ፥ ተፅእኖ:: *ንቅናቄው የውጭ ግፊት አለበት::*

**ግፍ** ስ አንዱ በሌላው ላይ የሚያደርሰው ወይም የሚፈፅመው በደል፥ ክፉ ስራ::

**ግፍ ዋለ** ክፉ አደረገ፥ ግፍ ሰራ፥ በደል ፈፀመ::

**ግፈኛ** ቅ አቅም አለኝ ብሎ ሌላን የሚበድል፥ ግፍ የሚሰራ::

**ገፋፋ** ግ በል በል አለ፥ አበረታታ፥ ጎተጎተ (አንድን ድርጊት እንዲፈፅም)::

**ተገፋ** ግ በደል ወይም ግፍ ደረሰበት::

**ተገፋፋ** ግ በል በል ወይም አድርግ አድርግ ተባለ፥ ተበረታታ፥ ድፍረት አገኘ(አንድ ድርጊት እንዲፈፅም)::

**ተጋፋ** ግ 1. ተቀናቀነ፥ ተዳፈረ:: *ስልጣን ተጋፋ::* 2. ትርምስ ወይም ትንቅንቅ ባለበት ቦታ ገብቶ ከመጣበብ የተነሳ ተገፈታተረ::

**አጋፋ** ግ እንዲጋፋ ምክንያት ሆነ::

**ገፋፊ** "ገፈፈ" ስር ተመ.

**ገፋፋ** "ገፋ" ስር ተመ.

**ገፍ** ቅ ብዙ:: *ዘንድሮ ዝናቡ ገፍ ነው::*

**በገፍ** በብዛት::

**ገፍጣጣ** "ገፈጠጠ" ስር "ግፍጥጥ"ን ተመ.

**ጉ** የ "ገ" ፊደል ካእብ ዘር::

**ጉለንታ** "ጎለንታ"ን ተመ.

**ጉሊት**[1] ስ 1.ያልደቀቀ አፈር፤ ጓል:: 2. በምስጥ የተሰራ ጉብታ::

**ጉሊት**[2] "ጎለተ" ስር "ጉልት"ን ተመ.

**ጉላንጆ** ቅ 1. በቀላሉ የማይታኘክ፥ መንቻካ ስጋ::2. (ዘይ.፥ ስድብ) ፀባዩ መጥፎ የሆነ፥ ችኮ::

**ጉል** "ጓል"ን ተመ.

**ጉልህ** "ጎላ" ስር ተመ.

**ጉልላት** ስ ብዙውን ጊዜ ክብ ሆኖ በተሰራ ቤት ወይም በቤተክርስቲያን አናት ላይ የሚደረግ ድቡልቡል ወይም ክብ ወይም የአክሊል ወይም የዘውድ ቅርፅ ያለውና ከቆርቆሮ ፥ ከሸክላ፥... የሚሰራ ጌጥ::

**ጉልማ** "ጎለመ" ስር ተመ.

**ጉልምስና** "ጎለመሰ" ስር ተመ.

**ጉልበተኛ** "ጎለበተ" ስር ተመ.

**ጉልበታም** ዝ.ከ.

**ጉልበት** ዝ.ከ.

**ጉልባን** ስ የባቄላ ክክ ከስንዴ ወይም ከተፈተገ ገብስ ጋር አንድ ላይ ተቀቅሎ የሚዘጋጅና የፀሎተ ሃሙስ እለት የሚበላ ንፍሮ::

**ጉልት** ስ ቀደም ባለው ጊዜ ከንጉስ ይሰጥ የነበረ ርስት::

**ጉልተኛ** ቅ ባለጉልት::

**ጉልት** "ጎለተ" ስር ተመ.

**ጉልቻ** ዝ.ከ.

**ጉልድም** "ጎለደመ" ስር ተመ.

**ጉልድፍ** "ጎለደፈ" ስር "ጎልዳፋ"ን ተመ.

**ጉልጎላ(ጉልጓሎ)** "ጎለጎለ" ስር ተመ.

**ጉልጥምት** ስ 1. የጉቶ ቂጥ:: 2. የቅልጥም ጫፍና ጫፍ፥ የአጥንት ራስ::

**ጉሎ(ቃጭማ)** ስ ቅጠሉ ሰፋፊ የሆነና ፍሬው ዘይት የሚወጣው የእፅዋት አይነት::

**የጉሎ ዘንግ** (ዘይ.)ጥንካሬ የሌለው፥ አቅመ ቢስ::

**የጉሎ ዘይት** ስ ከጉሎ ተክል ፍሬ የሚዘጋጅ ዘይት::

**ጉመሮ(ገመሮ)** ስ ፍሬው የሚበላ፥ እንደ ሃረግ በዛፍ ላይ የሚጠመጠምና እሾህ ያለው የእፅዋት አይነት::


**ጉመደው** ስ እንስሳትን የሚገድል የበሽታ አይነት::

**ጉማ**[1] ስ ሰው የገደለ ሰው ለሟች ወገን የሚከፍለው የገንዘብ ካሳ ወይም የነፍስ ዋጋ።

**ጉማ**[2] ቅ ቀራጭ፣ ሙዳ (ስጋ)።

**ጉማምላ** ስ በባህር ዳርቻ የሚበቅል ቀላ ያለና አንጓ ያለው የእፅዋት አይነት።

**ጉማሬ** ስ ቆዳው በጣም ወፍራምና ፀጉር አልባ የሆነ ትልቅ ጭንቅላት አጭር ጭራና አጫጭር እግሮች ያሉት በወንዝ ወይም በባህር ውስጥ ወይም አቅራቢያ የሚኖር ግዙፍ ሳረ በል እንስሳ።



ጉማሬ

**ጉማሬ አለንጋ** ስ ከጉማሬ ቆዳ የሚሰራ አለንጋ፣ አኮርባጅ።

**ጉም** ስ አብዛኛውን ጊዜ በክረምት ወራት የሚታይና አልፎ አልፎ ወደታች በመውረድ የምድርን አካል ለተወሰነ ጊዜ የሚሸፍን የተነደፈ ጥጥ የሚመስል ደመና።

**ጉም ለበሰ** በጉም ተሸፈነ፣ ተከለለ።

**የጉም ሽንት** ስ 1. ከጉም ውስጥ የሚንጠባጠብና ምድርን የሚያረጥብ የዝናብ ነጠብጣብ። 2. (ዘይ.) የማይጨበጥ፣ ሸላካ (ሰው)።

**የጉም ጅብ** ስ 1. አካባቢው በጉም በሚሸፈንበት ጊዜ በጉሙ ውስጥ ሳይታይ በመምጣት ቀን በቀን ከብቶችን የሚበላ ጅብ። 2. (ዘይ.) ስስታም፣ ሆዳም።

**ጉምሩክ** ስ እቃዎች ወደ ሃገር ውስጥ ሲገቡና ከሃገር ሲወጡ ቀረጥ የሚያስከፍልና ወደ ሃገር እንዳይገቡ ወይም ከሃገር እንዳይወጡ የተከለከሉ ነገሮችን የሚቆጣጠር የመንግስት አካል።

**ጉምድ** **"ጎመደ"** ስር ተመ.

**ጉምጉምታ** **"*ጎመጎመ"** ስር ተመ.

**ጉማጅ** **"ጎመደ"** ስር ተመ.

**ጉረሮ** **"ጉሮሮ"**ን ተመ.

**ጉረኖ** ስ የፍየልና የበግ ማጎሪያ፣ ማደሪያ።

**ጉራ** ስ የሌለውን አለኝ፣ የማያውቀውን አውቃለሁ፣ የማይችለውን እችላለሁ ወይም እፈፅማለሁ የማለት ወይም ያለውን፣ የሚያውቀውን፣ የሚችለውን፣ የሚሰራውን፣ ...አጋኖ በማውራት የሚቀርብ የዝና ፍለጋ ንግግር ወይም ድርጊት።

**ጉራውን ቸረቸረ / ነሰነሰ / ነዛ/ ነፋ/** ስለአለው ሃብት፣ እውቀት፣ ችሎታ፣... በማጋነን አወራ ወይም የሌለውን አለኝ፣ የማያውቀውን አውቃለሁ፣ የማይችለውን እችላለሁ!... አለ።

**ጉረኛ** ቅ የሌለውን አለኝ፣ የማያውቀውን አውቃለሁ፣ የማይችለውን እችላለሁ፣ የማያደርገውን አደርጋለሁ የሚል ወይም ስለሃብቱ፣ ስለእውቀቱ፣ ስለችሎታው፣... አጋኖ የሚያወራ።

**ጉራማይሌ** ስ 1. ሙሉ በሙሉ ሳይሆን አለፍ አለፍ ብሎ የሚነቀስ የጥርስ ንቅሳት አይነት። 2. የተለያዩ ቋንቋዎችን በማደባለቅ የሚቀርብ ድብልቅ ንግግር ወይም ፅሁፍ (ለምሳሌ የእንግሊዘኛ ቃላት እየተደባለቁበት የሚቀርብ የአማርኛ ንግግር)። 3. ቅይጥ፣ ድብልቅ።

**ጉራንጉር** ስ እንደልብ ለመተላለፍ የማያመች፣ ጠባብና ወጣ ገባ የሆነ ስፍራ።

**ጉራድ** **"ጎረደ"** ስር ተመ.

**[የ]ጉራጌ ጎመን** ስ ቁመቱ ረዘም ያለና ቅጠሉ ሰፋፊ የሆነ የጎመን አይነት።

**ጉሬዛ** ስ ከጦጣና ከዝንጀሮ ወገን የሚመደብ፣ ጢሙና ከትከሻው ጀምሮ በግራና በቀኝ በኩል ያለው አካሉ ነጭ ፣ ከአናቱ ጀምሮ እስከ ወገቡ ደግሞ ጥቁር የሆነ፣ ዙሪያው ብትን ያለ ነጭ ፀጉር የከበበው ጥቁር ጅራቱ ነጭ የጣለበት ወይም ጫፉ ላይ ብትን ያለ ነጭ ፀጉር ያለበት፣ ጥቅጥቅ ባለ ጫካ ውስጥ ውሃ አጠገብ በሚገኙ ረጃጅም ዛፎች ላይ የሚኖርና ካንዱ ዛፍ ወደ ሌላ በረጅሙ እየተምዘገዘገ መዝለል የሚችልና ጦጣ የሚያክል የዱር እንስሳ (ስእሉን የዱር እንስሳ ስር ተመ.)።

**ጉሬዝማ** ቅ ጉሬዛ የሚመስል፤ የነጭና የጥቁር ድብልቅ መልክ ያለው።

**ጉር** ስ ድንጋይ የበዛበት ወይም ድንጋያማ የሆነ መሬት።

**ጉርምርምታ** **"*ጎረመረመ"** ስር ተመ.

**ጉርምስና** **"ጎረመሰ"** ስር ተመ.

**ጉርሻ** **"ጎረሰ"** ስር ተመ.

**ጉርብትና** **"*ጎረበተ"** ስር ተመ.

**ጉርና** ስ የወተት ማጠራቀሚያና መናጫ እቃ።

**ጉርና ሆድ** (ስድብ) ቀበደድ፣ ቀፈታም።

**ጉርናት** **"ጎረና"** ስር ተመ.

**ጉርዝኝ** ስ መጠኑ በእንቅብና በቁና መካከል የሆነ ለእህል መስፈሪያ የሚያገለግል የስፌት እቃ።

**ጉርዳ** ስ ላም እንዳታረግዝ የሚያደርግ የማህፀን ችግር።

**ጉርዳ ሆነች** አልወልድ ያለች ላም ማህፀኗን ዘግቶ እንዳታረግዝ የከለከላት ችግር በጉርዳ በሺ እንዲወገድላት ተደረገ።

**ጉርዳ በሺ** ስ አልወልድ ያለች ላም ማህፀን ውስጥ እጁን በማስገባት እንዳታረግዝ የከለከላትን ችግር የሚያስወግድ ወጌሻ ወይም ባለሙያ።

**ጉርድ** "ጎረደ" ስር ተመ.
**ጉርዶሽ** ዝ.ክ.
**ጉርጥ** ስ በአብዛኛው በመሬት የሚኖርና በመራቢያው ወቅት ውሃ ውስጥ የሚቆይ፥ ቆዳው ሻካራ የሆነ የእንቁራሪት አይነት።
**ጉርጥ አይን** ቅ(ስድብ) አይነ ፈጣጣ።
**ጉርጥርጥ** "ጎረጠ" ስር ተመ.
**ጉርጉጭታ** "ጎረጎጨ"ስር ተመ.
**ጉሮሮ(ጉረሮ)** ስ ለመተንፈሻና ምግብን ወደ ሆድ ለማውረጃ የሚያገለግል አሸንዳ መሰል ውስጣዊ የሰውነት ክፍል።
**ጉሮሮው እስኪሰነጠቅ ጮሀ** በጣም ጮሀ።
**ጉሮሮው ደረቀ** በጣም ተጠማ።
**ጉስር** "ጎሰረ" ስር ተመ.
**ጉስቁል** "ጎሰቆለ" ስር "ጎስቋላን" ተመ.
**ጉስጉሻ** "ጉሽጉሻ"ን ተመ.
**ጉሽ** "ጎሸ" ስር ተመ.
**ጉሽርጥ(ግሽርጥ)** ስ ስሩ ተፍቆና ደቆ ከተቀቀለ በሗላ ሴቶች እጅና እግራቸውን ለማቅለም ወይም ለማስጌጥ የሚቀቡት እንሶስላ የሚመስል የእፅዋት አይነት።
**ጉሽጉሽ (ጉስጉሻ)** ስ ከጭቃ የሚሰራ የእህል ማስቀመጫ፤ ድብኝት።
**ጉበት** ስ ለስላሳ ያለና ጥቁር ቀይ ቀለም ያለው፥ ሃሞት የሚያመነጭና ደምን የሚያጣራ፥ በሆድ እቃ ውስጥ የሚገኝ የሰውነት ክፍል።
**ጉበን** ስ ከመዝጊያ እናት በላይ የሚገኝ የበር አግዳሚ፤ የደፍ ተቃራኒ (ስእሉን ቤት ስር ተመ.)።
**ጉባ**[1] ስ ከረብታ፥ ቁልልታ፥ ጉብታ።
**ጉባ**[2] ስ የማጭድ ቅርፅ ያለው የከብት ቁስል መተከሻ።
**ጉባኤ** ስ 1. በአንድ ጉዳይ ላይ ለመወያየት ወይም ለመነጋገር የሚደረግ ስበሰባ።2. የተወሰኑ ጉዳዮችን እንዲያከናውኑ፥ ደንቦችን እንዲያወጡ፥ የማማከር ስራ እንዲሰሩ ተመርጠው ወይም ተሹመው የሚሰሩ ሰዎች ስብስብ።3.አንድ ጉዳይ ላይ ለመወያየት ወይም ለመነጋገር የተጠራ ተሰብሳቢ በአንድነት የሚገኝበት መድረክ።
**ጉብ**
**ጉብታ** ስ ከፍታነት ያለው ቦታ፥ ከረብታ።
**ጉብ አለ** ግ 1. ከአካባቢው ከፍ ብሎ ታየ። 2. ቁብ ብሎ ተቀመጠ ፥ ጉች አለ።
**ጉብራት** "ጎበረ" ስር ተመ.
**ጉብር** ዝ.ክ.
**ጉብታ** "ጉብ" ስር ተመ.
**ጉብኝት** "ጎበኘ" ስር ተመ.
**ጉብዝና** "ጎበዘ" ስር ተመ.
**ጉብጉባት** "*ጎበጎበ[1] ስር ተመ.
**ጉብጉብ** "*ጎበጎበ" ስር ተመ.
**ጉቦ** ስ ህጋዊም ሆነ ህጋዊ ያልሆነን ጉዳይ ለማስፈፀም ህጋዊ ባልሆነ መንገድ የሚሰጡት ወይም የሚቀበሉት ገንዘብ ወይም ሌላ የአይነት ስጦታ፤ መማለጃ።
**ጉቦ በላ** ጉቦ ተቀበለ ወይም ወሰደ።
**ጉቦኛ** ቅ ጉቦ ካልተሰጠው ጉዳይ የማይፈፅም።
**ጉተና** "ጎተነ" ስር ተመ.
**ጉትት** "ጎተተ" ስር 'ጎታታ'ን ተመ.
**ጉትቻ** ስ ከወርቅ ወይም ከብር ወይም ከነሃስ፥... የሚሰራ የጆሮ ጌጥ።
**ጉትያ** ስ ቀንጮ።
**ጉቶ** ስ 1. ዛፍ ተቆርጦ ከስሩ በኩል የሚቀረው የዛፍ ጉማጅ። ቅ 2. (ዘይ.) በጣም አጭር ሆኖ ወፈር ያለና ብዙ የማይንቀሳቀስ (ሰው)።
**ጉቶ ፊት** ቅ (ስድብ) ፊቱ ድርቶጭ ያለ፤ ቶንጋ።
**ጉች**
**ጉች አለ** ግ 1. ከአካባቢው ተለይቶ ከፍ ወይም ጉብ ብሎ ታየ። 2. ቁጭ አለ።
**ጉች ጉች ያለ ጡት** ስ ደረት ላይ ፈርጠምና ቀጥ ብሎ የሚታይ የሴት ጡት።
**ጉኒና** ስ ከተፈተለ የበግ ፀጉር ወይም ከሳር ወይም ከሰሌን፥... የሚሰራ፥ መሃሉ ላይ ጉትያ የሚመስል ነገር ያለበትና ብዙውን ጊዜ እረኞች የሚያደርጉት ቆብ።
**ጉንቁል** "ጎነቆለ" ስር ተመ.
**ጉንብስ** "*ጎነበሰ" ስር "ጎንባሳ"ን ተመ.
**ጉንዳን** ስ በህብረት የሚኖር፥ ወደ ጥቁረት የሚያደላ መልክ ያለው መጠኑ ከቁጫጭ ከፍ የሚል ተናካሽ የነፍሳት አይነት።



ጉንዳን

**ጉንዳን ነው** በጣም ብዙ ነው።*የመጣው ህዝብ ጉንዳን ነው።*
**ጉንድል** "ጎነደለ" ስር "ጎንዳላ"ን ተመ.
**ጉንድሽ** "ጎነደሸ" ስር ተመ.

**ጉንዶ** ስ ከቀንድ ወይም ከግንድ ተፈልፍሎ የሚሰራ ጥንታዊ የማር መስፈሪያ።

**ጉንጉን** " ጎነጎነ" ስር ተመ.

**ጉንጫም** "*ጎነጨ" ስር ተመ.

**ጉንጭ** ዝ.ከ.

**ጉንፋን** ስ በመጥፎ ሽታ ወይም በብርድ ምክንያት የሚመጣ፥ የሚያስነጥስና የሚያስል፥ አክታና ንፍጥ የሚያስከትል የአጭር ጊዜ በሽታ።

**ጉንፋኑ በሰለ** የጉንፋን ህመሙ እየቀለለ መጣ፥ ለመዳን ተቃረበ።

**ጉንፋናም** ቅ የጉንፋን በሽታ በተደጋጋሚና በተከታታይ የሚይዘው።

**ጉንፍ** "ጎነፈ" ስር ተመ.

**ጉኝር** "ጎኘረ" ስር ተመ.

**ጉዝጓዝ** "ጎዘጎዘ" ስር ተመ.

**ጉዞ** "*ጓዘ" ስር ተመ.

**ጉያ** ስ 1. በጭኖች መሃከል ወይም በብብት አካባቢ ያለው የሰውነት ክፍል።2. እቅፍ። *ልጇን በጉያዋ ይዛለች።* 3. ከለላ፥ ጥበቃ፥ እንክብካቤ። *በላባቱ ጉያ ስር እየኖረ ምን ይነካዋል* ?

**ጉደኛ** "ጉድ" ስር ተመ.

**ጉዳም** ዝ.ከ.

**ጉዳተኛ** "ጎዳ" ስር ተመ.

**ጉዳት** ዝ.ከ.

**ጉዳይ** ስ 1. አንድ መፈፀም ወይም መከናወን ያለበት ስራ ወይም ተግባር። 2. ከአንድ የተወሰነ ነገር፥ ቦታ፥ ሁኔታ፥ ሰው፥...ጋር የተያያዘ ነገር። *የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት።*

**ባለጉዳይ** ቅ 1. ጉዳይ ያለበት ሰው ወይም አንድ የሚፈልገው ነገር እንዲፈፀምለት ወደሚመለከተው ቦታ ሄዶ የሚጠይቅ ወይም የሚያመለከት ፥ የሚከታተል። 2. ነገሩ የሚመለከተው ወይም የሚያገባው።

**ከጉዳይ አልጣፈውም** ትኩረት አልሰጠውም፥ አላሳሰበውም፥ አላስጨነቀውም።

**ጉዳዩ አይደለም** 1.ግድ አይሰጠውም፥ አያስጨንቀውም። 2. አይመለከተውም።

**ጉዳይ አስፈፃሚ /ፈፃሚ** ቅ 1. ከአንድ የተወሰነ ስራ ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን ለማስፈፀም ተቀጥሮ የሚሰራ። ስ 2. አምባሳደር ባልተሾመበት ኤምባሲ ውስጥ የአምባሳደሩን ቦታ ተክቶ የሚሰራ ሰው፥ ዲፕሎማት።

**—ጉዳይ** ስ.የሚቀረው ወይም የሚጎድለው (ብዙውን ጊዜ ለሰአት)። *ለሳት አስር ጉዳይ፡*

**ጉድ** ስ 1. የሚያሳዝን ወይም የሚያሳፍር፥ የሚያስደንቅ ድርጊት ወይም ሁኔታ። 2. ያልተለመደ፥ እንግዳና አስገራሚ ነገር። 3. መጥፎን ወይም ጥሩን ነገር ለማዳነቅ የሚነገር ቃል።

**ለጉድ የጎለተው** ችግር ወይም መከራ እንዲያይ እድሜው የረዘመ።

**ጉድ ሆነ** መጥፎ ነገር፥ ችግር፥... አጋጠመው።

**ጉድ ታየ** የሚያስገርም ወይም የሚያስደንቅ ነገር ታየ።

**ጉድ አወጣ** ምስጢርን ወይም የተደበቀን ነገር አወጣ፥ አጋለጠ።

**ጉድ አደረገው** 1. የሚጎዳ ነገር፥ ችግር፥... አደረሰበት። 2. አሞኘው ወይም አጭበረበረው።

**ጉድ ፈላ** ያልታሰበ ወይም ያልተጠበቀ ድንገተኛ ነገር ደረሰ።

**ጉደኛ** ቅ 1. ድርጊቱ ሁሉ አስገራሚ ወይም አስደናቂ የሆነ፥ተአምረኛ። 2. በጣም የሚያምር፥ ቆንጆ። *ጉደኛ ቤት ላለው።*

**ጉዳም** ቅ እንዳይታወቅበት የሚፈልገውና የሚሸሽገው ነገር ያለበት (ሰው)።

**ጉድኝ** ስ በደጋ አካባቢ ውሃማ በሆነ ቦታ ላይ የሚበቅልና የሚበሉትን እንስሳት ሊገድል የሚችል አነስተኛ የእፅዋት አይነት።

**ጉድጉድ**

**ጉድጉድ አለ** ግ 1. በቤት ውስጥ ወዲያ ወዲህ አለ(ምግብ ለማብሰል፥ለማቅረብ ወይም ቤት ለማዘጋጀት፥ ለማፅዳት፥... ወይም እቃን ለመፈለግ )። 2. በቤት ውስጥ ምግብ ሲያበስል ወይም እቃ ሲያዘጋጅ ወይም ሲፈልግ፥... የኮቴ ድምፅ አሰማ።

**ተንጎዳጎደ** ግ 1. ጉድጉድ አለ። 2.(ዘይ.) በድብቅ የግብረ ስጋ ግንኙነት ፈፀመ፤ ተልከሰከሰ።

**አንጎዳጎደ** ግ 1. የ"ጉድ ጉድ አለ"ን 2ኛ ፍቺ ተመ. 2.በድብቅ የግብረ ስጋ ግንኙነት ፈፀመ፤ተልከሰከሰ።:::

**ጉድለት** "ጎደለ" ስር ተመ

**ጉድባ** "ጎደበ" ስር ተመ.

**ጉድጓድ** "ጎደጎደ" ስር ተመ

**ጉድፍ** "ጎደፈ" ስር ተመ.

**ጉዶ** ስ እንደ ጎራዴ ያለ ሆኖ ከጎራዴ አጠር ያለ ያለ ማረጃ።

**ጉጉ** "ጓጓ" ስር ተመ.

**ጉጉት**[1] ስ ከብ ፊትና ትላልቅ አይኖች ያሉት፥ በቀን ብርሃን ማየት ስለማይችልና በጨለማ ጊዜ ብቻ የሚዘዋወር የአሞራ አይነት (ስእሉን አሞራ ስር ተመ.)።

**ጉጉት[2]** “ኳኳ” ስር ተመ.

**ጉጉማ** ስ መልኳ ቡሳና ነጭ የሆነ፥ የእግሯ ጣት እንደ ጃንጥላ ቅድ ሆኖ የተያያዘና በውሃ አጠገብ የምትኖር የአሞራ አይነት።

**ጉግስ** ስ አባራሪና ተባራሪ በመሆን ፈረሰኞች ዘንግ እየወረወሩ በመወጋጋትና በመመከት የሚጫወቱት የባህል ጨዋታ።

**ጉጠት** ስ 1. ብዙውን ጊዜ ብረት ቀጥቃጮች የጋለ ብረትን ለመያዝ የሚጠቀሙበት እንደ መቆንጠጫ ያለ መንታ ጫፍ ያለው ብረት። 2. ለመንቀያ ወይም ምስማርን ሰርስሮ ለማውጣት የሚያገለግል ጫፉ ቆልመም ያለ ብረት።

**ጉጥ** “*ጎጠጎጠ” ስር ተመ.

**ጉጥር** “ጎጠረ” ስር ተመ.

**ጉጭማ** ስ 1. እሳቂ (የዶማ)። 2.(ስድብ) ቁመቱም ሆነ አንገቱ አጭር የሆነና ወፈር ያለ ሰውነት ያለው (ሰው)።

**ጉፋያ** “ጎፈየ” ስር ተመ.


**ጉፍታ** ስ ብዙውን ጊዜ ሙስሊም ሴቶች ፀጉራቸውን እስከ አንገታቸው ድረስ የሚሸፍኑበት ሻሽ።

**ጉፍጥጥ** “ጎፈጠጠ” ስር “ጎፍጣጣ”ን ተመ.

**ጊ** የ”ገ” ፊደል ሳልስ ዘር።

**ጊርጊራ** “ግርግራ[1]”ን ተመ.

**ጊታር** ስ እንደክራር እየሙቱ የሚጫወቱበት የክር ዘመናዊ ሙዚቃ መሳሪያ(ስእሉን የሙዚቃ መሳሪያ ስር ተመ.)።



**ጊንጥ** ስ 1. በእንጨት ቅርፊትና በድንጋይ ስር የምትኖር፥ ጅራቷ ረዥም ሆኖ ክርክር ያለውና ተናዳፊ መርዘኛ ነፍሳት። ቅ 2. (ዘይ.) ክፉ፥ መርዘኛ።

**ጊዜ** ስ 1. ከአለፈው እስካሁን ያለው ወደፊትም የሚመጣው ሰኮንድ፥ ሰአት፥ ቀን፥ ሳምንት፥ ወር፥ አመት። 2.ከመምሸቱ ትንሽ ቀደም ብሎ ያለው ሰአት ወይም ወቅት። 3. አንድ ነገር የሚሆንበት ወይም የሚፈፀምበት ወይም የሚገኝበት ወይም የሚሰራበት ተገቢ ወቅት ወይም ሰአት። *ለሁሉም ጊዜ አለው።*

**ለጊዜው** ለአሁኑ፥ በቋሚነት ሳይሆን።

**በ___ ጊዜ ___** በነበረበት ወቅት፥ ዘመን። *በንጉሱ ጊዜ።*

**በየጊዜው** ዘወትር፥ ሁልጊዜ።

**በጊዜ** 1. ሰአቱ ከመድረሱ በፊት፥ ቀደም ብሎ። *ከቀጠሮው በታ በጊዜ ደረስሁ።* 2.በጣም ሳይመሽ። *ሳያመሽም ወደ ቤቱ በጊዜ ይገባል።*

**በጊዜው** በዘመኑ ፥ በሰአቱ ።

**ባለጊዜ** ቅ ወቅቱ የፈቀደለት ወይም የተመቻቸለት፥ ባለመብት።

**ከጊዜ ወደ ጊዜ** ከእለት ወደ እለት፥ ከቀን ወደቀን። *ከጊዜ ወደጊዜ ሁኔታው እየተቀየረ መጣ።*

**ያለጊዜው** ወቅቱ ወይም ሰአቱ ሳይፈቅድ ወይም ሳይደርስ።

**ጊዜ ሰጠ** 1. ታገሰ። 2. ሰአት በማራዘም ፋታ ሰጠ።

**ጊዜ አጠፋ** ያለአግባብ ጊዜ እንዲያልፍ ወይም እንዲያልቅ አደረገ።

**ጊዜ ወሰደ** ብዙ ሰአት ፈጀ፥ አቆየ።

**ጊዜ የለኝም** በስራ ወይም በሌላ ጉዳይ ስለተያዝኩ ተጨማሪ ነገር የማከናውንበት ሰአት የለኝም።

**ጊዜ የሰጠው** ባለጊዜ።

**ጊዜ የወለደው** ዘመን ያመጣው።

**ጊዜ ያለጊዜ** 1. በምሽት። 2. አመቺ ወይም ተስማሚ ባልሆነ ወቅት፤ አጉል ጊዜ።

**ጊዜ ያለፈበት** ዘመኑ ያለፈ ወይም ዘመናዊ ያልሆነ።

**ጊዜ ይቆጥባል** ብዙ ሰአት አይፈጅም፥ ይፈጥናል ወይም ያፈጥናል።

**ጊዜ ገዛ** ሰበብ ፈጥሮ ጊዜን በማራዘም አንድን ነገር ለማከናወን የሚያስችለውን ሁኔታ ፈጠረ ወይም አመቻቸ።

**ጊዜ ገደለ** ጊዜ አጠፋ።

**ጊዜ ጠበቀ** አመቺ ወይም ተስማሚ ጊዜ እስኪያገኝ ቆየ።

**የጊዜ ሰሌዳ** ስ ስራዎች የሚከናወኑበትን ሰአት ወይም ወቅት የሚጠቁም ሰንጠረዥ።

**ጊዜያዊ** ቅ ለአጭር ጊዜ የሚቆይ ወይም ቋሚ ያልሆነ።

**ጊዜያዊ ሰራተኛ** ስ 1. የሙከራ ጊዜውን ያልጨረሰ አዲስ ሰራተኛ።2.በቋሚነት ያልተቀጠረ ሰራተኛ።

**ጊደር** ስ ለመጠቃት የደረሰች እንስት የቀንድ ከብት።

**ጊድራ** ስ 1. ክፋት፥ ተንኮል። 2. ምቀኝነት።

**ጊድረኛ** ቅ ክፉ፥ ተንኮለኛ።

**ጊጋር** ስ እንደወረንጦ ያለ መቆንጠጫ(የአንጥረኛ እቃ)።

**ጊጤ** ስ ሹል ዘንግ ወይም ጦር፥... እየወረወሩ በመውጋት የውድድር ጨዋታ የሚያደርጉበት የእንዶድ ወይም የሬት ግንድ፤ ጨዋታውም ጊጤ

እየተባለ ይጠራል።

**ጋ**[1] የ'ገ' ፊደል ራብእ ዘር።

**ጋ**[2] በስምና በተውላጠስም መጨረሻ እየገባ በታን፥ በ___ አጠገብ መገኘትን፥ ወይም አንድ ነገር የት እንደሚገኝ የሚያመለክት ቃል። *ጠረጴዛው ጋ /ሹሉ ጋ /* እዚያጋ።

**ጋ**[3]

**ጋ አለ** ግ የመጋጨት ድምፅ አሰማ፤ ጓ አለ።

**ጋለ** ግ 1. ሞቀ፥ተከሰ፥ ጠበረረ። 2. ደመቀ፥ ሞቀ። *ወዋታው ጋለ።*

**ግለት** ስ ሙቀት፥ ትኩሳት፥ ግመት።

**ጋል ጋል አለ** ግ ቆጣ ቆጣ አለ።

**ተጋጋለ** ግ ተሟሟቀ (ወሬ፥ጥል፥ ክርክር፥...)።

**አጋጋለ** ግ አሟሟቀ፥ አጻመቀ፥ አባባሰ (ወሬን፥ጥልን፥ክርክርን)።

***ጋለለ**

**ጋለል አለ** ግ ከአንገትና ከትከሻው ወደ ኋላ ዘንበል፥ ደገፍ ብሎ ተኛ፥ ጋደም አለ።

**ጋለል አደረገ** ግ አንጋለለ።

**ተንጋለለ** ግ በጀርባው ተኛ፥ ተጋደመ።

**አንጋለለ** ግ በጀርባው አስተኛ፥ አጋደመ።

**እንግሊላ(እንግላል)** ስ የጀርባ መኝታ።

**ጋለሎ** "*ገለለ" ስር "ግላሎ"ን ተመ.

**ጋለሞታ** "ገለሞተ" ስር ተመ.

**ጋለበ** ግ 1. በፈረስ ላይ ተቀምጦ በግልቢያ ሄደ። 2. እየፈጠነ፥ እየሮጠ ሄደ። 3. ጠለቅ ብሎ ወይም በደንብ ሳይሆን ላይ ላዩን በጥድፊያ አነበበ፥ አየ፥...።

**ግልቢያ** ስ 1. የፈረስ ሩጫ ወይም በሚሮጥ ፈረስ ላይ ተቀምጦ የሚደረግ የፍጥነት ጉዞ።

**ጋመ** ግ1. ጋለ፥ ተከሰ(ሸክላ፥ብረት፥..)። 2.ፋመ።

**ግመት** ስ ግለት፥ ሙቀት።

**ተጋጋመ** ግ ተፋፋመ፥ ተያያዘ (እሳት፥ ጦርነት፥...)።

**አጋጋመ** ግ አሟሟቀ፥ አባባሰ፥ አቀጣጣለ (እሳትን፥ ጦርነትን፥...)

**ጋመረ** ግ አደገ፥ ጎረመሰ።

**ጋመረች** ግ ለአካለ መጠን ደረሰች።

**ጋሙድ** ስ ረሃብ።

**ጋሙዳ** ቅ ረሃብተኛ።

**ጋማ** ስ የበቅሎ፥ የፈረስ፥ የአንበሳ፥... የማጅራት ፀጉር።

**የጋማ ከብት** ስ እንደ ፈረስ፥ በቅሎ፥ አህያ ያሉት የቤት እንስሳት የወል መጠሪያ ስም።

**ጋሜ** ስ 1. መሃሉ ተላጭቶ ዙሪያውን የሚቀር የሴት ልጅ ፀጉር (ስእሉን የፀጉር አሰራር ስር ተመ.)። 2.ጎንና ጎኑ ተላጭቶ ከግንባሩ እስከ ማጅራቱ ድረስ የሚቀር የወንድ ልጅ ፀጉር(ስእሉን የፀጉር አሰራር ስር ተመ.)። 3. ለአካለ መጠን ያልደረሰች ወይም ያልደረሰ ልጅ።

**ጋምቤሎ(ገምቤሎ)** ስ የዛፍ አይነት።

**ጋረ** ግ ጣረ፥ ለፋ፥ ደከመ።

**ጋረደ** ግ 1. ሸፈነ፥ ከለለ። 2. ማየት ከለከለ። *ዓይኑን ጋረደው።*

**መጋረጃ** ስ መስኮት፥ በር፥... ላይ የሚዘረጋ ጨርቅ (ለመከለያ ወይም ለጌጥ)።

**መጋረጃ ተጣለ** መጋረጃ ተጋረደ።

**ግርዶሽ(ግርጃ)** ስ መከለያ ወይም ከለላ።

**ጋረጠ** ግ 1. ቧጨረ፥ ቀደደ (መተላለፊያ ላይ ያለ ሹል ነገር፥ እሾክ፥...)። 2. ደነቀረ፥ መተላለፊያ ዘጋ፥ አወከ። 3. ሰካ፥ ተከለ።

**ጋሬጣ** ስ 1. እንደ እንጨት ስንጣሪ ወይም እሾክ ያለ ነገር። 2. እንቅፋት ወይም መሰናክል።

**ተጋረጠ** ግ 1. ፊት ለፊት በመቆም ለማየት ወይም ለመሄድ ከለከለ። 2. እንቅፋት ወይም መሰናክል ሆነ። 3. ተሰካ፥ ተተከለ።

**ጋሪ** ስ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ተሽከርካሪ ጎማዎች ያሉት በፈረስ ወይም በበቅሎ የሚጎተት መጓጓዣ።



ጋሪ

**ጋሪ ነጂ** ስ ጋሪ የሚነዳ ሰው።

**ጋሪያት** ስ የቀጡነት፥ የብስጩነት፥ የሞገደኝነት፥... ባህርይ።

**ጋሪያታም** ቅ ቁጡ፥ ብስጩ፥ ሞገደኛ፥ እልከኛ።

**ጋራ**[1] ስ ተራራ

**ጋራማ** ቅ ተራራማ።

**ጋራ**[2] "ጋር" ን ተመ.

***ጋራ**

**የጋራ** ቅ ከአንድ በላይ ባለቤት ያለው፥ የግል ያልሆነ፥ የወል። *ሃብቱ የጋራችን ነው /የጋራ ንብረት ላለን።*

**የጋራ መግለጫ** ስ መንግስታት፥ የፖለቲካ

ድርጅቶች፥... በተለያዩ ጉዳዮች ላይ አንድ አቋም በመውሰድ ይፋ የሚያወጡት መግለጫ።

**የጋራ ስምምነት** ስ ሁሉንም ወገኖች ሊጠቅም በሚችል ጉዳይ ላይ ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ ወገኖች የሚፈራረሙት ውል።

**የጋራ ድንበር** ስ የተለያዩ ሃገሮችን የሚያዋስን ቦታ።

**ተጋራ** ግ ተካፈለ። *የተገኘውን ትርፍ ከወንድሙ ጋር ተጋራ።*

**አጋራ** ግ አካፈለ።

**ጋራሚ** "ጋራ[1]" ስር ተመ.

**ጋራዥ** ስ የተለያዩ ተሽከርካሪዎች የሚታደሱበት ወይም የሚጠገኑበት ቦታ፥ ድርጅት።

**ጋሬ** ስ ዘንጋዳ፥ ገብስ፥ ስንዴ፥... በመቀላቀል የሚዘጋጅና ብዙውን ጊዜ ከጤፍ እንጀራ ስር የሚጎዘጎዝ ወፍራም እንጀራ።

**ጋሬጣ** "ጋረጠ" ስር ተመ.

**ጋር (ጋራ)** ከ" ከ-" በመጣመር "አብሮ" የሚለውን ሃሳብ የሚገልፅ ቃል። *ከአበባ ጋር ሄደ ።*

**ጋሸበ** ከተገቢው በላይ በጣም አድጎ ወይም በዝቶ ተጋደመ ፥ ወደቀ(የተዘራ እህል)።

**ግሸበት** "ዋጋ" ስር "የዋጋ ግሸበት"ን ተመ.

**ጋሻ[1]** ስ 1. ከጎሽ ወይም ከዝሆን ወይም ከጉማሬ ወይም ከበሬ ቆዳ የሚሰራ፥ ብዙውን ጊዜ ክብ የሆነ ቅርፅ የሚኖረውና ከውስጥ በኩል የእጅ ማስገቢያ ወይም ማንገቻ ያለው፥ በውጊያ ጊዜ ለጦር ወይም ለጎራዴ፥... መመከቻ በእጅ የሚያዝ የጦር እቃ። 2. (ዘይ.) መመኪያ፥ አለኝታ።



ጋሻ 1ኛ ፍቺ

**ጋሻ ጃግሬ** ስ የጦር መሳሪያ ተሸክሞ ጌታውን የሚከተል አሽከር።

**ጋሻ ሰጓጅ** ስ ጋሻ የሚሰራ ባለሙያ።

**ጋሻ[2]** ስ የመሬት ስፋት መለኪያ(አንድ ጋሻ መሬት አርባ ሄክታር ነው)።

**ጋሼ** ስ በእድሜ አነስ የሚል ሰው በእድሜ የሚበልጠውን ወንድ የሚጠራበት የአክብሮት ስም።

**ጋበን[1]** ስ ሩር ወይም ጥንግ።

**ጋበን[2]** ስ ወበቅ።

**ጋበዘ** ግ 1. በማብላት ወይም በማጠጣት አስተናገደ። 2. በአንድ ነገር ላይ እንዲሳተፍ ወይም አንድን ነገር (ቲያትር፥ሲኒማ፥...) እንዲመለከት ወሰደ፥ ጠራ።3. ሳበ፣ ገፋፋ። *ፊቷ ይጋብዛል /ለጠብ የጋበዘኝ እሱ ነው።*

**ግብዣ** ስ 1. የመብልና የመጠጥ መስተንግዶ። 2. አንድን ነገር እንዲመለከቱ ወይም አንድ ነገር ላይ እንዲሳተፉ የሚቀርብ ጥሪ ወይም ጥያቄ።

**የግብዣ ወረቀት** ስ የጥሪ ወረቀት።

**ተጋበዘ** ግ 1. ግብዣ ተጠራ ተደረገለት። 2. ልማታ ወይም ልደባደብ አለ፣ ተገለገለ።

**ተጋባዥ** ቅ ግብዣ የተደረገለት(እንግዳ)።

**ጋቢ** ስ በወፍራሙ የተፈተለ ጥንድ ነጠላ በአንድ ላይ ተሰፍቶ የሚዘጋጅና ከላይ የሚለበስ ወፍራም ሸማ።

**ጋቤጣ** ስ 1. ከኒኬል የሚሰራ ኩባያ የሚመስል የውሃ መጠጫ እቃ። 2. ከኒኬል የሚሰራና ብዙውን ጊዜ ለቅቤና ለወተት መያዣ የሚያገለግል ባለማንጠልጠያ እቃ።

**ጋብ**

**ጋብ አለ** ግ በረድ ወይም ቀነስ አለ። *ጫጫታው ጋብ አለ/ዝናቡ ጋብ አለ።*

**ጋብቻ** "ገባ" ስር ተመ.

**ጋተ** ግ በግድ ይዞ አጠጣ።

**አጋተ** ዝ.ከ.

**ተጋተ** ግ በብዛት ጠጣ።

***ጋተ**

**ግት** ስ ወተት በብዛት ቋጥሮ ወይም አጠራቅሞ የያዘ የላም፥የፍየል፥ የበግ፥... ጡት።

**አጋተ** ግ ወተት በብዛት ያዘ(ጡት)።

**ጋት** ስ የእጅ ጣቶች በመደዳ ሲቀመጡ ከትንሿ ጣት እስከ ሌባ ጣት ድረስ ያለው ስፋት ወይም የክንድ አንድ ስድስተኛውን ያህል የሚሆን ርዝመት።

**ጋኔን(ጋኔል)(ብ.ቁ.አጋንንት)** ስ 1. ሰይጣን፥ ርኩስ መንፈስ። ቅ 2. (ዘይ.) ክፉ፥ ርኩስ።

**ጋኔን አደረበት** ርኩስ መንፈስ ያዘው።

**ጋኔን ሳታች** ስ በድግምት ጋኔን የሚጠራ አስማተኛ።

**ጋኔናም** ቅ (ዘይ.) ተናዳጅ፥ ቁጡ።

**ጋን** ስ 1. ከሸክላ የሚሰራ የጠጅ ወይም የጠላ መጥመቂያ። 2. የ"ውሃ ጋን" ን፥ "ኤሌክትሪክ ጋን"ን ተመ.

**ጋን ጋን አለ** ግ አፉ ጠላ ጠላ ወይም ጠጅ ጠጅ ሸተተ።

**የጋን መብራት** ስ እውቀቱንና ችሎታውን

ለሌሎች ያላስተላለፈ፥ ያላስተማረ፥ ሌሎች እንዲጠቀሙበት ያላደረገ ሰው፡፡

**ጋንድያ** ስ 1. ትልቅ፥ ጠረንገሎ፡፡ 2. (ስድብ) መኻታ የሚያበዛ ወይም ሰነፍ፡፡

**ጋንጃ** ስ ማጅራት፡፡

**ጋንጢጥ** ስ (ስድብ) ያልተቀጣ፥ ባለጌ፡፡

**ጋንጩር** ስ 1. ጋኔን፥ ሰይጣን፡፡ 2. (ስድብ) ሰይጣናም፡፡

***ጋዘ[1]**

**ተጋዘ** ግ አንድ እቃ ከቦታ ወደ ቦታ ተወሰደ ወይም ተጓጓዘ፡፡

**አጋዘ** ግ እቃን ከቦታ ወደቦታ ወሰደ ወይም አጓጓዘ፡፡

***ጋዘ[2]**

**ግዞት** ስ አንድን ሰው ከሚኖርበት አካባቢ አንስቶ ወደ ሌላ አካባቢ በመውሰድና በዚያው ቦታ ብቻ ተወስኖ እንዲቆይ የሚደረግበት የእስራት አይነት፡፡

**ግዞተኛ** ቅ በግዞት ላይ ያለ (ሰው)፡፡

**ተጋዘ** ግ በግዞት እንዲቀመጥ ተደረገ፡፡

**አጋዘ** ግ በግዞት አስቀመጠ፡፡

**ጋዘና** ስ ከቀርከሃ የሚሰራና ለእንጀራ ማስቀመጫ የሚያገለግል እቃ፡፡

**ጋዜጣ** ስ የተለያዩ ዜናዎች፥ ማስታወቂያዎች፥... በየቀኑ ወይም በየወሩ ወይም በሌላ የተወሰነ ጊዜ ታትመው የሚወጡበት ወረቀት፡፡

**ጋዜጠኛ** ስ ዜናን ወይም ሌሎች ፕሮግራሞችን ለመገናኛ ብዙሃን የሚያጠናቅር፥ የሚያዘጋጅና መረጃን ለህዝብ የሚያቀርብ ባለሙያ፡፡

**ጋዜጣዊ መግለጫ** "ፕሬስ ኮንፈረስ"ን ተመ.

**ጋዝ** ስ 1. ወደ ፈሳሽነት ወይም ጠጣርነት ለመለወጥ የሚያበቃው የሙቀት ወይም የቅዝቃዜ መጠን ካላገኘ በስተቀር እንደ አየር ሆኖ የሚገኝ ንጠረ ነገር፡፡ 2. ለመብራት፥ ለማብሰያ፥... የሚያገለግል ነዳጅ፡፡

**ጋዝ ጋዝ አለ** ቸከ፥ ተሰለቸ፡፡

**ጋገ** ስ የሳር አይነት፡፡

**ጋየ** ግ ነደደ፥ ተቃጠለ፡፡

**ጋይ** ስ ጥሩ ሰብል ሊይዝ ይችላል በሚል እምነት የእርሻን አፈርና ጓል እየቆለሉ በእሳት የማጋል ወይም የማቃጠል ድርጊት፡፡

**አጋየ** ግ አነደደ፥ አቃጠለ፡፡

**ጋዱ** ስ ወንበዴ፥ ቀማኛ፡፡

**ጋዲ** ስ በቀንድ ከብቶች የሂላ እግር ላይ ከጭን በታች ከጉልበት ግጠፈያ በስተሂላ በኩል የሚገኝና ላም በምትታለብበት ጊዜ ማሰሪያው (የጋዲ ጠፍር) የሚውለበት ቦታ፡፡

**ጋዲ [ጠፍር]** ስ ላም በምትታለብበት ጊዜ ወዲያና ወዲህ እንዳትል በእግሯ ላይ የሚታሰር ጠፍር፡፡

**ጋድ(ገሃድ)** ስ በገና ወይም በጥምቀት በአል ዋዜማ የሚውል የፆም ቀን፡፡

**ጋድሚያ** "*ገደመ" ስር ተመ

**ጋድም** ዝ.ከ.

**ጋገረ** ግ የእንጀራን፥ የዳቦን፥... ሊጥ በሰግ ምጣድ ላይ አስፈቶ፥ ጠፍጥፎ በማብሰል እንጀራ፥ ዳቦ፥... አዘጋጀ፡፡

**ጋጋሪ(እንጀራ ጋጋሪ)** ስ መተዳደሪያዋ እንጀራ ለሌሎች ሰዎች መጋገር የሆነ ሴት፡፡

**ጋጋ** ግ መታ ወይም አጮለ፡፡ *በጥፊ ጋጋው፡፡*

***ጋጋ**

**ጋጋታ** ስ ትርምስ፥ ግርግር፡፡

**ተንጋጋ** ግ በብዛት ግር ብሎ ሄደ፡፡

**አንጋጋ** ግ በብዛት አመጣ ወይም ወሰደ፡፡

**ጋጋሪ** "ጋገረ" ስር ተመ.

**ጋጋታ** "*ጋጋ" ስር ተመ.

**ጋጋኖ** ስ አንገቱ ላይ ሁለት እንጥልጥል ያለው፥ በውሃ አካባቢ የሚገኝ፥ ሲጮህ አስደንጋጭ ድምፅ የሚያሰማና የወንዝ አሞቴ የሚመስል የአሞራ አይነት (በእሉን አሞራ ስር ተመ.)፡፡

**ጋግርት** ስ 1. አይንን የሚያስፈጥጥና ዝም የሚያሰኝ ወይም ንግግር የሚያስጠላ ህመም፡፡ 2. ከሰው ተለይቶና ዝም ብሎ ለብቻ የመቀመጥ ባህርይ ወይም ጠባይ፡፡

**ጋግርት አለባት** ወንድ የሚያስጠላ በሽታ አለባት (ወንድ እንዲጠጋት አትፈልግም)፡፡

**ጋግርታም** ቅ 1. ጋግርት ያለበት፡፡ 2. ከሰው ጋር ተቀላቅሎ መቀመጥ፥ መጫወት፥... የማይወድ፡፡ 3. እምቢ ወይም እሺ ፈረኝ ካለ የማይመለስ፥ በጣም እልህኛና ንዴተኛ የሆነ፡፡

**ጋጠ** ግ 1. በጥርሱ እየነጨ፥ እየገሸለጠ ወይም እየላጠ በላ፡፡ *ሳር ጋጠ /አጥንት ጋጠ፡፡* 2. አግ፡፡ *ሰው ሲግጡ ነው የሚውሉት፡፡*

**ግጠህ** ውጣው ችግርህን እራስህ ታግለህ ተወጣው፡፡

**ግጦሽ** ስ በሜዳ ላይ የሚገኝና ከብቶች የሚግጡት ሳር፡፡

**ተጋጋጠ** ግ ብዙ ቦታ ላይ ተላላጠ ወይም ተገሸላለጠ፡፡

**አጋጠ** ግ ከብቶችን ወደ ግጦሽ አሰማርቶ ሳር እንዲበሉ አደረገ፡፡

**ጋጠረ** ግ ጣረ፥ጋረ፥ለፋ።

**አጋጠረ** ግ 1. ጋጠረ። 2.አለፋ፥ አደከመ።

**ጋጠጠ** ግ ሟጠጠ፥ ምንም ሳያስቀር ሙልጭ አድርጎና ከስሩ ቆርጦ አነሳ፥ አጨደ።

**ጋጥ(ጋጣ)** ስ የበቅሎ፥ የፈረስ፥ የአህያ ፥... ማደሪያ ቤት።

**ጋጠወጥ** ቅ (ስድብ) ስነስርአት የሌለው፥ መረን፥ ባለጌ።

**ጋፈ** ግ 1. አፈሰ፥ ጠረገ። 2. (ዘይ.) በብዛት ጠጣ (ጠጅን፥ ጠላን፥..)።

**መጋፊያ** ስ 1. ብራኳ። 2. ለአሻሮ ማንኮሪያ የሚሆን የብራኳ አጥንት ወይም በብራኳ አጥንት ቅርፅ ከብረት ወይም ከእንጨት ተሰርቶ ለተመሳሳይ አገልግሎት የሚውል እቃ።

***ጋፈጠ**

**ተጋፈጠ** ግ 1. ተጋለጠ። 2. በአንድ ጉዳይ፥ ስራ፥... ላይ እውቀቱን፥ ጉልበቱን፥....ሳይቆጥብ ሙሉ በሙሉ ተሳተፈ ወይም ሰራ።

**አጋፈጠ** ግ አጋለጠ፥ አሳልፎ ሰጠ።

**ጋፈፈ** ግ በብዛት ሰበሰበ፥ አግበሰበሰ።

**አጋፈፈ** ዝ.ክ.

**ጋፊኛ** ስ የተገላቢጦሽ። *እኔ በተበደልኩ ጋፊኛ እሱ ላከረፈኝ።*

**ጋፍ** ቅ ሞኝ፥ ቂል።

**ጌ** የ"ገ" ፊደል ሃምስ ዘር።

**ጌሾ** ስ ቅጠሉና እንጨቱ እየተወቀጠ ወይም እየተቀቀለ ለጠላና ለጠጅ መጥመቂያ የሚሆን፥ መረር ያለ ጣእም ያላው የተክል አይነት።

**ጌታ** ስ 1. ሃብታም፥ ባለፀጋ። 2. አምላክ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ። 3. ባለቤት። *የቤቱ ጌታ ማነው?* 4. አለቃ፥ የበላይ።

**ለጌታ አደረ** ለሃብታም አሽከር ወይም ሎሌ ሆነ፤ የጌታ አደረም ይባላል።

**ጌቶች** (በቅርፁ ብ.ቁ. ቢመስልም የሚያገለግለው በነ.ጠቁ. ነው) በአብዛኛው አሽከሮች ወንድ ቀጣሪያቸውን በአክብሮት ለመጥራት የሚጠቀሙበት ቃል።

**ጌኛ** ስ መጋዣ፥ ለእቃ ማጓጓዣነት የሚያገለግል ፈረስ።

**ጌጠኛ** "*ገየጠ" ስር ተመ.

**ጌጣጌጥ** ዝ.ክ.

**ጌጥ** ዝ.ክ.

**ግ** የ"ገ" ፊደል ሳድስ ዘር።

**ግሁስ** ስ ባህታዊ፥ መናኝ።

**ግለሂስ** "ግል" ስር ተመ.

**ግለሰብ** ዝ.ክ.

**ግለት** "ጋለ" ስር ተመ.

**ግለኛ** "ግል" ስር ተመ.

**ግላሎ** "*ገለለ" ስር ተመ.

**ግላስ** ስ ከሃር ወይም ከግምጃ፥..የተሰራ የኮርቻ ልብስ

**ግላዊ** "ግል" ስር ተመ.

**ግላጭ** "ገለጠ" ስር ተመ.

**ግል**

**የግል** ቅ 1. የራስ፥ የብቻ። 2. የመንግስት ይዞታ ያልሆነ።

**የግል ማህደር** ስ በመስሪያ ቤት ውስጥ የአንድን ሰው የህይወት ታሪክ፥ የትምህርት ማስረጃ፥ የስራ አፈፃፀም፥... የያዙ ሰነዶች በአንድ ላይ የሚገኙበት ማህደር፤ ፋይል ።

**ግለሂስ** ስ ስህተትን ወይም ጥፋትን አምኖ በመቀበል በገዛ ራስ ላይ ሂስ ማካሄድና ራስን በራስ መውቀስ፥ መተቸት።

**ግለሂስ አደረገ /አካሄደ** እራሱን በራሱ ወቀሰ (በስብሰባ ላይ)።

**ግለሰብ** ስ አንድ ሰው።

**ግለኛ** ቅ 1. ብቸኛ። 2. ለራሱ ብቻ የሚያደላ።

**ግላዊ** ቅ የግል።

**ግልሙትና** "ገለሞተ" ስር ተመ.

**ግልምቢጥ(ግርምቢጥ)** የተገላቢጦሽ።

**ግልምጫ** "ገላመጠ" ስር ተመ.

**ግልቢያ** "ጋለበ" ስር ተመ.

**ግልባጭ** "ገለበጠ" ስር ተመ.

**ግልብ** "ገለበ$^{2}$" ስር ተመ.

**ግልብልብ** "*ገለበለበ" ስር ተመ.

**ግልብጥ** "ገለበጠ" ስር ተመ.

**ግልቱ** "*ገለታ" ስር ተመ.

**ግልየት** ስ በዕሁፍ ዳርና ዳር እንዲሁም በመሃል ከጥራዙ ግራና ቀኝ ያለው ያልተፃፈበት ቦታ።

**ግልድም** "*ገለደመ" ስር ተመ.

**ግልድሞሽ** ዝ.ክ.

**ግልድው**

**ግልድው አለ** ግ ወደቀ፥ ተኛ፥ ተጋደመ።

**ግልድው አደረገ** ግ ጣለ፥ አጋደመ፥ አስተኛ።

**ግልገል** ስ የበግ ፥ የፍየል ፥ የድመት፥... ያልጠነከረ ልጅ።

**ግልገል ሙሴ** ስ የፅዋ ማህበረተኞች ምክትል አለቃ፥ አስተናባሪ።

**ግልገል ሙቀጫ** ስ ዘነዘና ፣ የሙቀጫ ልጅ።

**ግልገል ሚዜ** ስ ከዋናው ወይም ከአንደኛው ሚዜ ቀጠሎ ያለ ምክትል ሚዜ።

**ግልገል ሞራ** ስ ከወተት አንጀት ጋር የሚገኝ ሞራ ወይም ስብ።

**ግልገል ሰኮና (ሸኮና)** ስ ከሰኮና(ሸኮና) በላይ ያለ የእንስሳት ትንሽ ጥፍር፥ ጉጥ።

**ግልገል አንሳ** ስ የሉስ፤ ትልቅ አሞራ።

**ግልጋሎት** "*ገለገለ" ስር ተመ.

**ግልግል** "ገላገለ" ስር ተመ.

**ግልጥ** " ገለጠ" ስር "ግልፅ" ን ተመ.

**ግልፅ** "ገለጠ" ስር ተመ.

**ግልፋፊ** "ገለፈፈ" ስር ተመ.

**ግልፍ**

**ግልፍታ** ስ ቁጣ፥ ንዴት፥ ብስጭት፤ በቀላልና በትንሽ ነገር ምክንያት ቶሎ ቱግ ማለት።

**ግልፍተኛ** ቅ በትንሹ ነገር ቶሎ የሚቆጣ።

**ግልፍ አለው** ግ ድንገት ተቆጣ።

**ግልፍጥ** "ገለፈጠ" ስር ተመ.

**ግልፍፍ** "ገለፈፈ" ስር ተመ.

**ግመል** ስ ቀመቱና አንገቱ ረዥም፥ በበረሃማ ቦታ የሚኖር፥ ውሃ ጥም ቻይ የሆነና ሻኛ ያለው የቤት እንስሳ(ስእሉን የቤት እንስሳ ስር ተመ.)።

**የግመል ሽንት** (ዘይ.) በቃሉ የማይረጋ፥ ተንሸራታች።

**ግመሬ** "ገመረ" ስር "ገመሬ"ን ተመ.

**ግመት** "ጋመ" ስር ተመ.

**ግማሽ** "ገመሰ" ስር ተመ.

**ግማታም** "ገማ" ስር ተመ.

**ግማት** ዝ.ከ.

**ግም** ዝ.ከ.

**ግቕም**

**ግቕም አለ** ግ 1. ጀመረ፥ ገባ(ክረምት)። *ሃምሌ ገም ሲል።* 2. እንደ መድፍ ያለ መሳሪያ ሲተኮስ የሚያሰማውን አይነት ድምፅ አሰማ።

**ግምል** "ገመለ" ስር ተመ.

**ግምበኛ** "ገነባ" ስር "ግንበኛ"ን ተመ.

**ግምባር** "ግንባር"ን ተመ.

**ግምባታ** "ገነባ" ስር "ግንባታ"ን ተመ.

**ግምብ** "ገነባ ስር" "ግንብ"ን ተመ.

**ግምት** "ገመተ" ስር ተመ.

**ግምጃ** ስ ቀይ ሱቲ።

**ግምጃ ቤት** ስ 1. የመስሪያ ቤት፥ የድርጅት፥... ንብረት ወይም ገንዘብ ማስቀመጫ ቤት። 2. የግምጃ ቤት ሃላፊ።

**ግምገማ** "ገመገመ" ስር ተመ.

**ግረን** ስ ላም ስትወልድ መጀመሪያ የሚታለበው ቀይ መሳይ የሆነ ወፍራም ወተት፤ እንገር።

**ግሩም** "ገረመ[2]" ስር ተመ.

**ግሪሳ** ስ ብዙ ሆኖ የሚሄድና በማሳ ላይ ያለን እህል በመብላት ከፍተኛ ጥፋት የሚያደርስ የወፍ አይነት።

**ግራ** ስ 1. የቀኝ ተቃራኒ (አንድ ሰው ፊቱን ወደ ፀሃይ መውጫ ሲያደርግ በስተሰሜን በኩል የሚገኘው የሰውነት ክፍል ወይም ቦታ። 2. ቀና ያልሆነ፥ ጠማማ።

**ግራ ገባው** 1. ተደናገረ፥ ግር አለው። 2. ተጨነቀ።

**ግራ አጋባ** አደናገረ፥ አወከ።

**የግራ ዳኛ** ስ በችሎት ላይ ሆነው ፍርድ በሚሰጡበት ጊዜ ከመሃል ዳኛው በስተግራ በኩል የሚቀመጥ ዳኛ።

**ግራ ቀኝ ተመለከተ** 1.በሁለት ተቃራኒ ወገኖች ወይም ባለ ጉዳዮች መካከል ሆኖ ሁለቱም የሚሉትን አዳመጠ ወይም ተመለከተ (ውሳኔ፥ ፍርድ፥...ለመስጠት)። 2. ረጋ ብሎ ወደ ቀኝም ወደ ግራም ልብ አድርጎ አየ ወይም አስተዋለ።

**ግራ አዝማች** ቅ በግራ በኩል ያለውን ጦር ለሚያዘምት የጦር አለቃ ይሰጥ የነበረ ማእረግ።

**ግራ እጅ** ስ በስተግራ በኩል የሚገኘው የሰው አንደኛው እጅ።

**ግራ ክንፍ** ስ ሶሻሊሲታዊ ወይም ኮሚኒስታዊ አመለካከትያለው የፖለቲካ ጎራ፥ ቡድን፥...።

**ግራ ወንበር** ስ የግራ ዳኛ።

**ግራ ጌታ** ስ (ቤ.ክህ.) በቅኔ ማህሌት ላይ የቤተ ክርስቲያኑ አስተዳደሪ(አለቃ) ከሚቆምበት በስተግራ በኩል የሚቆም፥ ማእረጉ ከቀኝ ጌታው ዝቅ ያለ የመዘምራን አለቃ።

**ግራኝ** ቅ በግራ እጁ የሚበላ፥የሚሰራ፥...።

**ግራማፎን** ስ የሸክላ ማጫወቻ መሳሪያ።

**ግራም** ስ የክብደት መለኪያ (1/1000 ኪሎ ግራም የሚመዝን)።

**ግራምጣ** ስ በቆላና በወይናደጋ በረግረግ ውስጥ የሚበቅልና ለስፌት ስራ የሚያገለግል፥ ግንዱ አራት ማእዘንነት ያለውና እንደ ቄጠማ ወፍራም የሆነ የሳር አይነት።

**ግራር** ስ እሾህ ያለው፥ ልጡ ጠንካራ የሆነና በብዛት በሞቃት አካባቢ የሚበቅል የዛፍ አይነት።

**ግራሶ** ስ ብሎኖች፥ የብረት ጥርሶች፥... እንዳይዝጉና እንዳይጣበቁ ለማለስለሻነት የሚያገለግል ወፍራም ቅባት።

**ግራት** "ገራ[1]" ስር ተመ.


**ግራኝ** "ግራ" ስር ተመ.

**ግራዋ** ስ ቅጠሉ እንደጋን፥ እንስራ ላሉ የጠላ መጥመቂያ እቃዎች በማጠቢያነት የሚያገለግል መራራነት ያለው የእፅዋት አይነት።

**ግራዋ ግራዋ አለ** ጣእሙ መረረ።

**ግራጫ** ቅ በነጭና በጥቁር መካከል ያለ አመድማ የቀለም አይነት።

**ግራፍ** ስ የአንድን ነገር መጠን፥ እድገት፥... የመሳሰሉትን ለማሳየት በወረቀት ላይ የሚሳሉ፥ ቀጥታ ወይም ቀጥታ ያልሆኑና አንድ ወይም ከአንድ በላይ ፣ሁኑ መስመራዊ ምልክቶች።



ግራፍ

**ግሬራ** ስ ለወተት ማለቢያ የሚያገለግል ከስፌት ወይም ከቅል የሚዘጋጅ ጮጮ ወይም እኮሌ።

**ግር** "ገራ[1]" ስር ተመ

**ግር̈**

**ግር̈ አለ** ግ ተደናገረ፥ ተምታታ።

**ግርማ** ስ 1. ሞገስ፥ ክብር። 2. ግርማ ሞገስ። *ሲያዩት ግርማው ያስፈራል።*

**ግርማ ሞገስ** ስ በተፈጥሮ የሚታደሉት የመፈራትና የመከበር ፀጋ።

**ግርማዊ** (አን. ፆታ **ግርማዊት**) ቅ የንጉስ የአክብሮት መጠሪያ ።

**ግርምቡድ(ግርንቡድ)** ስ 1. ለመቀመጫነት የሚያገለግል የግንድ ጉራጅ 2. በርጩማ።

**ግርምቢጥ (ግርንቢጥ)** "**ግልምቢጥ**"ን ተመ.

**ግርሻ** "ገረሸ" ስር ተመ.

**ግርንቡድ** "**ግርምቡድ**"ን ተመ.

**ግርንቢጥ** "**ግርምቢጥ**"ን ተመ.

**ግርንድስ** (ስድብ) እንቅልፍ የሚያበዛ ወይም ተጋድሞ የሚውል።

**ግርንግሪት** ስ ሁለት እጅን ወደሂላ በማድረግ የሚታሰር የእስር አይነት ፤ ፊጥኝ።

**የግርንግሪት ታሰረ** የፊጥኝ ታሰረ።

**ግርዘት** "ገረዘ" ስር ተመ.

**ግርዝ** ዝ.ከ.

**ግርድ** ስ አውድማ ላይ ምርቱ(ፍሬው) ከገለባ በሚለይበት ጊዜ ከዋናው ምርት ውስጥ እየተንገዋለለ የሚወገድ የእህል ፍሬ ስብርባሪ፤ በደንብ ፍሬ ያልያዘና በእንቡጥነት የቀረ እንጭጭ፥ ብጣሪ፥ ንፋሽ፥... ያለበትና ደረጃው ዝቅተኛ የሆነ የምርት ክፍል።

**ግርድና** "ገረደ" ስር ተመ.

**ግርድፍ** "ገረደፈ" ስር ተመ.

**ግርዶሽ** "ጋረደ" ስር ተመ.

**ግርጃ** "ጋረደ" ስር "**ግርዶሽ**"ን ተመ

**ግርጌ** ስ 1. በመኝታ ጊዜ እግር የሚውልበት ቦታ። 2. በታች፥ ስር። *ቤቱ ከተራራው ግርጌ ነው።*

**ግርግም** ስ ከድንጋይ ወይም ከእንጨት የሚሰራ የከብቶች መኖ መብሊያ ወይም መመገቢያ።

**ግርግራ[1] (ጊርጊራ)** ስ ከሸክላ ወ.ይም ከቆርቆሮ፥... የሚሰራ የእጣን ማጨሻ እቃ (ስእሉን የሸክላ እቃ ስር ተመ.)።

**ግርግራ[2]** ስ ሲታረስ የሚያስቸግር ጭንጫ መሬት።

**ግርግራት** ስ ሴቶች እንደ ብርጉድ የመሳሰሉ ጥሩ መአዛ ያላቸውን የእፅዋት ጢስ የሚታጠኑበት፥ እንደ ዕዋ ያለ እግር ያለው የሸክላ እቃ።

**ግርፊያ** "ገረፈ" ስር ተመ.

**ግርፋት** ዝ.ከ.

**ግርፍ** ዝ.ከ.

**ግሮሰሪ** ስ 1. መጠጥ በጅምላም ሆነ በመለኪያ የሚሸጥበት የንግድ ቤት።2. ልዩ ልዩ የምግብ ሸቀጣሸቀጦች የሚሸጡበት የንግድ ቤት።

**ግሳታም** "*ገሳ" ስር ተመ.

**ግሳት** ዝ.ከ.

**ግሳንግስ** ስ 1. ዝባዝንኬ፥ ግብስብስ። 2. ኮተት።

**ግሳንግሳም** ቅ 1. አለሱን፡ ገለሱን ሁሉ የሚሰበስብ። 2. ኮተታም።

**ግሳጼ(ግሳጤ)** "ገሰፀ" ስር ተመ.

**ግስ** "ገሰሰ[3]" ስር ተመ.

**ግስላ** ስ 1. ቁጡ የሆነ ነብር መሳይ አውሬ። ቅ 2. ሃይለኛ፥ ቁጡ።

**ግሽልጥ** "ገሸለጠ" ስር ተመ.

**ግሽርጥ** "ጉሽርጥ" ን ተመ.

**ግሽበት** "ጋሸበ" ስር ተመ.

**ግሸጣ** ስ ቅርፁ ልብ የሚመስል የሚበላ ፍሬ የሚያፈራና በቆላ አካባቢ የሚበቅል፥ ፍሬውና ስሩ ለመድሃኒትነት ያገለግላል የሚባል የእፀዋት አይነት፤ ፍሬውም ግሸጣ ይባላል፡፡

**ግበቡ** "ገባ" ስር ተመ.

**ግቢ** ዝ.ክ.

**ግብ** ዝ.ክ.

**ግብረ ሃዋርያ** "*ገበረ[1]" ስር ተመ.

**ግብረ ሰዶም** ዝ.ክ.

**ግብረ ስጋ** ዝ.ክ.

**ግብረ አበር** ዝ.ክ.

**ግብረ ገብ** ዝ.ክ.

**ግብረ በላ** "ገበረ" ስር ተመ.

**ግብረ ጠል** ዝ.ክ.

**ግብር[1]** "ገበረ" ስር ተመ.

**ግብር[2]** "*ገበረ[1]" ስር ተመ.

**ግብርና** "*ገበረ[2]" ስር ተመ.

**ግብር ውሃ** ስ ሴቶች ግታ ከመኝታ በፊትና ጠዋት ስራ ከመጀመራቸው በፊት ብልታቸውን የሚታጠቡበት ውሃ።

**ግብር ውሃ ወጣች** ግታ ከመኝታ በፊት ወይም ጠዋት ከስራ በፊት ብልቷን ታጠበች።

**ግብስብስ** "*ገበሰበሰ" ስር ተመ.

**ግብአተመሬት**"ገባ" ስር "ግባተመሬት"ን ተመ.

**ግብዝ** "*ገበዘ" ስር ተመ.

**ግብዣ** "ጋበዘ" ስር ተመ.

**ግብይት** "ገበየ" ስር ተመ.

**ግብዳ** "ገበደ" ስር ተመ.

**ግብግብ** ስ ትግል ወይም ትንቅንቅ።

**ግብጣ** ስ ልብስ ሲጠብ ወሽመጥ ሆኖ የሚገባ ቁራጭ ጨርቅ።

**ግብጦ** ስ በአብዛኛው በጎጃም አካባቢ የሚበቅልና ባቄላ መሳይ ሆኖ መራራ ጣእም ያለው የአበባ እህል።

**ግተት** "ገተተ" ስር ተመ.

**ግት** "*ጋተ" ስር ተመ.

**ግትልትላም** "*ገተለተለ" ስር ተመ.

**ግትልትል** ዝ.ክ.

**ግትር** "ገተረ" ስር ተመ.

**ግትት** "ገተተ" ስር ተመ.

**ግትቻ** ዝ.ክ.

**ግነት** "ገነነ" ስር ተመ.

**ግን** ቀደም ብሎ በተነገረው ነገር ላይ አፍራሽ ወይም አጠራጣሪ የሆነ ሃሳብ ወይም አረፍተ ነገር ለማስከተል ሲፈለግ የሚገባ ማያያዣ። መደበኛ በሆነ ሁኔታ ላይ ብዙ ጊዜ "ነገር ግን" ይባላል። *መኪናዬን ውሰድ፤ ግን ቶሎ እንድትመልስ /ቶሎ እጠብቅሃለሁ፤ ግን ካልመጣስ?/ ብዙ መሰናከል ገጥሞን ነበር፤ ግን ውጤቱ የተሳካ ሆነ።*

**ግንበኛ** "ገነባ" ስር ተመ.

**ግንባር(ግምባር)** ስ 1. ፀጉር ከበቀለበት የራስ ክፍል በታች ከአይን በላይ ያለ የሰውነት ክፍል(ስእሉን ራስ ስር ተመ.)። 2. ፊት ለፊት። *ቤቱ ግንባር ላይ ነው ያለው።* 3.(ዘይ.) እድል፥ ገድ። *ጥሩ ግንባር አለው።* 4. አንድነት፥ ህብረት። *ግንባር ፈጥረው አጠቁት።* 5.ጦርነት የሚካሄድበት መስመር፤ጦር ግንባር። 6. ለጋራ አላማ በአንድ አመራር ስር በመጠቃለል የሚታገሉ የተለያዩ ሃይሎች የሚሰባሰቡበት የፖለቲካ መድረክ ወይም ድርጅት። *ነፃ አውጭ ግንባር።*

**ግንባሩ አይታጠፍም** ወደኋላ አይልም፥ አይበገርም።

**ግንባሩን አስመታ/አስወጋ** 1. ወደአንድ ቦታ ለትንሽ ጊዜ ብቅ በማለት መኖሩን አሳወቀ ወይም አሳየ። 2. ደጅ ጠና።

**ግንባሩን ከሰከሰ** ተኮሳተረ።

**የግንባር ስጋ** ቅ የማይፈራ፥ እውነቱን ፊት ለፊት የሚናገር።

**ግንባረ ቦቃ** ቅ ግንባሩ ላይ ነጭ ምልክት ያለበት (ከብት)።

**ግንባር ለግንባር** ስ ፊት ለፊት።

**ግንባር ቀደም** ስ የመጀመሪያ፥ ቀዳሚ።

**ግንባታ** "ገነባ" ስር ተመ.

**ግንብ** ዝ.ክ.

**ግንብጥ** "*ገነበጠ" ስር ተመ.

**ግንቦት** ስ ከሚያዝያ ቀጥሎ የሚመጣ የአመቱ ዘጠነኛ ወር ስም።

**ግንቦቴ** ስ በግንቦት ወር የሚዘራ ገብስ።

**ግንትር** "ገነተረ" ስር ተመ.

**ግንኙነት** "*ገነኘ" ስር ተመ.

**ግንዘት** "ገነዘ" ስር ተመ.

**ግንዛቤ**"*ገነዘበ" ስር ተመ.

**ግንዝ** "ገነዘ" ስር ተመ.

**ግንድ** ስ 1. በስር አማካኝነት ከመሬት ውስጥ የሚስበውን ውሃና ንጥረ ነገር ተቀብሎ ወደ ተክሉ ቅርንጫፎች አስተላላፊና ቅርንጫፎቹን ተሸካሚ የተክል ትልቁና ወፍራሙ ክፍል (የዛፍን ስእል ተመ.)። 2. ተቆርጦም ሆነ ሳይቆረጥ የሚገኝ ወፍራም እንጨት። 3. የትውልድ ሃረግ መነሻ።

**ግንድ የሚያክል** ትልቅ ወይም ግዙፍ የሆነ::
**ግንደ ቆርቁር** ስ በምንቃሩ ግንድ እየቦረቦረ በተቦረቦረው ቦታ ውስጥ የሚኖር ወፍ (ስእሉን ወፍ ስር ተመ.)::
**ግንዲላ** ስ ሳይፈለጥ ወይም ሳይሰነጠቅ ድፍኑን በተወሰነ ርዝመት የተቆራረጠ ግንድ::
**ግንድስ** "ገነደሰ" ስር "ግንዳሳ" ን ተመ.
**ግንገና** "ገነገነ" ስር ተመ.
**ግንጣይ** "ገነጠለ" ስር ተመ.
**ግንጥል** ዝ.ከ.
**ግንጭል** ስ መንገጭላ::
**ግንፍልፍል** "*ገፈለፈለ" ስር ተመ.
**ግኝት** "*ገኘኘ" ስር ተመ.
**ግኡዝ** ስ 1. ተንቀሳቃሽ ያልሆነና ህይወት የሌለው ነገር:: 2. (ዘይ.) የማይናገር(ሰው)::
**ግኡዝ ዖታ** ስ (ሰዋ.) በጥንታዊ የቋንቋ ሊቃውንት ትንተና መሰረት በአንስታይ ወይም በተባእታይ የፆታ መደብ የማይጠቃለል የፆታ አይነት (ለምሳሌ ድንጋይ)::
**ግእዝ** ስ 1. የጥንት የኢትዮጵያ የስነ ፅሁፍ ቋንቋ የነበረና አሁን በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ውስጥ ብቻ በአገልግሎት ላይ የሚገኝ ቋንቋ:: 2. ፊደል ገበታ ላይ ቀልቀል የመጀመሪያውን ረድፍ ይዘው የሚገኙት እንደ ሀ፥ለ፥... ያሉት ፊደላት ከዘሮቻቸው ማለትም ከካእብ (ሁ፥ሉ፥...)፥ ከሳልስ (ሂ፥ሊ፥..) ተለይተው የሚታወቁበትና የሚጠሩበት የቅርፃቸውና የረድፋቸው አጠቃላይ መጠሪያ:: 3. ከሶስቱ ያሬዳዊ የዜማ አይነቶች ያንደኛው መጠሪያ::
**ግው**[1]
**ግው(እግው) አለ** ግ ትልቅ ወይም ወፍራም ነገር ሲጋጭ፥ ሲወድቅ ወይም ሲመታ የሚፈጥረውን አይነት ድምፅ አሰማ::
**ግው**[2]
**ግው አለ** ግ በሃይል ነደደ::*እሳቱ ግው ብሎ ነደደ::*
**ግዙፍ** "ገዘፈ" ስር ተመ.
**ግዛት** "ገዛ" ስር ተመ.
**ግዝረት** "ገረዘ" ስር "ግርዘት"ን ተመ.
**ግዝት** "ገዘተ" ስር ተመ.
**ግዝፈት** "ገዘፈ" ስር ተመ.
**ግዞተኛ** "*ጋዘ[2]" ስር ተመ.
**ግዞት** ዝ.ከ.
**ግዢ** "ገዛ" ስር ተመ.
**ግዱፍ** "ገደፈ[1]" ስር ተመ.

**ግዳይ** "ገደለ" ስር ተመ.
**ግዳጅ**[1] "ገደደ[2]" ስር ተመ.
**ግዳጅ**[2] ስ የወር አበባ፥ አደፍ::
**ግዴታ** "ገደደ[2]" ስር ተመ.
**ግድ** ዝ.ከ.
**ግድም** "ገደመ"ስር ተመ.
**ግድርድር** "*ገደረደረ" ስር ተመ.
**ግድብ** "ገደበ" ስር ተመ.
**ግድንግዲ (ግድግዲ)** ስ የአሞራ አይነት::
**ግድንግድ** ቅ ወፍራምና ግዙፍ የሆነ::
**ግድያ** "ገደለ" ስር ተመ.
**ግድግዳ** "ገደገደ" ስር ተመ.
**ግድግዲ** "ግድንግዲ"ን ተመ.
**ግድፈት** "ገደፈ" ስር ተመ.
**ግግ** ስ ከድድ ውስጥ ወደ ላይ ገና እየበቀለ ያለ የህፃን ጥርስ::
**ግግር** "ገገረ" ስር ተመ.
**ግጥሚያ** "ገጠመ" ስር ተመ.
**ግጥም** ዝ.ከ.
**ግጥብ** "ገጠበ" ስር ተመ
**ግጦሽ** "ጋጠ" ስር ተመ.
**ግጫ** "እንግጫ"ን ተመ.
**ግጭት** "ገጨ" ስር ተመ.
**ግፈኛ** "ገፋ" ስር ተመ.
**ግፊት** ዝ.ከ.
**ግፊያ** ዝ.ከ.
**ግፍ** ዝ.ከ.
**ግፍልፍል** "*ገፈለፈለ" ስር"ግንፍልፍል"ን ተመ.
**ግፍጥጥ** "ገፈጠጠ" ስር ተመ.
**ጎ** የ"ገ" ፊደል ሳብእ ዘር::
**ጎህ** ስ በደንብ ከመንጋቱ በፊት የሚታይ ብርሃን ወይም ውጋጋን::
**ጎህ ሲቀድ** በደንብ ከመንጋቱ በፊት ባለው ጊዜ::
**ጎህ ቀደደ** ጨለማው ተገፈፈ፥ መንጋት ጀመረ፥ የፀሃይ ውጋጋን ታየ::
**ጎለመ** ግ ለየ፥ ከፈለ፥ ለብቻ አደረገ(የእርሻ መሬትን)::
**ጉልማ** ስ አባት ለልጁ የሚሰጠው ትንሽ የእርሻ መሬት::
**ጎለመሰ** ግ 1. ጎልማሳ ሆነ:: 2. (ዘይ.) አደገ፥ በሰለ (በአእምሮ፥ በአስተሳሰብ)::

**ጉልምስና** ስ ከወጣትነት በሂላ÷ ከሽምግልና በፊት ያለው የእድሜ ክልል።

**ጎልማሳ** ስ ከወጣትነት በሂላና ከሽምግልና በፊት ባለው የእድሜ ክልል ውስጥ የሚገኝ ወንድ (ሰው)።

**አጎላማሽ** ቅ አጠናካሪ÷ ተጨማሪ (ፊደል÷ ቃል÷..)።

**ጎለሰሰ** ግ በቀላሉ ጣለ ወይም አጋደመ።

**ጉልሽ** ቅ አቅመቢስ÷ በቀላሉ የሚወድቅ÷ የሚጋደም።

**ጎለበተ** ግ ጠነከረ÷ ሃይል አገኘ÷ በረታ።

**ጉልበት** ስ 1. የጭንና የቅልጥም መጋጠሚያ የሆነና ወደ ውጪ ወጣ ብሎ የሚታይ የሰውነት ክፍል (ስእሉን ሰውነት ስር ተመ.) ። 2.አቅም ሃይል÷ ብርታት። 3.(ዘይ.) በስራ ላይ የፈሰሰ ወይም የዋለ ሃይል። *ጉልበቴን በዘበዘኝ።*

**በጉልበት** በግድ÷ በሃይል በማስገደድ። *ሰዓቴን በጉልበት ነጠቀኝ።*

**በጉልበቱ ያረገዘ** ሰነፍ÷ ጉልበት እያለው የማይሰራ።

**ጉልበቱን ቆጠበ** መስራት የሚችለውን ያህል ከመስራት ተቆጠበ፤ ለገመ።

**ጉልበቱን አሳየ** 1.ሃይሉን÷አቅሙን÷ ችሎታውን ተጠቅሞ አሸነፈ÷ ድል አደረገ። 2. የሃይል እርምጃ ወሰደ።

**ጉልበቱን አፈሰሰ** በስራ ለፋ÷ ደከመ።

**ጉልበት ሳመ** 1. ጉልበት በመሳም አከበረ÷ አክብሮቱን አሳየ። 2.ተሸነፈ÷የበታችነቱን ተቀበለ።

**ጉልበት አወጣ** ሃይል አገኘ÷ በረታ።

**የጉልበት ስራ** ስ የአእምሮ ስራ ያልሆነ(እንደ ሸክም÷ ቁፋሮ÷... ያለ ስራ)።

**የጉልበት ሰራተኛ** ስ መሸከም÷ መቆፈር÷... በመሳሰሉና ከስልጠና ይልቅ ጉልበትን በሚጠይቁ ስራዎች ላይ የተሰማራ ሰራተኛ።

**የጉልበት ዋጋ** ስ አንድ ሰው ለሰራው የጉልበት ስራ የሚከፈል ገንዘብ ፥ ደመወዝ ወይም ሌላ ነገር ።


**ጉልበተኛ** ቅ 1. ሃይል÷ አቅም ያለው። 2. የፈለገውን በግድ ማድረግ ወይም ማስደረግ የሚችል÷ አመፀኛ።

**ጉልበታም** ቅ ሃይል ወይም አቅም ያለው።

**ጎለተ** ግ 1. ጉልቻን ተከለ ወይም አስቀመጠ። 2.በቂጡ አስቀመጠ÷ ቁጭ አደረገ። 3. ያለምንም ስራ ወይም ጥቅም ለረዥም ጊዜ አንድ ቦታ ላይ አስቀመጠ።

**ጉልት** 1. ስ (ስድብ) ሰነፍ፤ ከተቀመጠበት ተንቀሳቅሶ መስራት የማይወድ። 2. ስ በመንደር ውስጥ÷ በመንገድ ዳር÷... የተለያዩ ሸቀጦች(እንደ ሽንኩርት÷ ድንች÷...የመሳሰሉት) ለዚሁ ስራ ተብሎ በተዘጋጀ መደብ ላይ ተዘርግተው የሚሸጡበት አነስተኛ ገበያ፤ ጉሊትም ይባላል።

**ጉልቻ** ስ የድስት÷ የምጣድ...መጣጃ ሆኖ የሚያገለግል ሶስት ድንጋይ ወይም ሸክላ ወይም ከላይ ክብ ሆኖ ሶስት እግሮች እንዲኖሩት ተደርጎ ከብረት የሚሰራ መጣጃ።




**ጉልቻ ራስ** ስ (ስድብ) ትልቅ ራስ።

**ተጎለተ** ግ ያለ ምንም ስራ ወይም ጥቅም ለረዥም ጊዜ አንድ ቦታ ላይ ተቀመጠ።

**ጎለንታ(ጉለንታ)** ስ ከእርሻ ላይ አፈሩ በጎርፍ እንዳይሸረሸር አፈሩን ዳርና ዳር በመቆለል የሚሰራ የጎርፍ መከላከያ።

**ጎለደመ** ግ አፈነገጠ÷ከመደበኛ ቦታው ወጣ ብሎ ታየ(አጥንት÷ እንጨት÷...)።

**ጉልድም** ቅ ያፈነገጠ÷ ወጣ ብሎ የሚታይ(አጥንት÷ እንጨት÷...)።

**አጎለደመ** ግ ጎለደመ።

**ጎለደፈ** ግ ደነዘ÷ ዶለዶመ (ለምሳሌ ስለት)።

**ጎልዳፋ** ቅ 1. ስለት የሌለው÷ ዱልዱም (ቢላዋ÷ምላጭ÷...)።2. (ዘይ.) አብራርቶ ወይም አፍታቶ መናገር የማይችል። *ላንደበተ ጎልዳፋ።*

**ተጎላደፈ** ግ አብራርቶ ወይም አፍታቶ መናገር አቃተው።

**ጎለጎለ** ግ በዶማ ወይም በማረሻ የተነቀለን አረም አፈሩን በማራገፍ ጣለ። 2. ውሉን አጠፋ÷ ተበተበ (የልቃቂትን÷ የክርን÷...)። 3. በጣም ወደ ውጪ አወጣ (ለምሳሌ ምላሱን)። 4. አወጣ÷ ዘከዘከ (ምስጢርን÷ በድብቅ የተፈፀመን ነገር)።

**ጉልጓሎ(ጉልጎላ)** ስ በዶማ ወይም በማረሻ በተነቀለ አረም ቂጥ ላይ ያለን አፈር የማራገፍና አረሙን ከእርሻው ላይ የማስወገድ ስራ።

**ተጎለጎለ** ግ 1. አፈሩ እየተራገፈ አረሙ ከእርሻው ላይ ተነሳ÷ ተወገደ።2. ውሉ ጠፋ ተተበተበ(ክር÷ልቃቂት÷...)።3. ወጣ÷ ፈጠጠ (አይን÷ ምላስ÷...)።

***ጎለፈፈ**

**ጎልፋፋ** ቅ አቅመቢስ÷ በቀላሉ ጉልስስ የሚል።

**ጎላ**[1] ግ 1.ጉልህ ሆነ÷ ደመቀ(ዕሀፈት)። 2. ትልቅ

ወይም ግዙፍ ሆኖ ታየ።

**ማጉሊያ** ቅ አጉልቶ የሚያሳይ ወይም የሚያሰማ መሳሪያ።

**ጉልህ** ቅ 1. ግልፅ፥ ትልቅ ሆኖ ወይም ደምቆ የሚታይ(ፅሁፍ)። 2. በደንብ የሚታይ፥ የሚታወቅ፥ ከፍተኛ፥ ከባድ። (ለምሳሌ ጉልህ ስህተት፥ አስተዋፅኦ፥...)።

**አጎላ** ግ 1. ግልፅ፥ ትልቅ ሆኖ እንዲታይ አደረገ። 2. ከፍ ብሎ፥ በደንብ እንዲሰማ አደረገ።

**ጎላ**[2] ስ ለጎፍሮ፥ ለስጋ፥... መቀቀያ የሚያገለግል በጣም ትልቅ ብረት ድስት ወይም ጉርድ በርሜል።

**ጎል** ስ ግብ።

**ጎል ጠባቂ** ስ ግብ ጠባቂ፥ በረኛ

**ጎልማሳ** "ጎለመሰ" ስር ተመ.

**ጎልዳፋ** "ጎለደፈ" ስር ተመ.

**ጎልፍ** ስ አነስተኛና ጠንካራ የሆኑ ኳሶችን ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀ ልዩ በትር በመምታት ብዙውን ጊዜ ቁጥራቸው 9 ወይም 18 በሆኑና ተቆፍረው በተዘጋጁ የመሬት ቀዳዳዎች (ጉድጓዶች) ውስጥ ለማስገባት የሚደረግ ስፖርታዊ ጨዋታ።

***ጎመለለ**

**ጎምላላ** ቅ ሲሄድ ወይም ሲራመድ የሚጀነን።

**ጎምለል ጎምለል አለ** ግ ተጎማለለ።

**ተጎማለለ** ግ በመጀነን ወይም በኩራት ተራመደ፥ ሄደ።

**ጎመረ** ግ አኮራ፥ በኩራት ወይም በትእቢት ኮፈሰ፥ ወጠረ።

**ተጎመረ** ግ ኮራ፥በኩራት ወይም በትእቢት ተኮፈሰ፥ ተወጠረ።

**ጎመራ** ግ በሰለ፥ደረሰ(ሰብል፥ፍራፍሬ፥...) ።

**ጎመተ** ግ ሙዳ ሙዳ እያደረገ ቆረጠ ወይም ከፈለ (ስጋን)።

**ጎማች** ቅ ስጋ ቆራጭ፥ ስጋን በብልትና በሙዳ እየመጠነ የሚቆርጥ።

**ተጎመተ** ግ በተወሰነ መጠን ተቆረጠ (ስጋ)።

**ተጓመተ** ግ ተካፈለ (ስጋን)።

**ጎመን** ስ 1. የተለያየ ዝርያ ያለውና ተቀቅሎ የሚበላ የተክል አይነት (ለምሳሌ የአበሻ ጎመን፥ የጉራጌ ጎመን፥ ጥቅል ጎመን)።

**ጎመን በጤና** ጭቅጭቅና ውጥረት ካለበት የድሎት ኑሮ ይልቅ ሰላም ያለበት የድህነት ኑሮ ይሻላል ለማለት የሚነገር አባባል።

**የጎመን ትል** ስ በጎመን ቅጠል ላይ የሚገኝ ቅጠሉን እየተመገበ የሚኖርና መልኩ ቅጠል የሚመስል ትል።

**ጎመን ዘር** ስ ተወቅጦ ለምጣድ ማሰሻ እንዲሁም ተጨምቆ የምግብ ዘይት የሚሆን የአበሻ ጎመን ፍሬ።

**ጎመዘዘ** ግ ሆመጠጠ።

**ጎምዛዛ** ቅ ሆምጣጣ።

**ጎመደ** ግ 1. ቆረጠ፥ጎረደ። 2. ገመጠ፥ በላ (ዳቦን፥ ስጋን፥...)። 3. መታ (በዱላ)።

**ጉማጅ** ቅ ከላዩ ላይ ተቆርጦለት የቀረው ክፍል ወይም ቁራጩ(ለምሳሌ የእንጨት ጉማጅ /የዳቦ ጉማጅ)።

**ጉምድ** ቅ ቆራጣ።

**ጉምድ አለ** ግ ማለቅ ከሚገባው ጊዜ በፊት አለቀ። *ለአንድ ወር የተገዛው ጤፍ በሁለት ሳምንት ውስጥ ጉምድ አለ።*

**ጎመድ** ስ ቆመጥ፥ ወፍራም ዱላ።

**ጎማዳ** ቅ 1. ጎራዳ፥ቆራጣ። 2. (ዘይ.) ቶንጋ፥ መልከ ጥፉ። 3. (ስድብ) ውሸታም።

**ጎመጀ(ጎመዠ)** ግ ተመኘ፥ቋመጠ፥ ጓጓ።

**አስጎመጀ** ግ አጓጓ ወይም አጓረ።

**ጎመጎመ** ግ 1.መብቀል ወይም መውጣት ጀመረ፥ ጎነቆለ። 2. አጎጠጎጠ፥ መውጣት ወይም ማደግ ጀመረ(ጡት)።

**አጎመጎመ** ዝ.ከ.

***ጎመጎመ**

**ጉምጉምታ** ስ 1. ይፋ ያልሆነ፥ ውስጥ ውስጡን የሚወራ ሃሜት፥ቅሬታ፥...። 2. በአንድ ቦታ ላይ የተሰበሰቡ ሰዎች ድምፃቸውን በደንብ ሳያሰሙ በሹክሹክታ ሲያወሩ የሚሰማው የሚያስገመግም ድምፅ።

**ጉም ጉም አለ** ግ ሃሜትን፥ ቅሬታን፥... በሹክሹክታ ወይም በድብቅ አወራ።

**ጎመጭ**[1] ስ 1. አገዳው ቀጭን የሆነና ብዙ ዛላ ያለው የሳር አይነት።

**ጎመጭ**[2] ስ ማር የለሽ የንብ እንጀራ፥የማር ከዳ።

**ጎሚስታ** ስ የመኪና ጎማ በመቀየር፥ የተነፈሰ አየር በመሙላት፥ የተቀደደውን በመጣፍ፥... አገልግሎት የሚሰጥ ድርጅት።

**ጎማ** ስ 1. ከጎማ ዛፍ ከሚገኝ ፈሳሽ በፋብሪካ ውስጥ ክብ ሆኖ ተሰርቶ የሚወጣና ከተሽከርካሪዎች ቸርኬ ላይ እየተገጠመ ተሽከርካሪዎችን ለመሽከርከር የሚያስችላቸው አካል ። 2. ጠንካራና ወፍራም ላስቲክ።3. (ዘይ.) የማይታኘክ፥ ጎማ1ኛኛቺ አኞ (ስጋ)።



**የጎማ ዛፍ** ስ እንደመኪና ጎማ፥ የውሃ ጎማ፥ ላስቲክ፥... የመሳሰሉትን ለመስራት የሚያስችል ወተት የመሰለ ፈሳሽ የሚያመነጭ የተክል አይነት።

**ጎማ ጫማ** ስ ካገለገለ ጎማ እየተቆረጠ የሚዘጋጅ ሽፍን ያልሆነ ጫማ።

**ጎማች** "ጎመተ" ስር ተመ.

**ጎማዳ** "ጎመደ" ስር ተመ.

**ጎምላላ**"ጎመለለ" ስር ተመ.

**ጎምቱ** ትልቅ ወይም ጨዋ ሰው፥ አዛውንት።

**ጎምበሬ(ገንቦሬ)** ስ በክረምት ዝናብ ሲዘንብበት ጭቃ የማይሆን የአፈር አይነት።

***ጎረመረመ**

**ጉርምርምታ** ስ 1. የነጎድጓድ ድምፅ። 2. ተከታታይነት ያለው የመንጓጓት ድምፅ ። 3. ጉምጉምታ።

**ተጉረመረመ** ግ የነጎድጓድ ድምፅ ተሰማ።

**አጉረመረመ** ግ 1. የነጎድጓድ ድምፅ አሰማ(ሰማይ)። 2. ጮሀ፥ ተንጓጓ(ሆድ)። 3. ዝቅ ባለ ድምፅ የቅሬታ አነጋገር ተናገረ፤ አጉተመተመ።

**ጎረመሰ** ግ 1. ጎረምሳ ሆነ። 2. አስቸጋሪ ወይም ጥጋበኛ ሆነ(ለወጣት ልጅ)።

**ጉርምስና** ስ ከ14-18 አመት ያለው የወንድ ልጅ እድሜ።

**ጎረምሳ** ስ ከ14-18 ገደማ ባለው የእድሜ ክልል ውስጥ የሚገኝ ወንድ ልጅ።

**ጎረመደ** "ግረመደ" ን ተመ.

**ጎረምሳ** "ጎረመሰ" ስር ተመ.

**ጎረሰ** ግ 1. ምግብ አፉ ውስጥ ጨመረ። 2. በላ። *በምቴ ትንሽ ጉረስ እስኪ*። 3. ጠበንጃ፥ሽጉጥ፥... ውስጥ ጥይት ተጨመረ ወይም ገባ። 4. ያዘ። *ባትሪው ስንት ድንጋይ ይጎርሳል።*

**ጉርሻ** ስ 1. አፍ ውስጥ አንዴ ሊገባ የሚችልና እጅ መጥኖ የሚይዘው የምግብ መጠን። 2. ዳረጎት። 3. ከመደበኛ ክፍያ ወይም ደመወዝ በተጨማሪ የሚሰጥ የገንዘብ ስጦታ። 4. ጉቦ። 5. ምግብ ሲበላ (ለማቅመስ፥ ለማጥገብ፥ ፍቅርን ለመግለፅ፥...) ሲባል አንዱ ለሌላው በእጅ ጠቅልሉ ወደአፉ የሚከትለት ምግብ።

**ጎራሽ** ቅ የህል የሚጎርስ።*ዘጠኝ ጎራሽ ጠመንጃ።*

**ጎረበ** ግ 1. የውስጥ እጅ ቆዳ በስራ ብዛት የተነሳ ወይም ሌላው የሰውነት ክፍል ቆዳ በበሽታ ምክንያት ውሃ እየቋጠረ ወይም ሳይቋጥር አኮፈኮፈ፥ ጉብ ጉብ አለ። 2. ተወጥሮ የነበረው ወይም መወጠር ያለበት ነገር ረገበ ወይም ላላ አለ።3. ገለባው ከፍሬው ላይ ሙልጭ ብሉ እንዳይሄድ ለማድረግ በመጠኑ ተፈተገ (ስንዴ፥ ገብስ፥...)። 4. የፈላ ውሃ ውስጥ የገባ አተር፥ ባቄላ፥... ቆዳው ተጨማደደ።

**ተጉረበረበ** የ"ጎረበ" ን 1ኛ ፍቺ ተመ.

**አጉረበረበ** ዝ.ከ.

**አጎረበ** ዝ.ከ.

***ጎረበተ**

**ጎረቤት** ቅ 1. አቅራቢያ፥ አጠገብ ለአጠገብ፥ ቅርብ ለቅርብ። *እኔና እሱ ጎረቤት ነን*። 2. በአቅራቢያ ወይም በድንበር አካባቢ ያለ (ለምሳሌ ሃገር)። ስ 3. መኖሪያ ቤቱ ከሌላው መኖሪያ አጠገብ ወይም አቅራቢያ የሆነ ሰው። *እገሌ ጎረቤቴ ነው።*

**ጉርብትና** ስ አጠገብ ለአጠገብ ወይም ቅርብ ለቅርብ በሚኖሩ ሰዎች መካከል ያለ ግንኙነት፥ መቀራረብ።

**ተጎራበተ** ግ አጠገብ ለአጠገብ ወይም ቅርብ ለቅርብ ሆነ።

**ተጎራባች** ቅ ጎረቤት።

**አጎራበተ** ግ ጎረቤት አደረገ።

**አጎራባች** ቅ ወሰንተኛ ጎረቤት።

**ጎረበጠ** ግ 1. ቆረቆረ፥ አልመች ወይም አልሰማማ አለ። 2. አመመ(ሆድን)።

**ጎርባጣ** ቅ የሚቆረቁር፥ምቾት የሌለው (መቀመጫ፥ መኝታ፥...)።

**ጎርበጥባጣ** ቅ ወጣ ገባ፥ ያልተስተካከለ።

**ጎረነነ** ግ ጎርናና ሆነ።

**ጎርናና** ቅ ወፍራም (ድምፅ)።

**ጎረና** ግ በአግባቡ ባለመግሰሉና በማረሩ ምክንያት ጣእሙ ተበላሸ (ለምሳሌ ወጥ)።

**ጉርናት** ስ እንደወጥ የመሰለው በአግባቡ ባለመግሰሉና በማረሩ ምክንያት የሚያመጣው መጥፎ ቃና ወይም ጣእም።

**ጎረንጎሬ** ስ ከቆዳ የሚሰራ ስለት ያላቸው እቃዎች መከተፊ።

**ጎረደ** ግ 1. ቆረጠ፥ ጎመደ። 2.ዘለለ፥ ገደፈ (ፊደልን)።

**ጉራጅ** ቅ ቁራጭ፥ ጉማጅ።

**ጉርድ** ስ 1. የደረሰኝ ቀሪ ካርኒ። 2. ሙሉ ያልሆነ።

**ጉርድ ሸሚዝ** ስ እጅጌው አጭር የሆነ ሸሚዝ።

**ጉርድ ቀሚስ** ስ ከወገብ በታች ያለውን የሰውነት ክፍል ብቻ የሚሸፍን የሴት ቀሚስ ።

**ጉርድ ፎቶ** ስ ከወገብ በላይ ያለውን የሰውነት ክፍል ብቻ የሚያሳይ ፎቶግራፍ።

**ጉርዶሽ(ጉርዶ)** ስ ተጀምሮ ሳያልቅ የቀረ ስራ::

**ጎራዳ** ቅ አፍንጫው አጭርና ትንሽ የሆነ፡ ፉንጋ::

**አጉራዶ** ስ ባጭር ባጭሩ የተቆረጠ ግንድ::

***ጎረደደ**

**ጎርዳዳ** ቅ ጅንን÷ቁንን::

**ጎርደድ ጎርደድ አለ** ግ በቀስታ በመራመድ ወዲያና ወዲህ ተመላለሰ::

**ተንጎራደደ** ዝ.ከ.

**አንጎራደደ** ግ እያራረጠ ደበደበ(በዱላ÷ በፍልጥ÷..)::

**ጎረደማን(ጎረዶማን)** ስ በጋማ ከብት ጀርባ ላይ ሸቀጡን እያስጫነ ከሚያጓጉዝ ነጋዴ ጋር እየተጓዘ ጭነቱን በመጫን÷ በማራገፍ÷ ከብቶቹን በመንዳት÷... አገልግሎት ይሰጥ የነበረ የሲራራ ነጋዴ አሽከር::

**ጎረጎማ** ቅ የተሸራረፈ ወይም የወላለቀ (ጥርስ)::

**ጎረጎረ** ግ 1. ሰረሰረ:: 2. በጣት÷ በሳር÷ በላባ÷... የጆሮን÷ የአፍንጫን÷... ውስጥ ነካካ ወይም አከከ:: 3. ፈተሸ÷ በረበረ::

**ጎረጎደ** "ጎደጎደ"ን ተመ.

**ጎረጠ** ግ ፈጠጠ÷ ወጣ (አይን)::

**ጉርጥርጥ(ጎረጥራጣ)** ቅ አይነ ፈጣጣ::

**ጎሪጥ** ዝ.ከ.

**የጎሪጥ አየ** በንቀት÷ በጥላቻ÷..አየ፤ የጎድን አየ::

**ተጉረጠረጠ** ግ በቁጣ÷ በንዴት÷... ምክንያት አይኑ ፈጦ ወዲያና ወዲህ ተንከባለለ::

**አጉረጠረጠ** ግ በቁጣ÷ በንዴት÷... ምክንያት አይኑን በሚፍጠጥ ወዲያና ወዲህ አንከባለለ::

**ጎረጎጨ** ግ ጉሮሮው አካባቢ ድምፅ በማሰማት ጠጣ፡ ጎርጎጭ አደረገ::

**ጉርጉጭታ** ስ ፈሳሽ ነገር ሲጠጣ ጉሮሮ አካባቢ የሚሰማ ድምፅ::

**ጉርጉጭ አደረገ** ግ የተጎነጨውን በጉሮሮው አወረደ::

**ጎርጎጭ አደረገ** ዝ.ከ.

**ጎረፈ** ግ 1. ድፍርስ ውሃ መሬት ለመሬት በብዛት ፈሰሰ÷ወረደ(በዝናብ የተነሳ):: 2. በብዛት ፈሰሰ (ደም÷እንባ÷..)::3.በብዛት ተመመ÷ ተጕጎደጎደ:: *ህዝቡ ወደ ስብሰባው ይጎርፋል::* 4. በብዛት ቀረበ:: *ግብዣው ጎረፈ / ጥያቄው ጎረፈ::*

**ጎርፍ** ስ 1. በብዛት የሚፈስ የዝናብ ውሃ::2. ብዙ አያሌ::

**አጎረፈ** ግ 1. ጎርፍ ሆነ (የጣለው ዝናብ):: 2. አረፋ ሆነ ወይም አረፋው በደንብ እንዲታይ አደረገ (ልብስ በሳሙና ሲታጠብ)::

**ጎሪጥ** "ጎረጠ" ስር ተመ.

**ጎራ**[1] ስ 1. ከፍተኛ ቦታ÷ ኮረብታ:: 2. ፊና÷ ወገን:: *ሁሉም በጎራው ተሰልፏል::*

**ጎራ**[2]

**ጎራ አለ** ግ እግረ መንገዱን ደረስ ወይም ገባ አለ (ወደ ሌላ ቦታ በመሄድ ላይ ያለ ሰው)::

**ጎራ** ግ ከመረ÷ ቆለለ (ድንጋይን÷ እንጨትን÷...)::

**ጎራዳ** "ጎረደ" ስር ተመ.

**ጎራዴ** ስ ቅርፁ ጎበጥ ብሎ ረዘም ያለና በአንድ በኩል ብቻ ስለት ያለው ባለእጀታ የጦር መሳሪያ::

**ጎሬ** ስ ዋሻ÷ ጉድጓድ::

**ጎርምጥ**[1] ስ እግር አካባቢ የሚወጣና በቀላሉ የማይድን ከባድ ቁስል::

**ጎርምጥ**[2] ስ በባህር ውስጥ የሚገኝ ባለ ብዙ እግር ነፍሳት::

**ጎርበጥባጣ** "ጎረበጠ" ስር ተመ.

**ጎርባጣ** ዝ.ከ.

**ጎርናና** "ጎረነነ" ስር ተመ.

**ጎርዳዳ** "*ጎረደደ" ስር ተመ.

**ጎርፍ** "ጎረፈ" ስር ተመ.

**ጎሰመ** ግ 1. ጎነጠ÷ መታ÷ ወጋ:: 2. ደለቀ÷ መታ(ከበሮን÷ ነጋሪትን)::

**ጎሰረ** ግ ጠቀጠቀ÷ አመቀ÷ አጨቀ:: 2. በብዛት አፉ ውስጥ ጨመረ::

**ጉስር** ቅ ቁዝር::

**ተጎሰረ** ግ ተቆዘረ::

**ጎሰቆለ** ግ ተጎሳቆለ::

**ጎስቋላ (ጉስቁል)** ቅ የከሳ÷ የመነመነ÷ የተጎዳ(በችግር÷ በሃዘን)::2 በአለባበሱ ቆሻሸ ያለ÷ችግረኛ::

**ተጎሳቆለ** ግ 1. ከሳ÷ መነመነ÷ ገረጣ(በችግር÷ በሃዘን ምክንያት)::2. በችግር ምክንያት አለባበሱ ቆሸሸ አለ:: 3. በደንብ ካለመያዝ የተነሳ ተበላሸ÷ ተንገላታ(ልብስ÷ እቃ÷...)::

**ጎሰጎሰ** ግ 1. በብዛት ጠቀጠቀ÷ አመቀ÷ ከተተ:: 2. (ዘይ.) በብዛት በላ::

**ጎሳ** ስ የባህልና የቋንቋ አንድነት እንዲሁም በደምና በስጋ ዝምድና ላይ የተመሰረተ ግንኙነት ያለውና መጠኑ ከነገድ አነስተኛ የሆነ ማህበረ ህዝብ::

**የጎሳ ፖለቲካ** ስ በዘር÷ በጎሳ÷ በብሄረሰብ ላይ የተመሰረተ ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ::

**ጎስቋላ** "ጎሰቆለ" ስር ተመ.

**ጎሸ** ግ ደፈረሰ::

**ጉሽ** ቅ ድፍርስ ወይም ያልጠራ::

**ጉሽ ጠላ** ስ ድፍርስ ወይም ያልጠራ ጠላ::

**ኀሸመ** ግ 1.በክርን ነካ ወይም ገፋ አደረገ፥ጎነተለ ፥ መታ:: 2."**በነገር ኀሸመ**"ን ተመ.

**ኀሸመጠ** ግ 1. በአሽሙር ተናገረ:: 2. አሽሟጠጠ::

**ኀሽ**[1] ስ ፈርጣማ ጫንቃና አጫጭር እግሮች እንዲሁም ሰፋፊ ሆነው ወደታች የተቀለበሱ ጆሮዎች ያሉት፥ የማየትና የመስማት ችሎታው ከፍተኛ የሆነ፥ ከቀንድ ከብት ጋር በቅርብ የሚዛመድ የዱር እንስሳ (ሰአሉን የዱር እንስሳ ስር ተመ.)::

**የኀሽ ፀጉር** ስ በአንዳንድ ሰዎች ማጅራት ወይም ጆሮ ግንድ ወይም ግንባር አካባቢ የሚበቅል ስስ፥ ለስላሳና ቀላ ያለ ፀጉር::

**ኀሽ**[2] 1. እንኳን፥ ጥሩ፥ መልካም፥... ለማለት የሚባል የምስጋናና የማበረታቻ ቃል::*ኀሽ የኔ ልጅ/ ኀሽ በርታ!* 2. እባክህ::*ኀሽ መፅሃፉን ላቀብለኝ::*

**ኀሽ አለ** ግ እሰይ፥ እንኳን፥... አለ::

**ኀበረ** ግ 1. አበጥ ወይም ወጣ ብሎ ታየ:: 2. ልጥፍ፥ ልስቅ ሳይል ቀረ፤ ከፈፍ አለ::

**ጉብር** ስ እንደ ጉጥ ወጣ ብሎ የሚታይ የአንድ ነገር አካል::

**ጉብራት** ዝ.ክ.

**ተኀበረ** ግ አበጥ፥ ከፈፍ፥ ጉብ አለ::

**አኀበረ** ግ ኀበረ::

**ኀበረረ** ግ በመድረቁ ምክንያት ኀባጣ ሆነ::

**ኀብራራ(ኀበረር)** ቅ የደረቀና የኀበጠ::

**ተንኀበረረ** ግ ኀበረረ::

**አኀበረረ** ዝ.ክ.

**አንኀበረረ** ግ ኀብራራ እንዲሆን አደረገ፥ አንኀበደደ::

**ኀበሰተ** ግ በተደጋጋሚ ሳለ፥ ኡሁ ኡሁ አለ::

**ኀበበ** ግ 1. ልጥፍ ወይም ልስቅ ሳይል ቀረ፤ ከፈፍ አለ:: 2. ኀበጠ::

**ኀባባ** ቅ ኀባጣ::

**ተንኀበበ** ግ ኀበበ::

**አንኀበበ** ግ ኀንባሳ ወይም ኀባጣ እንዲሆን አደረገ::

**ኀበኘ** ግ ተዘዋውሮ አየ ወይም ተመለከተ::

**ጉብኝት** ስ ስለአንድ ነገር ወይም ቦታ ለማወቅ፥ ለመረዳት ወይም ለማድነቅ እየተዘዋወሩ የማየት ወይም የመመልከት ድርጊት::

**ኀብኚ** ስ ታሪካዊ ቦታዎችን ወይም ሌሎች ነገሮችን እየተዘዋወረ የሚያይ ወይም የሚመለከት ሰው::

**አስኀበኘ** ግ ከኀብኚው ጋር አብሮ በመዞር ስለሚታየው ነገር ለኀብኚው አስረዳ፥ አሳወቀ::

**አስኀበኚ** ቅ ኀብኚዎችን እያዞረ የሚያሳይ፥ የሚያስኀበኝ::

**ኀበዘ** ግ ኀበዝ ሆነ::

**ኀበዝ** ቅ 1. ጀግና፥ ሃይለኛ፥ ብርቱ፥ ጠንካራ:: 2. ታታሪ፥ ትጉህ:: 3. በአንድ ሙያ ወይም የእውቀት ዘርፍ፥... ጥሩ ችሎታ ያለው::

**የኀበዝ አለቃ** ስ በጦርነት፥ በአሰሳ ወይም ሌሎች ተመሳሳይ በሆኑ እንቅስቃሴዎች ወቅት በአንድ አካባቢ የሚገኙ ተዋጊዎችን ወይም አሳሾችን እንዲመራ በአካባቢው ሰዎች በችሎታው የሚመረጥ አለቃ ወይም መሪ::

**ጉብዝና** ስ 1. ጀግንነት፥ ሃይል፥ ብርታት፥ ጥንካሬ:: 2. ትጋት፥ ታታሪነት:: 3. ጥሩ ችሎታ::

***ኀበደደ**

**ኀብዳዳ** ቅ ኀባጣ፥ ኀንባሳ::

**ጉብድድ አለ** ግ ኀባጣ ወይም ኀንባሳ ሆነ::

**ኀብደድ አለ** ግ ኀንበስ አለ::

**አኀበደደ** ግ 1. ኀበጠ:: 2. አኀነበሰ:: 3. (ዘይ.) ራሱን ዝቅ በማድረግ ተለማመጠ፥ አሽረገደ::

**አኀብዳጅ** ቅ ራሱን ዝቅ በማድረግ የሚለማመጥ፥ የሚያሽረግድ፤ አድርባይ::

**ኀበኀበ**[1] ግ ጉብጉባት አበጀ::

**ጉብጉባት** ስ አንድን ነገር ለማስጌጥ ሲባል ጉብ ጉብ እንዲል ተደርጎ የሚሰራ ጌጥ::

**ኀበኀበ**[2] ግ ውሃ ያዘ፥ ቋጠረ፥ አኀረበ(የሰውነት ቆዳ)::

**አኀበኀበ** ዝ.ክ.

***ኀበኀበ**

**ጉብጉብ** ስ የተኀበኀበ ሊጥ::

**ተኀበኀበ** ግ አብሲት በመብዛቱ ወይም ሊጡ በመቅጠኑ የተነሳ ለማስተካከል ሲባል ሊጡ ላይ ዱቄት በመጨመር ተለወሰ::

**አኀበኀበ** ግ አብሲት የበዛበትን ወይም የቀጠነ ሊጥን አወፍሮ ለማስተካከል ዱቄት በመጨመር ለወሰ::

**ኀበጠ** ግ አኀነበሰ፥ ኀበበ፥ የደጋን ቅርፅ ያዘ::

**ኀባጣ** ቅ የደጋን ቅርፅ ያለው፤ ኀንበስ ያለ::

**ኀቢጥ** ቅ (ስድብ) ዝ.ክ.

**ኀበጥባጣ** ቅ ኀርበጥበጣ፥ብዙ ቦታ ላይ ኀባጣነት ያለው::

**ጎባባ** "ጎበበ" ስር ተመ.
**ጎባን** ስ ጣውንት።
**ጎባጣ** "ጎበጠ" ስር ተመ.
**ጎብራራ** "ጎበረረ" ስር ተመ.
**ጎብኚ** "ጎበኘ" ስር ተመ.
**ጎብዳዳ** "*ጎበደደ" ስር ተመ.
**ጎተራ** ስ 1. ከጭቃ ወይም ከእንጨት ወይም ከቆርቆሮ፥... አራት ማእዘን ወይም ክብ ሆኖ የሚሰራና ክዳን ያለው የእህል ማስቀመጫ። 2. (ዘይ.) ብዙ የሚበላ፣ ሆዳም።


ጎተራ 1ኛ ፍቺ

**ጎተተ(ገተተ)** ግ 1. ሳበ፥ ወደ ራሱ አቀረበ። 2. ወደሂላ አስቀረ፥ አዘገየ፥ እንዳይፈጥን አደረገ።3. የማይፈለግን ጉዳይ፥ ሰው፥ ነገር፥... አስከትሎ ወይም ይዞ መጣ። *የማልፈልገውን ነገር ለትጎትትብኝ* ። 4. ጠራ(ሰይጣንን)።
**ጉታታ(ጉትት)** ቅ ሲሄድ፥ ሲሰራ፥... ፍጥነት፥ ቅልጥፍና የሌለው፥ ቀርፋፋ።
**ጎታች** ቅ ፍጥነትን፥ እድገትን፥...ወደሂላ የሚያስቀር፥ የሚያዘገይ።
**ጎታች ባህል** ስ ለእድገት፥ ለዘመናዊ ስልጣኔ፥.. እንቅፋት የሆነ ባህል።
**ተጎተተ** ግ ዝግ ወይም ቀስ አለ፣ ተንቀረፈፈ።
**ተጎታች** ስ ተሳቢ(የመኪና)።
**ተጓተተ** ግ 1. በታሰበው ጊዜ ሳይከናወን ወይም ሳይፈፀም ቀረ።2.አብሮ ተያይዞ ወይም ተግተልትሎ መጣ ወይም ሄደ።
**አጓተተ** ግ በታሰበው ጊዜ ሳይፈፀም ወይም ሳይከናወን እንዲቀር አደረገ (አንድን ጉዳይ)።
***ጎተነ**
**ጉተና** ስ አጠር ያለ ጎፈሬ።
**አጎተነ** ግ አጠር ያለ ጎፈሬ አሳደገ።
**ጎተጎተ** ግ አንድ ነገር እንዲደረግ ወይም እንዲፈፀም፥...በተደጋጋሚ በትጋት አሳሰበ፥ ወተወተ፥ ቀሰቀሰ።
**ጎትጓች** ቅ አንድ ነገር እንዲደረግ ወይም እንዲፈፀም፥...በተደጋጋሚ በትጋት የሚያሳስብ፥ የሚያስታውስ።
**ጎታ** ስ ከጭቃ ወይም ከእንጨት ወይም ከቆርከሃ የሚሰራና ከጎተራ አነስ ያለ የእህል ማስቀመጫ።
**ጎታታ** "ጎተተ" ስር ተመ.
**ጎታች** ዝ.ከ.
**ጎትጓች** "ጎተጎተ" ስር ተመ.

**ጎቸ** ግ በትንሽ በትንሹ ከመረ፥ ቆለለ፣ ቆጭ ቆጭ አደረገ።
**ጉች አለ** ግ 1. በትንሹ ተቆለለ። 2. ቆጭ አለ፥ ተቀመጠ።
**ጉች ጉች ያለ ጡት** ቀጥ፥ ፈርጠም ብሎ የሚታይ ያልወደቀ ጡት።
**ጎነቀለ(ቆነጎለ)** ግ ውሃ ውስጥ የተነከረ ባቄላ፥ አተር፥ ሽንብራ፥...መብቀል ጀመረ።
**ጉንቁል** ቅ ውሃ ውስጥ ተነክሮ የበቀለ (አተር፥ ባቄላ፥ ሽንብራ፥...)።
**አጎንቆለ** ግ 1. ጎነቀለ። 2. እንዲጎነቅል አደረገ(ጥራጥሬን ውሃ ውስጥ በመንከር)።
***ጎነበ**
**ተጎናነበ** ግ ተከናነበ፥ ተጀቦነ፥ ተሸፋፈነ።
***ጎነበሰ**
**ጎንባሳ(ጉንብስ)** ቅ ጎባጣ።
**በጉንብሱ ሄደ** አጎንብሶ ወይም ጎብጦ ብሎ ሄደ።
**ጎንበስ ቀና አለ** 1. ለፋ፥ ደከመ። 2. ተሽቆጠቆጠ። *ጎንበስ ቀና ብሎ ላስተናገደኝ።*
**ጎንበስ አለ** ግ 1. ጎበጥ ወይም ጎብደድ አለ። 2. አንገቱን ዘንበል ወይም ደፋ አደረገ። 3. ከአንገቱ፥ ከትከሻውና ከወገቡ ወደ መሬት ዘንበል ብሎ ዝቅ አለ።
**ተጎነበሰ** ግ ከአንገቱ፥ከትከሻውና ከወገቡ ወደ መሬት ዘንበል ብሎ ዝቅ አለ፣ አጎነበሰ።
**ተጎናበሰ** ግ ጎንበስ በማለት ይቅር ተባባለ፣ ታረቀ።
**አጎነበሰ** ግ 1. ጎንበስ አለ። 2. ራሱን ዝቅ በማድረግ ተለማመጠ፥ አሸረገደ።
**አጎንባሽ** ቅ አጎብዳጅ።
**ጎነተለ** ግ ጎነጠ፥ ጎሸም አደረገ።
**ጉንተላ** ስ ጉነጣ፥ጉሸማ።
***ጎነዘለ**
**ጎንዛላ** ቅ ዘንፋላ።
**ተጎናዘለ** ግ ተዘናፈለ።
**አጎናዘለ** ግ አዘናፈለ።
**ጎነደ** ግ እራሱን ችሎ ለብቻው መኖር ጀመረ።
**ጎናጄ** ቅ ለብቻው ኗሪ ሳጤ።
**ጎነደለ** ግ ቆረጠ።
**ጎንዳላ(ጉንድል)** ቅ ቆራጣ።
**ጎነደበ** ግ ቆረጠ፥ ጎረደ፥ ጎመደ።
**ጎነደሸ** ግ ቆረጠ፥ ቆመጠ።
**ጉንድሽ** ቅ (ስድብ) ቆራጣ፥ ቆማጣ (እጅ

ወይም እግር)።

**ጎነጎነ** ግ 1. ሶስት ወይም ከዛ በላይ የሆኑ ገመዶችን ወይም ክሮችን÷... በአንድነት እያጠላለፈ ገመደ። 2. የፀጉር ጉንጉን ሰራ።3. (ዘይ.) ነገርን ወይም ሴራን አውጠነጠነ÷ ዶለተ።

**ጉንጉን** ስ የተጎነጎነ (ፀጉር÷ ቃጫ÷...)።

**ጉንጉን አበባ** ስ የ"አበባ ጉንጉን"ን ተመ.

**ጎነጠ** ግ 1. ወጋ (በጣት÷ በእንጨት÷...)። 2. (ዘይ.) በነገር ነካ ወይም በአሽሙር ተናገረ። *በነገር ጎነጠኝ።*

***ጎነጨ**

**ጉንጭ** ስ ከአይን በታችና ከአፍ ግራና ቀኝ በኩል የሚገኝ የሰውነት ክፍል (ስእሉን ራስ ስር ተመ.)።

**ጉንጭ አልፋ ንግግር** ፍሬ የሌለው አሰልቺ ንግግር።

**ጉንጫም** ቅ ጉንጩ ወፍራም የሆነ (ሰው)።

**ጎንጨት(ጉንጭት) አደረገ** ግ አፉ የሚችለውን ያህል አንዴ ጠጣ።

**ተጎነጨ** ግ 1. ዝ.ከ. 2. ጠጣ(መጠጥን)።

***ጎነፀፈ**

**ተጎናፀፈ** ግ 1. መላ ሰውነቱን ሸፈነ (ለምሳሌ በልብስ÷ በመጎናፀፊያ)። 2. በለበሰው ልብስ ላይ ደርቦ ለበሰ(ካባን÷ካፖርትን÷...)። 3. (ዘይ.) ተቀዳጀ÷ አገኘ(ክብር÷ ድል÷...)።

**መጎናፀፊያ(መጎናጠፊያ)** ስ የዕላት መሸፈኛና መሸከሚያ የሆነ ረጅምና ሰፊ ግምጃ።

**አጎናፀፈ** ግ 1. አለበሰ÷ ሸፈነ። 2. አቀዳጀ÷ ሰጠ (ክብርን÷ ድልን÷...)።

**ጎነፈ** ግ 1. የለበሰውን ልብስ በጉያው ወይም በብብቱ ወደ ላይ ሰብስቦ ያዘ።2. አፈነ÷ ሸፈነ(በጪስ)። 3. አፈር አስታቀፈ(ተክልን)። 4. በሙቅ ውሃ ዘፍዝፎ አጠበ(ልብስን ወይም ማንኛውንም እቃ)። 5. በረመጥና በውሃ አጠበ(በቅባት የተበከለን እቃ)።

**ጉንፍ** ስ በብብት አካባቢ ያለ የሰውነት ክፍል፤ ጉያ።

**ጎናም** "ጎን" ስር ተመ.

**ጎናዴ** "ጎነደ" ስር ተመ.

**ጎን** ስ 1. በሰውነት ግራና ቀኝ በኩል የሚገኝና ከብብት እስከ ዳሌ ድረስ ያለው የሰውነት ክፍል። 2. በስተቀኝ ወይም በስተግራ በኩል የሚገኝ የማንኛውም አካል÷ ነገር ክፍል።

**ከጎንህ ታገኘዋለህ** ያደረግከው ወይም የምታደርገው ነገር መጥፎ ውጤት ያስከትልብሃል ለማለት የሚነገር የማስጠንቀቂያ ወይም የዛቻ አነጋገር።

**ወደጎን ተጠመዘዘ /ታጠፈ** ወደ ቀኝ ወይም ወደ ግራ በኩል ተጠመዘዘ።

**የጎን ቁጥር** ስ በህዝብ ወይም በጭነት ማመላለሻ መኪናዎች ጎን ላይ ከታርጋ ቁጥር በተጨማሪ የሚፃፍ መለያ ቁጥር።

**የጎን ንግግር** አሽሙር።

**የጎን ውጋት ሆነበት** በጣም ነዘነዘው÷ ጨቀጨቀው፤ ፋታ ነሳው።

**ጎን ለጎን** አጠገብ ለአጠገብ።

**ጎናም** ስ ጎኑ ሰፊ የሆነ።

**ጎንባሳ** "*ጎነበሰ" ስር ተመ.

**ጎንዛላ** "*ጎነዘለ" ስር ተመ.

**ጎንዳላ** "ጎነደለ" ስር ተመ.

**ጎኘረ** ግ 1. ነፋ÷ ቆዘረ(ለሆድ)። 2. አጨቀ÷ ጠቀጠቀ÷ ሞላ(ከረጢትን)።

**ጉኘር** ቅ ቁዝር።

**ጎዘጎዘ** ግ 1. ነሰነሰ÷ በተነ÷ አነጠፈ(ሳርን÷ ቅጠልን÷...)። 2. አነጠፈ÷ ደለደለ÷ ጉዝጓዝ አደረገ(ለመኝታ÷ለመቀመጫ÷...)።

**ጉዝጓዝ** ስ 1. በቤት÷ በድንኳን÷ በዳስ÷... ወለል ላይ የሚነሰነስ÷ የሚነጠፍ ሳር÷ ቄጠማ ወይም ቅጠል። 2. ምቾት እንዲኖረው በመኝታ ወይም በመቀመጫ ላይ የሚደረግ ድልዳል።

**ጎደለ** ግ 1. ፊት የነበረውን ያህል ሳይሆን ቀረ፤ ሙሉ የነበረው መጠኑ ቀነሰ ወይም አነሰ። 2. የሚፈለገውን ያህል ሳይሆን÷ ሳይሞላ÷ ሳይገኝ ቀረ፤ መጠኑ ወይም ብዛቱ አነሰ።

**ጉድለት** ስ 1. እንከን÷ ስህተት። 2. ማነስ÷ መቀነስ÷ መጉደል። *ገንዘቡ ሲቆጠር ጉድለት አሳየ።* 3. እጥረት። *የቫይታሚን ጉድለት።*

**ጎደሎ(ጎዶሎ)** ቅ 1. ሙሉ ያልሆነ÷ የተቀነሰለት÷ ያልተሟላ። 2. የሰውነት ክፍሉ ወይም አካሉ ያልተሟላ(እጁ ወይም እግሩ የተቆረጠ÷ አይኑ የጠፋ÷..)። 3. (ዘይ.÷ስድብ) አጭር÷ ኩሩሩ።

**ጎደሎ ቀን** ስ መጥፎ አጋጣሚ(አደጋ÷ ሞት÷...) የደረሰበት ወይም ያጋጠመበት ቀን።

**ጎደሎ ቁጥር** ስ ለሁለት ሲካፈል ቀሪ የሚኖረው ቁጥር (ለምሳሌ 3÷5÷ 9÷ 11...)።

**ተጓደለ** ግ 1. ሲደረግ የነበረው ወይም የተለመደው ነገር ተቋረጠ÷ ቀረ÷ ተስተጓጎለ። 2.ሳይሟላ ቀረ÷ ጎደለ።

**አጎደለ** ግ 1. ካለው ወይም ከነበረው ነገር ላይ አነሳ÷ ቀነሰ። 2. (የሆነ ሰው ወይም እቃ) ባለመኖሩ ወይም ባለመገኘቱ የተነሳ መከናወን÷ መፈፀም÷... የሚገባው ነገር ሳይከናወን ወይም ሳይፈፀም ቀረ፤ አጎዳ።

**ጎደራ** ግ ጮሀ፥ አገሳ (ለምሳሌ አንበሳ)።

**ጎደሬ** ስ ስሩ እንደ ድንች ከመሬት ተቆፍሮ የሚወጣና የሚበላ ቅጠለ ሰፋፊ ተክል።

**ጎደበ** ግ 1. ጉድባ ሰራ። 2. አድፍጦ ጠበቀ።

**ጉድባ** ስ 1. ፈፋ፥ ጉድጓድ። 2. ምሽግ።

***ጎደኘ**

**ተጎዳኘ** ግ 1. (በስራ፥በአላማ፥...) አብሮ ሄደ ወይም ተጓዘ፤ ተወዳጀ። 2. ተጣመረ።

**አጎዳኘ** ግ 1. (በስራ፥ በአላማ፥...) አብሮ እንዲጓዝ ወይም እንዲሄድ አደረገ፤ አወዳጀ። 2. አጣመረ።

***ጎደደ**

**ጎዳዳ** ቅ ጅንን፥ ኩሩ።

**ተጓደደ** ግ ኮራ፥ ተጀነነ፥ ታበየ።

**ጎደጎደ(ጎረጎደ)** ግ 1.ጥልቀት ኖረው፤ ጉድጓድ ሆነ። 2. ዝርግ የሆነ ወይም ሞላ ወይም ወጣ ያለ ነገር ወደ ውስጥ ገባ፥ ተሰረጎደ።

**ጉድጓድ** ስ ወደ ታች ተቆፍሮ ወይም ተምሶ ክፍት የሆነ መሬት።

**ጉድጓድ ገብተህ ታመጣለህ** ከየትም ፈልገህ ታመጣለህ።

**ጎድጓዳ** ቅ ዝርግ ያልሆነ ወይም ወደ ውስጥ የሰረጎደ።

**ጎድጓዳ ሳህን** ስ ዝርግ ያልሆነ፥ እንደብረት ድስት የተሰራ ሳህን።

**አጎደጎደ** ጥልቀት እንዲኖረው አድርጎ ቆፈረ።

***ጎደጎደ**

**ነጎድጓድ** ስ የመብረቅ ድምፅ ወይም ጉርምርምታ።

**ተንጎደጎደ** ግ 1. ጮሀ ወይም የነጎድጓድ ድምፅ ተሰማ። 2.ተንገረቀገረቀ፥ በብዛት ፈሰሰ፥ ወረደ። 3. በብዛት ሆነ ወይም ተደረገ።

**አንጎደጎደ** ግ 1. የነጎድጓድ ድምፅ አሰማ። 2. በብዛት ሰጠ፥ አንጎደጎደ። 3. አወረደ፥ አፈሰሰ። *ዝናቡን አንጎደጎደው።*

**ጎደፈ** ግ 1. አደፈ ወይም ቆሸሸ። 2. ጠፋ፥ ተበላሸ (ስም፥ክብር፥ ዝና፥..)።

**ጉድፍ** ስ ቆሻሻ ወይም ጥራጊ።

**አጎደፈ** ግ 1. አቆሸሸ። 2. (ዘይ.) አጠፋ፥ አበላሸ(ስምን፥ ክብርን፥ዝናን፥..)።

**ጎደፈረ** ግ ጫረ፥ ማሰ፥ ቆፈረ።

**ጎዳ** ስ 1. ቀንድ የሌለው(ከብት)። 2. ጥለት የሌለው(ጋቢ፥ ኩታ፥...)።

**ጎዳ** ግ 1. ችግር፥ ስቃይ፥ ህመም፥... አስከተለ (አደጋ፥ ዱላ፥...)። 2. በደለ፥ ቅር አሰኘ፥ አስቀየመ። 3. አድሎአዊ በሆነ ወይም ባልተመጣጠነ ወይም ትክክል ባልሆነ፥... ሁኔታ አንድን ነገር አደረገ። *ዳቦውን ሲያካፍል እኔን ጎድቶኛል/ ጫማውን ሲሸጥልኝ በዋጋ ጎድቶኛል።*

**ጉዳት** ስ 1. ችግር፥ ስቃይ፥ ጉስቁልና(በህመም፥ በአደጋ፥ በሃዘን፥... ምክንያት የሚመጣ)። 2. ትክክል፥ ተገቢ፥ ተመጣጣኝ ባልሆነ ሁኔታ የተፈፀመ ድርጊት። የአንድ ነገር መሰበር፥ መበላሸት፥... ወይም የአካል መጉደል።

**ጉዳተኛ** ቅ ጉዳት የደረሰበት(ሰው)።

**ጎጂ** ቅ ጉዳት የሚያስከትል።

**ጎጂ ባህል** ስ በሰው ላይ ጉዳት የሚያመጣና ሂላቀር የሆነ ባህል፥ ልማድ።

**ተጎዳ** ግ የቅርብ ዘመድ ሞተበት።*እገሌ ሰባቱን ተጎዳ።*

**አጎዳ** ግ (የሆነ ሰው ወይም እቃ) ባለመኖሩ ወይም ባለመገኘቱ የተነሳ መከናወን ወይም መፈፀም የሚገባው ነገር ሳይከናወን ወይም ሳይፈፀም ቀረ፤ አጎደለ።

**ጎዳና** ስ መንገድ።

**ጎዳዳ** "ጎደደ" ስር ተመ.

**ጎድን** ስ 1. በግራና በቀኝ በኩል ከአከርካሪ አጥንት እስከ ደረት አግድም የሚዘረጋና በቀኝ አስራ ሁለት በግራ አስራ ሁለት ሆኖ የሚገኝ የደረት አጥንት። 2. ጎን። 3. ጎድን! እንዳይገፋህ ወይም ዞር በል ለማለት የሚነገር ቃል(የተጫነ አህያ በሰዎች አጠገብ በሚተላለፍበት ጊዜ)።

**የጎድን አየ** 1. ገረመመ። 2. ገላመጠ።

**ጎድን ጥብስ** ስ ለምግብነት ከነአጥንቱ ተጠብሶ የሚዘጋጅ የከብት ጎድን።

**ጎድጓዳ** "ጎደጎደ" ስር ተመ.

**ጎደሎ** "ጎደለ" ስር ተመ.

**ጎጂ** "ጎዳ" ስር ተመ.

**ጎጆ** ስ 1. ጎጆ ቤት። 2. (ዘይ.) የትዳር ኑሮ።

**ጎጆ ቀለሰ** 1. ጎጆ ቤት ሰራ። 2. ትዳር መሰረተ።

**ጎጆ ወጣ** 1.ትዳር መሰረተ። 2. እራሱን ችሎ ለብቻው መኖር ጀመረ (ከነሚስቱ ከወላጆቹ ጋር ይኖር የነበረ)።

**ጎጆ መውጫ** ላልተደራጀና የራሱን ቤትና ትዳር ገና ለሚመሰርት ሰው የሚሰጥ ማቋቋሚያ(ገንዘብ፥ እቃ፥...)።

**ጎጆ ወጪ** 1. አዲስ ትዳር መስራች። 2. እራሱን ችሎ ለብቻ መኖርን ገና የጀመረ።

**ጎጆ አወጣ** ለአንድ ሰው ገንዘብ፥ እቃ፥... በመስጠት ራሱን እንዲችል ወይም እንዲቋቋም አደረገ።

**ጎጆ ቤት** ስ አነስተኛ የሳር ቤት።



ጎጆ ቤት

**የጎጆ ኢንዱስትሪ** ስ እንደ ፋብሪካ ውስብስብ ቴክኖሎጂና የማምረቻ መሳሪያዎችን ሳይጠቀም በቤት ወይም በመኖሪያ አካባቢ ተወስኖ ልዩልዩ የፍጆታና የአገልግሎት ውጤቶችን የሚያመርት አነስተኛ ኢንዱስትሪ።

**ጎጠረ** ግ ነፋ፥ ቀበተተ(ሆድን)።

**ጉጥር** ቅ (ስድብ) ሆዱ የተነፋ ወይም ጉስር ያለ።

**ጎጠጎጠ** ግ ወጋ፥ወጋ አደረገ። *በጣቱ ጎጠጎጠው።*

***ጎጠጎጠ**

**ጉጥ** ስ 1. በእንጨት ላይ እንደ ጡት ጉብ ጉብ ብሎ የሚታይ የእንጨቱ ክፍል። 2. በማንኛውም ነገር ላይ አበጥ ወይም ጉብ ብሎ የሚታይ አካል።

**አጎጠጎጠ** ግ 1. መውጣት ወይም ማደግ ጀመረ(ጡት)። 2. አበቀለ፥ አጎመጎመ(ተክል ላይ የሚወጣ ጉጥ)።

**አጎጠጎጤ** ቅ ጡቶቿ ቆም ቆም ማለት የጀመሩ ወይም ለአካለ መጠን የደረሰች (ልጃገረድ)።

**አጎጤ** ቅ 1. አጎጠጎጤ። 2. ቆም ቆም ማለት የጀመረ ጡት።

**ጎጥ** ስ 1. ጉብታ፥ ኮረብታ። 2. መንደር።

**ጎፈረ** ግ አደገ ወይም እንደ ጎፈሬ ሆነ(ፀጉር)።

**ጎፈሬ** ስ ተከርክሞና ተበጥሮ ቀጥ ብሎ የሚቆም ፀጉር

**ጎፈር** ስ 1. የአንበሳ ወይም የዝንጀሮ ጋማ ወይም ፀጉር። 2. እንደ ቆብ ተዘጋጅቶ በራስ ላይ የሚጠለቅ የአንበሳ ወይም የዝንጀሮ ፀጉር ። 3. ከአንበሳ ቆዳ የተዘጋጀ ለምድ።

**አጎፈረ** ግ ፀጉሩን እንደ ጎፈሬ አሳደገ።

**ጎፈነነ** ግ አንገሸገሸ፥ አንገፈገፈ(ጣእም)።

**ጎፍናና** ቅ የሚያንገሸግሽ፥ ጎምዛዛ (ለጣእም)።

**ጎፈየ** ጉፋያ ሆነ።

**ጉፋያ** ቅ 1. የማይታኝክ፥ አንጀ(ስጋ)። 2. የከሳና ያረጀ (ከብት)። 3. (ዘይ.፥ስድብ) ያረጀ፥ የሸመገለ(ሰው)።

**ጎፈጎፈ** ግ አረጀ፥ ሸመገለ።

**ጎፍጓፋ** ቅ (ስድብ) ያረጀ፥ የደከመ።

**ጎፈጠጠ** ግ በእርጅና ወይም በህመም ምክንያት ጎበጠ።

**ጎፍጣጣ(ጉፍጥጥ)** ቅ (ስድብ) ያረጀ፥ የደከመ።

**ተንጎፈጠጠ** ግ ጎፈጠጠ።

**ጎፈጨረ** ግ በጥፍሩ ጫረ፥ ሟጨረ፥ ቧጠጠ።

***ጎፈፈ**

**ጎፋፋ** ቅ ቀርፋፋ፥ ቅልጥፍና የሌለው፥ ጎታታ።

**ተንጓፈፈ** ግ በአለባበሱ ዝርክርክ ብሎ እየተጎተተ ወይም እየተንቀረፈፈ ተራመደ፥ ሄደ።

**ጎፋ** ግ በረገገ፥ ወገሸ።

**ጎፍላ[1]** ስ በሞተ ጥጃ ቆዳ ውስጥ ገለባ በመጠቅጠቅ የሚሰራ የጥጃ ምስል።

**ጎፍላ[2]** ስ በሽጉጥ ማህደር፥ በመጎናፀፊያ፥... ዙሪያ የሚገኝ የክር ወይም የሃር ወይም የሱፍ ዘርፍ።

**ጎፍናና** "ጎፈነነ" ስር ተመ.

**ጎፍጓፋ** "ጎፈጎፈ" ስር ተመ.

**ጎፍጣጣ** "ጎፈጠጠ" ስር ተመ.

**ጓ[1]** የ "ገ" ፊደል ፍንፅቅ ዘር።

**ጓ[2]**

**ጓጓታ** ግ በመተረማመስ ወይም በመጋጨት የሚሰማ ድምፅ።

**ጓ አለ** ግ እንደ በርና መስኮት ያለ ነገር ሲጋጭ የሚሰጠውን ድምፅ አይነት ሰጠ።

**ጓጓ አለ** ግ ተንጓጓ።

**ጓጓ አደረገ** ግ አንጓጓ።

**ተንጓጓ** ግ በመተረማመስ ወይም በመጋጨት በተደጋጋሚ ጓ ጓ የሚል ድምፅ ሰጠ።

**አንጓጓ** ግ በማተረማመስ ወይም በማጋጨት በተደጋጋሚ ጓ ጓ የሚል ድምፅ እንዲሰጥ አደረገ።

**ጓል(ጉል)** ቅ ያልደቀቀ፥ አንኳር (የአፈር፥ የስኳር፥ የጨው፥...)።

***ጓመጠ**

**አጓመጠ** ግ ባፉ ሙሉ ጎርሶ አኘከ ወይም አላመጠ።

**ጓሚያ** ስ 1. ያልበሰለ ወይም ገና ጥሬ የሆነ(ፍራፍሬ)። 2. ከጮርቃነት ያለፈና በቃሪያነት ደረጃ ላይ ያለ ፍራፍሬ።

**ጓሮ** ስ በቤት ጀርባ ያለ ቦታ።

**የጓሮ አትክልት** ስ እንደ ሽንኩርት፥ ጎመን፥ ድንች ያለና በቤት አካባቢ የሚተከል አትክልት።

**ጓሳ** ስ ለገመድ፥ ለቤት ክዳን፥ ለወፍጮ

መጥረጊያ÷... የሚያገለግልና በደጋ አካባቢ የሚገኝ ቀጭንና ሻካራ የሳር አይነት::

**ጓነ** ግ ወደ ላይ ተወረወረ÷ ነጠረ::

**አጓነ** ግ ወደ ላይ ወረወረ ወይም አነጠረ::

**ጓንት** ስ በእጅ ቅርፅ ከላስቲክ ወይም ከሱፍ ወይም ከቆዳ÷... የሚሰራና ለእያንዳንዱ ጣት ማስገቢያ ያለው የእጅ ሽፋን፣የእጅ ሹራብ::



ጓንት

**ጓንዴ** ስ ስድስት ጥይት የሚጎርስ አፈ ዱልዱም የጠመንጃ አይነት::

***ጓዘ**

**ጉዞ** ስ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ በእግር ወይም በሌላ የመጓጓዣ አይነት የሚደረግ እንቅስቃሴ::

**ጉዞ ፍታት** ስ (ኢ .ኦ. ተ. ቤ .) አስከሬን ከቤት ወጥቶ መቃብር ቦታ እስኪደርስ ድረስ ሰባት ቦታ ላይ እያረፈ ለሰባት ጊዜ የሚደረግለት የፀሎተ ፍትሃት·አይነት::

**ጓዝ** ስ አብሮ ያለ ወይም የሚኖር ብዙ እቃ÷ ኮተት ወይም ቤተሰብ::

**ጓዙን ጠቀለለ** ያለውን እቃ ወይም ንብረት ሁሉ ጠቅልሎ ለመሄድ ተነሳ÷ ተዘጋጀ::

**ተጓዘ** ግ 1. ሄደ÷ ተራመደ:: 2. ጉዞ አደረገ:: 3. ገሰገሰ:: *በስልጣኔ ጎዳና ተጓዘ::*

**ተጓዥ** ቅ 1. ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ለመሄድ የተነሳ ወይም በመሄድ ላይ ያለ:: 2. በአንድ ቦታ ረግቶ የማይቀመጥ ወይም መንገድ የሚያበዛ::

**ተጓጓዘ** ግ ብዛት ያለው እቃ ወይም ሰው ከአንዱ ወደ ሌላው ቦታ ተጭኖ ተወሰደ÷ሄደ::

**መጓጓዣ** ስ 1. ከቦታ ወደ ቦታ ለመሄድ ወይም ለመንቀሳቀስ የሚያገለግል የጋማ ከብት÷ መኪና÷አውሮፕላን÷... (ስእሉን የሚቀጥለው ገፅ ላይ ተመ.):: 2. በመኪና÷ በአውሮፕላን÷ በመርከብ÷... ለመጓዝ የሚከፈል ገንዘብ::

**አጓዘ** ግ ብዛት ያለውን እቃ ወይም ሰው ከቦታ ወደ ቦታ ወሰደ::

**አጓጓዘ** ግ ብዛት ያለውን እቃ ወይም ሰው ከቦታ ወደ ቦታ ወሰደ::

**ጓያ** ስ በእሸትነቱ ከተመገቡት÷ እሸትም ባይሆን እንኳ እሱን በልቶ በላዩ ላይ ወተት ወይም ተልባ ከተጠጣበት ይሰብራል ወይም ያሽመደምዳል የሚባል አተር መሳይ እህል::

**ጓደኛ** "ጓድ" ስር ተመ.

***ጓደደ**

**ተጓደደ** ግ ኮራ÷ ተጀነነ (በትእቢት)::

**አጓደደ** ግ አኮራ÷ ጀነነ::

**ጓዳ** ስ በዋናው ቤት ውስጥ የሚገኝና ለማንኛውም ቁሳቁስ ማስቀመጫ የሚሆን ልዩ ክፍል::

**ጓዳዋን ያውቃል** ምስጢሯን÷ ገመናዋን÷ አኗኗሯን ያውቃል::

**የጓዳ በር** የምስጢር ወይም የስርቆሽ በር::

**ጓድ** ስ 1. ጓደኛ:: 2. በሶሻሊዝም ወይም በኮሚኒዝም ስርአት ውስጥ ያሉ የፖለቲካ አራማጆች እርስ በርሳቸው የሚጠራሩበት የአቶ ወይም የክቡር መተኪያ ስም:: 3. ለአንድ ስራ ወይም ተልእኮ የተመደበ ቡድን::

**ጓደኛ** ስ 1. ባልንጀራ:: 2. አቻ÷ ተመሳሳይ (በእድሜ ወይም በሌላ)::3. ወዳጅ::

**ጓደኛ አፈራ** ጓደኛ አገኘ ወይም አበጀ::

**ጓጉንቸር**[1] ስ 1. በአፈርና በድንጋይ ውስጥ የምትኖርና ቆዳዋ ሻካራ የሆነ የእንቁራሪት አይነት::

**ጓጉንቸር**[2] ስ ተንጠልጣይ የበር ቁልፍ (ስእሉን ቁልፍ ስር ተመ.)::

**ጓጎለ** ግ 1. (እንደ ዱቄት ያለ ነገር በውሃ ሲበጠበጥ) በደንብ ሳይሟሟ ወይም ሳይፈርስ ቀረ÷ አልፎ አልፎ እንደኳስ ተድቦልቡሎ ተገኘ::2. በእግር ብዙ ከመጓዝ ወይም ከባድ ስራ ከመስራት የተነሳ በሰውነት ላይ አልፎ አልፎ ህመም ተሰማ÷ ሰውነት ጣመነ::

**ጓጓላ** ግ (በውሃ ከተበጠበጠ እንደ ዱቄት ካለ ነገር ውስጥ አልፎ አልፎ ሳይሟሟ ወይም ሳይፈርስ እየተድበለበለ የሚገኝ ዱቄት::

**ጓጎረ** ግ ጮሀ÷ አጓራ::

**አጓጎረ** ዝ.ከ.

**ጓጎት** "አጓጎት" ን ተመ.

**ጓጎጠ** ግ 1. በጣት÷ በእንጨት÷... ነካ ነካ ወይም ወጋ ወጋ አደረገ:: 2. ለማስታወክ ጉሮሮውን በጣቱ ነካ ነካ አደረገ::3. አስታወከ ወይም አስመለሰ::

**አስጓጎጠ** ግ አስታወከ ወይም አስመለሰ::

**ጓጓ** ግ ተመኘ÷ ጎመጀ÷ ፈለገ::

**ጉጉ** ቅ አንድ ነገር ለማድረግ÷ ለማግኘት÷... ከፍተኛ ፍላጎት ወይም ምኞት ያለው::

**ጉጉት** ስ ከፍተኛ ፍላጎት ወይም ምኞት::

**አጓጓ** ግ 1. አማረ÷ ስሜት ሳበ:: 2. አንድን ነገር በማሳየት ሌላው ሰው እንዲመኝ ወይም እንዲፈልግ አድርጎ አስጎመጀ:: 3. አሳሳ::

**ጓጓታ** "ጓ[2]" ስር ተመ.

***ጓጠጠ**


**ማንጓጠጥ** ስ ማናናቅ÷ማጣጣል ወይም ማሽሟጠጥ::

**ተንጓጠጠ** ግ ተናቀ÷ተሽሟጠጠ::

**አንጓጠጠ** ግ አናናቀ÷ አቃለለ÷ አዋረደ ወይም አሽሟጠጠ::


**ጓፈለ** ግ አደፈ÷ ቆሸሸ (ልብስ)::

**አጓፈለ** ግ አቆሸሸ÷ አሳደፈ::


1



2



3


4


5


6


7


8


9


10

1.ብስክሌት
2.አውቶቡስ
3.የቤት መኪና
4.ባቡር
5.ሄሊኮፕተር
6.አይሮፕላን
7.ጀልባ
8.ሞተር ብስክሌት
9.መርከብ
10.ታንኳ